በየጊዜው የሚበለፅግ የአስደሳች ህይወት ሳይንስ

# ኑሮMAP

እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሕይወት ቀራፂ ነው!



ዶ/ር ኤርሲዶ ለንደቦ

Systems Thinking 4 Life Book 1

# ኑሮ MAP

**በዶ/ር ኤርሲዶ ለንደቦ**

(ከዮሃንስ ሰ. ጋር)



የቴሌግራም
ቻናላችንን
ለመቀላቀል ና
ሌሎች
መጽሐፍት ና
ትረካዎች
ለማግኘት
@amharicbooks24
ወይ
ወይም
ይሄን ይጫኑ

የፀሃፊው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።

© ዶ/ር ኤርሲዶ ለንደቦ

መጋቢት 2003 ዓ.ም.

የሽፋን ዲዛይን፡
ሃሳብ - ዶ/ር ኤርሲዶ ለንደቦ
ቅንብር- አሸናፊ ሰርፀ
ሃውልት - self made man በመባል በአለም የሚታወቅ
ሌይአውት ዲዛይን - ምስራቅ ደምሴ እና ዮሃንስ ሰ.
የአሳዎቹ መስሉች - Big fish eats small fish ከተሰኘ መፅሃፍ
ሌሎች ምስሎች - ዮሃንስ ሰ.

ምስጋና፡

ለባለቤቴ ለሲስተር ትዕግስት እንግዳ
እንዲሁም ለልጆቼ ሃኒ፣ አሴት፣ አዲስ እና ሃማም

ስማችሁ ባይጠቀስም ለረዳችሁኝ ጓደኞቼ በሙሉ
አመሰግናለሁ

መታሰቢያነቱ እና

## አክብሮትን ለመግለፅ - መታሰቢያነቱ

ከሁን በፊት ለነበሩ፣ አሁን ለሚኖሩ፤ ካሁን በኋላ ለሚኖሩ ፈርቀዳጅ ሰዎች (1sthanders) በሙሉ፣ ከብርና አድናቆት ይገባቸዋል። ከሰው ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ተመልከቱ...

አእምሯቸውን ተጠቅመው ይማራሉ፣ ያስተምራሉ እንጂ፤ ጭፍን ተከታይ ወይም አስከታይ አይሆኑም።

የራሳቸውን አላማ ይዘው በፍቃደኝነት ይተባበራሉ እንጂ፤ ገዢ ወይም ተገዢ መሆንን አይፈቅዱም።

ራሳቸውን ችለው፣ ምርትን በነፃነት ይገበያያሉ እንጂ መፅዋች ወይም ተመፅዋች መሆንን አይመርጡም።

ሰውን በባህሪውና በተግባሩ እየመዘኑ አሪፉን ያደንቃሉ እንጂ፤ በጭፍን በዘርና በሃይማኖት አይቧደኑም።

በተለያየ መጠንና ደረጃ እነዚህን መገለጫዎች የጠረጉ አሪጅናል ሰዎች ናቸው፤ ጀግኖች ማለት። ለምሳሌ፣ አቶ በቀለ ሞላ፣ ሃይሌ ገ/ስላሴ፣ ቢል ጌትስ፣ ቶማስ ኤዲሰን፣ አሪስቶትል፣ አየን ራንድ የመሳሰሉ..።

1. በሰው ሰራሽ ነገሮችና በእውኑ ተፈጥሮ (reality) መካከል ያለውን ልዩነት በአእምሯቸው አስተውለውና አስበው በግልፅ ላወቁ ሰዎች ከብርና አድናቆት ይገባቸዋል። የተፈጥሮ ህግ አይነኬነትን በመገንዘብ፤ የሳይንስ እውቀትንና የቴክኖሎጂ ፈጠራን አስፋፍተዋል።

2. ሰው ሰራሽ የሆነውን ነገር (ስርአትንና ህግን፣ ባህልና እምነትን ...) በሙሉ ለመመርመር የማይፈሩ፣ ትክክለኛነቱን ሳያረጋግጡ የማይቀበሉ ሰዎችም ከብርና አድናቆት ይገባቸዋል። የነፃነት ስርአቶችንና የፍትህ ህጎችን የተከሉ ናቸው፤ ስልጡን ባህልና ሳይንሳዊ አስተሳሰብንም አስፋፍተዋል።

3. የሰው ልጅን ድንቅ ጀግንነት በኪነጥበብ ስራዎቻቸው ላሳዩ ደራሲዎችና ሌሎች አርቲስቶችም ከብርና አድናቆታችን ከፍ ያለ ነው። ብሩህ የተነቃቃ መንፈስ የሚያነግሱ ናቸው።

4. ብቻቸውንም ይሁን በሰዎች ፊት፤ እውነትን እውነት የሚሉ፣ ውሸትንም ውሸት የሚሉ ቅን ሰዎች፤ ብቻቸውን ለማሰብ የማይፈሩና ካስፈለገም ለእውነታ ብቻቸውን ለመቆም የማያመነቱ ጀግኖች፣ ክብር ይግባቸው። ሰው የመሆን ክብርን ከፍ ከፍ አድረገዋልና።

5. ቅንነትና ጀግንነትን፣ ነፃነትንና ፍትህን፣ ሳይገነቡ ቴክኖሎጂን አዋህደው በምርታማነት ራሳቸውን ያበለፀጉ ሰዎች አድናቆት ይገባቸዋል። ለራሳቸው አላማ ሲሰሩ አለምን ጭምር የሚያበለፅጉ የስኬት ሰዎች አርአያዎቻችን ናቸው።

የመፅሃፉ መታሰቢያነት ለእነዚህ የስኬት ጀግኖች ያለንን ክብር የሚገልፅ ነው። በእርግጥም ውድቀት የስህተት ምልክት ነው። ትክክለኛውና "ኖርማሉ" የሰው ልጅ ህይወት፤ ከተፈጥሮው ጋር የሚስማማ የስኬት ህይወት እንደሆነ ጀግኖቹ በእውን አሳይተውናል።

## ማሳፈሪያነቱ

የሰውን ልጅ ታላቅነት ለማየት ለማይፈልጉ፣ ሰው በተፈጥሮው ደካማ፣ ሚስኪንና መናኛ ነው ብለው ለሚያምኑ

ጭፍን እምነታቸው ትክክል መስሎ እንዲታይ፤ የሰው ስኬት ሳይሆን ውድቀት እንዲበዛ ለሚመኙ

በአለም የሚያጋጥሙ ውድቀቶች በደፈናው ከሰው ተፈጥሮ የሚመነጩና ሊለወጡ የማይችሉ ናቸው ብለው ለሚፅፉ

በተፈጥሮአቸው የከንቱነት አባዜ ባይኖራቸውም፤ ከንቱነትን መርጠው ከንቱነትን ለሚሰብኩ (ለአዛዎች - ለ2nd hander ሰዎች)

ቅንብራዊ አስተሳሰብ............ 67
System thinking

ክፍል ሶስት የስኬት መሳሪያዎች............. 89

1. የማያዛልቅ ጥገና - ታጥቦ ጭቃ........ 90
(Fixes that fail)
2. ሸክምን ማንሸራተት - አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ........ 96
(Shifting the Burden)
3. ግብን መሸርሸር ትግልን ለመሸሽ - መነሳሳትና መቀዛቀዝ........ 102
(Drifting Goals)
4. መተጋተግ፤ መነቋቆር -. የቀከከር ቤት ሳይዘጋ ያድራል........ 108
(Escalation)
5. የሁሉ የሆነ የማንም - እኔ የሌለው እኛ፣ የእኔ የሌለው የእኛ........ 117
(Tragedy of the Commons)
7. የስኬት ገደቦች - ሁሉም ነገር ልክ አለው........ 123
(Limits to Success)
8. ኢንቨስትመንት የጎደለው እድገት - ሳይመገቡ ማለብ........ 137
(Growth and Underinvestment)

ክፍል አራት የህይወት ክህሎት............. 141

ክፍል አምስት ስኬታማ የህይወት ካርታ
(The 5Ps)...................... 159

1. ፍልስፍና/ አመለካከት........ 165
2. የህይወት አላማ........ 179
3. የስራ ውጤታማነት........ 186
4. የመንፈስና የኑሮ ብልፅግና........ 188
5. ብሩህ ስብእና........ 194

# መግቢያ

## ምን አይነት መጽሀፍ ነው?

ኑሮMap በሚል የቀረበው መፅሃፍ፤ አዲስና ውጤታማ የስኬት ሳይንስን በማስተዋወቅ የተግባር መሳሪያዎችን ያስታጥቃል።

"systems thinking" (ST) ይባላል ሳይንሱ። በማንኛውም የኑሮ መስክ፤ ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታትና ስኬታ ህይወትን ለመመስረት በስራ ላይ እየዋለ የሚገኝ አዲስ የሳይንስ ውጤት ነው። ባለፉት 50 አመታት እያደገ መጥቶ፤ ዛሬ ፍቱን የአስተሳሰብና የተግባር መሳሪያ ለመሆን በቅቷል። በአማርኛ ቅንብራዊ አስተሳሰብ ብለን ለመሰየም ሞክረናል።

ሰው በተፈጥሮው፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ በአእምሮና በአካል፣ በመንፈስና በሃብት እየበለፀገ የሚቀጥል አስደሳች ህይወት መኖር ይችላል። ተፈጥሮው ነው - ለጀግንነትና ለፍቅር ተጣጥሞ የተቀናበረ ክቡር ተፈጥሮ።

አስደሳች የብልፅግና ህይወት፣ እንዲያው በዘፈቀደ እውን አይሆንም። በትምህርትም ሆነ በስራ አለም፣ በቢዝነስም ሆነ በፍቅር ግንኙነት፣ በቤተሰብም ሆነ በተቋም፣ በማህበርም ሆነ በአገር ደረጃ፤ በሁሉም መስክ፤ የስኬት ጉዟችንን ለመጀመርና ለማፋጠን የምንችልበትን መንገድ ማወቅ አለብን።

ስኬትን ለመጎናፀፍ፣ ከተፈጥሮ ጋር ተጣጥሞ የተቀናበረ እንዲሁም በተጨባጭ ስራ ላይ ሊውል የሚችል ትክክለኛ አስተሳሰብና አስተማማኝ መሳሪያዎች ያስፈልጉናል።

የዚህ መፅሃፍ አላማም፣ ትክክለኛ የስኬት አስተሳሰብንና፣ አስተማማኝ የስኬት መሳሪያዎችን ማስታጠቅ ነው።

### የመፅሃፉ ተደራሽነት

ስኬት ለሁሉም ሰው ተገቢ የመሆኑን ያህል፤ የስኬት መፅሃፍም ለሁሉም ሰው ግልፅ በሆነ አቀራረብ መዘጋጀት ይኖርበታል።

አሁን የምታነብቡት መፅሃፍ፤ የስኬት አስተሳሰብን ከነመሳሪያዎቹ በግልፅ አቀራረብ አጣምሮ ይዟል። እያንዳንዱ የመፅሃፉ ክፍልና ርእስ ጉዳይ፣ እያንዳንዱ ገፅና አረፍተ ነገር፤ በጥንቃቄ የተመረጠ ነው - ጠቅላላ የመፅሃፉን አላማ ከግብ ለማድረስ። ማንኛውም ግለሰብ በህይወቱና በተሰማራበት የኑሮ ዘርፍ ውስጥ እንዲጠቀምበት፤ ተጨባጭ አዎንታዊ ለውጥም እንዲያገኝበት ታስቦ የተዘጋጀ የመጀመሪያው የቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST) መጽሐፍ ነው።

የተበጣጠሱ እልፍ የምክር ሃሳቦችን የመደርደር ጉዳይም አይደለም። ሰው፣ ርቦት አይደለም። "እንዲህ አይነት ችግር ሲያጋጥምህ፣ ይህንን አድርግ"፣ "እንዲያ አይነት ችግር ሲመጣብህም፣ ያንን አድርግ"፣ "ለእንትን ስኬት ደግሞ እንደዚያኛው..." የሚሉ ሚሊዮን ነጠላ ምክሮች ቢዘረዘሩ፣ ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ያመዝናል። ግራ መጋባትን ከማምጣት ያለፈ ፋይዳ አይኖራቸው - ብጥስጣሽ የምክር ሃሳቦች።

በደፈናው አስተሳሰባችንን እንለውጥ ብሎ መናገር በቂ አይደለም። ችግሮችን እየፈታን፣ በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወት ለመጎናፀፍ፣ ትክክለኛውና ተመራጩ የስኬት አስተሳሰብ ምን አይነት እንደሆነ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። ከትክክለኛ አስተሳሰብ ነው፣ ሚሊዮን ትክክለኛ ሃሳቦች የሚመነጩት። ከዚህም ጋር ሚሊዮን ውጤታማ እቅዶችና ስራዎች በተጨባጭ እየተከናወኑ ስኬቶች እውን ይሆናሉ።

አእምሮን በመጠቀም፣ አስተዋይነትን መጨበጥና እውቀትን ማዳበር፤ ... እውቀትን ለምርትና ለቢዝነስ ማዋል፤ በነፃነት ተከባብሮ በራስ ጥረት ሙያንና ሃብትን ማበልፀግ፣ በውጤቱም መጠቀምና ህይወትን ማሻሻል... እነዚህ ሁሉ፣ ከትክክለኛ አስተሳሰብ የሚመነጩ ናቸው። ለራስ የሚኮሩበትና የሚረኩበት ክቡር ሰብእና፣ የደስታና የፍቅር ጣፋጭ ህይወት፣ በአጠቃላይ ምሉእ የስኬት ሰብእና ... ከንቱ ወሬ ሳይሆን፣ ተጨባጭ እውነታ ነው። ይሄ ነው ከሰው ተፈጥሮ ጋር የተጣጣመ ህይወት።

በእርግጥ፤ በዙሪያችን ከደስታ የራቁ መራራ የችግር ኑሮዎችን በብዛት እናያለን። ግን የማይለወጡና ዘላለማዊ አይደሉም። አጣፈንታና እርግማን ብሎ ነገር የለም። ውድቀትና ችግር፤ በተሳሳቱ አስተሳሰቦች ምክንያት የሚመጡ ናቸው። እነዚህን መንስኤዎች አንጥሮ በግልፅ ለማየት የሚያስችል ነው - በክፍል አንድ "አሳዎቹ" በሚል ርዕስ የቀረበው አጭር ግራኪ ትረካ።

የበለፀጉ አገራትን ተመልከቱ። አንዳንዶቹ ከሶስትና አራት መቶ አመታት በፊት በድህነትና በችጋር የሚሰቃዩ ነበሩ። አንዳንዶቹ ደግሞ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በረሃብ የሚታወቁ ነበሩ። ያንን ኑሮ ወደ አስደሳች የብልፅግና ህይወት ቀይረዋል። ሩቅ መሄድም አያስፈልገንም። የኑሮ ችግሮችን በፅናት አሸንፈው በትጋት ህይወታቸውን ያበለፀጉ ስኬታ ሰዎች በየሰፈራችንና በየአካባቢያችን እንዳሉ በቅርበት እናውቃለን።

ሁላችንም ትክክለኛ አስተሳሰብን ከነመሳሪያዎቹ በመያዝ ህይወታችንን መለወጥ እንችላለን፤ የአጣፈንታ ሳይሆን የምርጫ ጉዳይ ነውና። ከተሳሳተ አስተሳሰብ የሚመነጨውን ውድቀትና ችግር በማስወገድ፤ ስኬትና ብልፅግናን መጎናፀፍ እንችላለን - በትክክለኛ አስተሳሰብ።

የመፅሃፉ ሁለተኛ ክፍል፤ የትክክለኛ አስተሳሰብ ምንነትን ቀላልና ግልፅ በሆነ መንገድ የምናስተዋውቅበት ነው - ቅንብራዊ አስተሳሰብ (system thinking) በሚል ስያሜ። የቅርብና የሩቅ ታሪኮችን፣ የውድቀት መንስኤዎችንና የስኬት መሰረቶችን፣ የድሮና የዘመናችን አዳዲስ

መረጃዎችንና እውቀቶችን ከመመርመር የተገኘ ነው - ቅንብራዊ አስተሳሰብ። ከመመርመር አልፎም፤ ሃሳቦቹን አንጥሮና አጣርቶ በመቀመር ያቀናበረ አስተሳሰብ ነው።

አርኪታይፐስ የሚለው የመፅሃፉ ሶስተኛ ክፍል፤ የነጠሩና የተቀመሩ ሃሳቦችን እንዲሁም የስኬት መሳሪያዎችን ከነአተገባበራቸው እየፈተሸን፤ እንዴት ወደ አስደሳች የብልፅግና ህይወት ጉዞ መጀመር እንደምንችል ያስረዳል።

የነጠሩ፤ የተጣሩ፤ የተቀመሩ ግልፅ ሃሳቦችን አጥር ምጥን አድርጎ ማቅረቡ ብቻ ሳይሆን፣ ሃሳቦቹንም አርስበርስ አቀናብሮ ይዟል። የችግር መንስኤዎችንና የስኬት መሰረቶችን ለማወቅ አስተማማኝ የአእምሮ ብቃት ማስጨበጥ ብቻ ሳይሆን፤ በተግባር ችግሮችን ለማስወገድና ስኬቶችን ለመቀዳጀት የሚያስችሉ መሳሪያዎችን ያስታጥቃል።

ሃሳባችንን፣ ተግባራችንንና አላማችንን፤ ከእውኑ ተፈጥሮ ጋር አጣጥመን የምንመራበት የስኬት መንገድ ላይ ነው የምንጓዘው - የእውነት፤ የህይወትና የፍቅር ስኬታማ መንገድ። (ከእውኑ ተፈጥሮ ጋር የሚጣላ አስተሳሰብ ደግሞ በተቃራኒው፤ የውድቀት መንገድ ነው።)

## የራሳችን መሪ መሆን

አስደሳች የብልፅግና ህይወትን ለመቀዳጀት የወጠንነው አላማ እውን እንዲሆንና ግቦቻችን እንዲሳኩ የምናደርግበት ብቃት፤ በጥቅሉ የህይወት ክህሎት ይባላል። የመጀመሪያዎቹን የመፅሃፉ ሶስት ክፍሎች በሚያጠናክር መንገድ፤ አራተኛው ክፍል የህይወት ክህሎትን መጠቀምና መገንባት ላይ ያተኩራል።

የህይወታችንን አቅጣጫ የምንወስነው ወይም መሪውን የምናሽከረክረው ራሳችን ነን። መሪው የተፈጥሯችን አካል ነው። መሪው በእጃችን ነው (መሪው በአእምሯችን ነው)። ግን መሪውን መጠቀምና አለመጠቀም እንዲሁም የመሪውን አቅጣጫ መወሰን የእያንዳንዳችን ምርጫ ነው።

መሪው በእጃችን ስለሆነ፤ አንዳንዴ በገዛ ራሳችን ህይወታችንን እናወሳስበዋለን። በተሳሳተ ምርጫ፤ ህይወት እንድትጨልምና እንድትወሳሰብ የሚያደርግ አቅጣጫ እንጓዛለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ ትክክለኛ ምርጫ ህይወት በጣም አጓጊና ብሩህ እንድትሆን እናደርጋታለን። የህይወትን ሂደት (Life Process) በአግባቡ የመምራትና ያለመምራት ጉዳይ ነው። በዋናው የሚበለፅግ አስደሳች የህይወት ሂደትን በመፅሃፉ ክፍል አምስት እንመለከታለን - የስኬታማ ህይወት ካርታ በሚል ርእስ።

አንዳንዴ፤ በተግባር ከመሞከር ይልቅ በፍርሃት ከስኬት እየራቅን፤ ችግር ሲፈጠርም

"የኑሮMAP ድህረገጽ የፖስታና የኢሜይል ውይይት" (Disscussion groups) እንዲሁም "የኑሮMAP ንባብና እውቀት ክለብ" ስለሚያቋቋሙ ልዩ ድጋፍ ይደረግላችኋል፡፡

6. ከምንም በላይ የእውቀት ጥቅም ችግሮችን በመፍታት፣ ተግዳሮቶችን በማሸነፍና ስኬትን በመቀዳጀት ሕይወትን በተጨባጭ ለመቀየር ስለሆነ፤ የመጽሐፉን ዋነኛ ፅንሰ ሀሳቦች በቀን ተቀን ሕይወታችሁ ተጠቀሙባቸው።

በየጊዜው የምታገኟቸውን ውጤቶች (የሕይወት ልምዶች) ቢፅፉልን በቀጣይ የመፅሃፍ ህትመቶች፤ የናንተ ታሪክ ሌሎችን ለማስተማር ሊታተም ይችላል፡፡ አክብሮታችንንም ለመግለፅ ሽልማት እናዘጋጃለን።

ይህንን መፅሃፍ ለማንበብ ይህችን ሰዓት ስለሰጡ በራስዎ ስም አመሰግንዎታለሁ።

መልካም የንባብ ጊዜ ! መልካም የእስተሳሰብና የተግባር ለውጥ ለራስዎ፣ ለቤተሰብዎ፣ ለቢዝነስዎ፣ ለመስሪያቤትዎ!

በእርግጥም ያኔ ኢትዮጵያ ትለወጣለች !

ዶ/ር ኤርሲዶ ለንደቦ

Email:-erssido@yahoo.com

WWW.Dr.erssidobooks.Com

# ክፍል 1

# የአሳምቹ ታሪክ

## አሳምቹ ፡ ለአዲሱ ሚሌኒየም የማይገጥም ቀሽምነት

በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወትን መቀዳጀት እየቻልን፤ ለምን በአሰልቺ የድብርት ህይወት እንሰቃያለን?

ስኬትኮ ላወቀበት ወለል ብሎ የተከፈተ የህይወት መንገድ ነው። ታዲያ ለምን በውድቀት አዙሪት ህይወትን እናባክናለን? ዋናዎቹ የውድቀት መንስኤዎች እጅግ ከባድ ችግሮች ይመስላሉ እንጂ፤ በመናኛ ስህተቶች ሰበብ የሚፈጠሩ ናቸው። የስህተቶቹን ምንነት ለይተን ካወቅን ችግሮቹን ነቃቅሎ ለመጣል አይከብደንም።

የመፅሃፉ ትኩረት፤ አስተማማኝ የስኬት መሳሪያ ማስጨበጥ ነው። በቅድሚያ ግን መናኛዎቹን ስህተቶች ለይተን ለመገንዘብ፤ አሳምቹ በሚል ርእስ የቀረበውን አጭርና ማራኪ ትረካ እናንብብ።

በትረካው የምናገኛቸው የእነ ቁባርና የእነ በርጊ አገር ነዋሪዎች፤ ለስህተቶች የሚዳረጉት፤ አለምክንያት አይደለም። ስህተቶች በገፍ የሚፈለፈሉት፤ ከቀሽም አስተሳሰብ ነው። ቀሽሙን አስተሳሰብ፤ "ለአዲሱ ሚሌኒየም የማይገጥም (incompatible) ቀሽም የህይወት ሶፍትዌር" ልንለው እንችላለን።

ትረካውን ካየን በኋላ፤ ስህተቶቹን እንጥረን በማውጣት፤ ሁነኛ መፍትሄ ማበጀት ብቻ ሳይሆን አስተማማኝ የስኬት መሳሪያ መታጠቅ እንጀምራለን - (አዲስና ስኬታማ የህይወት ሶፍትዌር)።

# አሳዎቹ



ዋው! ትልቅ አሳ ይሄውና።

ትንሽ አሳ ደግሞ ይሄው።።



ትልቁ አሳ ትንሹን አሳ ይበላዋል - ዋጥ ነው።። አንዳንዴም ትንንሽ አሳዎች ተረባርበው ትልቁን አሳ እየነከሱ ይቦጫቁታል።።



«መበላላትኮ የሕይወት እውነታ ነው» ይባላል።። ደግሞም፤ ያለምክንያት ዝም ተብሎ የተነገረ ጉዳይ አይደለም።። በዚህ ትስማማላችሁ? «አዎ» የሚል ምላሽ ብትሰጡ አይገርምም።። ዛሬ በየእለቱ የምናየውና የሚያጋጥመን ነገር ነው - «ትልቁ»፤ «ትንሹ» ተባብለው በዘር መቧደንና መበላላት!

በፊት - በፊት ግን ኑሮ እንዲህ አልነበረም:: ድሮ - ድሮ፣ አሳ አሳን አይበላም ነበር:: የባህር ውስጥ ዕፀዋት ነበር ምግባቸው:: የባህር ዕፀዋት ተከለው አያበቅሉና አያጨዱ ይኖራሉ:: በእርግጥ ይህ የሆነው፣ የባህር ተክል እንዴት እንደሚበቅልና እንደሚያድግ በማስተዋል ካገናዘቡ በኋላ ነው:: «ህይወትን በየጊዜው ማበልፀግ» የሚል አላማ በመያዝ፣ ብዙ ምግብ ለማምረት ወስነው በብርታት ወደ ስራ ሲገቡ... ብዙ ስህተት፣ ብዙ ፈተና፣ ብዙ ድካም አጋጥሟቸዋል::

ነገር ግን በግልና በህብረት ባደረጉት ጥረት፣ ውጤት ማግኘታቸው አልቀረም:: ምግብ አምርተዋል:: ይህም ብቻ አይደለም:: እዚያው በዚያው ለምርታማነት የሚጠቅም፣ «ትልቅ ሃብት» እየገነቡ ነበር:: ትልቁ ሃብት ምን መሰላችሁ? ብቃት ልትሉት ትችላላችሁ - ሶስት አይነት ብቃት:: አንደኛ፣ በተሞክሮና በምርምር ስህተታቸው እየታረመ፣ አስተዋይነታቸውና እውቀታቸው እያደገ መጣ:: ሁለተኛ፣ ስራ ላይ በመትጋታቸው፣ ብርታትና ልምድ አዳበሩ:: በዚያውም፣ የአላማ ፅናትና በራስ የመተማመን መንፈሳቸው ተጠናከረ - ሶስተኛ::

እንዲህ ብቃታቸው ሲጨምር ደግሞ፣ ይበልጥ ምርታማ እየሆኑ፣ በምርታማነታቸው ደግሞ እንደገና ብቃታቸው እየመጠቀ፣ የስኬት ምህዋር ፈጥረዋል (Virtous reinforcing Loop):: ህይወታቸው በየጊዜው እየበለፀገ በደስታ ይኖራሉ::

ለብዙ ዘመናት፣ አንዳችም ነገር አልተለወጠም:: ሕይወት በየጊዜው የምትበለፅግ አስደሳች ነበረች:: ፈፅሞ የምግብ ችግር አልነበራቸውም:: እንዲያውም፣ በየግላቸው ከፍተኛ ትርፍ ስለሚያመርቱ፣ ሃብት አከማችተዋል:: ለልጆች ማውረስም የተለመደ ነበር:: ቤተመፃህፍት መክፈት፣ የተቸገሩ ጎበዝ ተማሪዎችን ማገዝ፣ በአጠቃላይ በልግስና ማህበረሰብን ለሚጠቅም ስራ እርዳታ መስጠት ይችሉ ነበር::



ከዚህ በኋላ ነው፣ አሳዎች እንደልባቸው ተዘዋውረው የሚመገቡባቸው የጋራ የአትክልት ማሳዎች እንዲቋቋሙ የተደረገው:: ቀስ በቀስም ብዙ አሳዎች ዕፀዋት መትከል እያቆሙ፣ የግል ማሳዎች እየጠፉና በጋራ ማሳዎች እየተተኩ

መጡ፡፡ በቃ፤ የጋራ ማሳዎች ውስጥ ገብተው እየበሉ ሲዝናኑ ይውላሉ፡፡ ትምህርትም ሆነ ስራ እየተረሳ ነው፡፡

ግን ችግር የለም፤ ምግብ ሞልቷል፡፡ በቀለምና በቅርፅ የሚለያዩ ብዙ አይነት አሳዎች እንደ አንድ ትልቅ ደስተኛ ቤተሰብ ነበር የሚኖሩት፡፡ የቀለምም ሆነ የቅርፅ ልዩነት፤ ማንኛውም የዘር ልዩነት ለአሳዎች ትርጉም አልነበረውም፡፡

ይሄ ቁሳር ይባላል፡፡

ትልቅ አሳ ነው፡፡ ነገር ግን፣ ትልቅ ስራ የሚሰራ ወይም ከባድ ሃላፊነት የያዘ አሳ አይደለም፡፡ ቁሳር ገና የአንድ አመት ህፃን ነው - የትልቅ ዓሳ ዘር ተወላጅ፤ ትንሽዬ ልጅ፡፡



ይሄኛውስ? ትንሽ አሳ ነው፡፡



ነገር ግን፤ የትንሽ አሳ ዘር ተወላጅ ስለሆነ እንጂ፤ ብዙ ሺ ልጆች እንዲሁም የልጅ ልጆች ያሉት፤ ሽማግሌ አሳ ነው፡፡ በዚያ ላይ፤ የጋራ የአትክልት ማሳዎች እንዲስፋፉ በመቀስቀስና ተሰሚነትን በማግኘት ታዋቂነትን አትርፏል፡፡ ከልጅ ልጆቹ መካከል አንዷ፤ በርገር ትባላለች - በቅጽል ስሟ በርጊ ይሏታል፡፡ የቁሳር ጓደኛ ነች፡፡ እያደገች ስትመጣም ፍቅረኛው ሆናለች።

ቋሳርና በርጊ፤ የትልቅና የትንሽ አሳ ዘር ተወላጆች ቢሆኑም፤ ከጓደኞቻቸው ጋር አብረው ነው የሚጫወቱት።



አያቶቻቸውና ቅድመ አያቶቻቸውም በልጅነታቸው ዘወትር አብረው ነበር የሚጫወቱት፤ ወደ ትምህርት ቤትም የሚሄዱት።

እነ ቋሳርና በርጊ ግን እድሜያቸው ከደረሰ በኋላም፤ በፍፁም ትምህርት ቤት ሄደው አያውቁም። የጋራ ማሳ ውስጥ ሲበሉና ሲጫወቱ ይውላሉ። እድሜያቸው ከፍ ሲልም፤ እየተጋቡ ይወልዳሉ፤ ይዋለዳሉ።




ድሮ ድሮ የአሳዎች ትምህርት ቤት ሁሌጊዜ በተማሪዎች የተሞላ ነበር። ዛሬ ዛሬ ግን ባዶውን ቀርቷል። መማር ትተዋል

አሳዎች ትምህርት ቤት መሄድ አቁመዋል:: መዋለድ ግን አላቆሙም:: ተምረው አያውቁም፤ ቁጥራቸው ግን እየበዛ ነው:: ቁጥር ማባዛት አይችሉም:: መባዛት ግን አላቃታቸውም፤ በጣም ጎበዝ ናቸው::

ዋው! ለካስ ማባዛት ማለት አንጎልን ይጠይቃል:: መባዛት ማለት ግን....!! ማባዛት ስሌት ሲሆን፤ መባዛት ግን ስሜት ብቻ ነው! የነዋሪ አሳዎች ቁጥር ሲበራከት፤ የሚዋለዱና የሚፈለፈሉ አሳዎች ይበዛሉ:: ይህም ተመልሶ የአሳዎቹ ቁጥር እንዲበራከት ያደርጋል :: የመራባት ምህዋር ነው::

ግን እስከ መቼ? በሌላ ገፅታው ሲታይስ? የአሳዎቹ ቁጥር እየበዛ ሲመጣ፤ የጋራ የአትክልት ማሳቸው መራቆቱ አይቀርም:: የአንዱ ከፍ ሲል፤ ሌላኛው ዝቅ! እየተመገበ ይባዛል፤ ምግቡን እያጠፋ::



የሁሉም አሳዎች የመራባት ችሎታ ቀላል ባይሆንም፤ የትንንሾቹ አሳዎች የመራባት ፍጥነት ግን ጉድ ያሰኛል፡፡ ለዚህም ነው፤ የትንንሾቹ አሳዎች ቁጥር ከትላልቆቹ የበለጠ ሲበዛ የሚታየው፡፡ ቢሆንም ግን የሁሉም ቁጥር እየጨመረ ነው፡፡ ነገር ግን፤ ይህንን አስተውሎ የተመለከተ አሳ አልነበረም፡፡

ሂሳብ ስላልተማሩ፤ ማባዛትም ስለማያውቁ፤ የህዝብ ብዛት ወዴት እያመራ እንደሆን ቀድመው ለመገመት በፍፁም አልቻሉም፡፡ የአትክልት ማሳዎቹ ደግሞ እየተራቆቱ ነው፡፡ «የቤተሰብ ምጣኔ» የሚባለውን ነገር እንዲያውቁ፤ ምናለ የህዝብ ቆጠራ ቢኖራቸው? የ100 ብር ደሞዝተኛ ሆኖ 10 ልጆችን እንሚወልድ ያገሬ ሰው ካልሆኑ በቀር!

ድሮ ድሮ፤ አሰላስሎ ማገናዘብ፤ በአሳማ ወስኖ መስራት፤ አምርቶ መብላት... ለየብቻ ተነጣጥለው የሚታዩ አልነበሩም፤ እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው - እውቀትን፤ በራስ መተማመንንና ልምድን የሚያዳብሩ፡፡

ዛሬ ግን፤ ብዙዎቹ አሳዎች፤ አንድ ነገር ብቻ (መብላት ብቻ) ነው በቁንፅል የሚታያቸው፤ «የቁንፅል አስረኛ» እንደሚባለው ሆነዋል፡፡ ሌላው ሌላው ሁሉ አይታያቸውም፤ እየሽመጠጡ መብላት ብቻ ሆኗል፡፡ ምግብ የጠፋ ጊዜስ?

የዓሳዎቹ የሕዝብ ብዛት በአስደንጋጭ ፍጥነት እየጨመረ ሄዷል፡፡ ነገር ግን፤ ማሳ ላይ የቀረው ምግብ ለዘላለም የማያልቅ ይመስል፤ መብላትና ማኘክ እንጂ፤ ለማምረት የሚያሰላስል፤ የሚወስንና የሚሰራ የለም፡፡ ወይስ፤ ዛሬውኑ፤ አሁኑኑ፤ ለዚህች ቅፅበት መብላታቸው ብቻ ነው የሚታያቸው? ከዚህ ውጭ አሻግረው አያዩም፡፡

እውነታውን ላለማየት ራሳቸውን «የቅፅበት እስረኛ» ቢያደርጉም፤ እውነታው ግን አፍጥጦ መምጣቱ አይቀርም። የተከፈቱ አፎችና ያገጠጡ ጥርሶች በዝተው፤ የአትክልት ማሳዎቹ ተራቆቱ። በአሳዎች ታሪክ ተሰምቶ የማይታወቅ፤ የምግብ እጥረት ተፈጠረ።

አንድ ችግር ሲፈጠር ሌሎች ችግሮችንም እየጎተተና እየተባባሰ አይደል የሚሄደው፣ ከምግብ እጥረቱ ጋር፤ ሌሎች አይቀሬ ችግሮች ተከሰተዋል። ምን-ምን አትሉም፣ በቃ... መጨቃጨቅ፤ መገፋፋጥ፤ መወነጃጀል፤ እርስ በርስ አለመተማመንና መጠራጠር በዛ። ለምን ብለን መጠየቅ ያስፈልገን ይሆን?

እኮ ለምን፣ አፍና ሆድ ከምግብ መብዛን እንደማይፈልጉት ሁሉ፤ አንጎልም ልክ እንደነሱ ለእውቀት፤ ለአላማና ለስራ ቢተጋ ምን አለበት? መብላትን ለብቻው በቁንፅል ባይነጥል ኖሮኮ... አሳዎቹ ለዚህ ሁሉ ደንታ አልነበራቸው፤ ጣጣ አያውቁም። ሸምጥጦ ማኘክ ብቻ!

ሆድ፤ ዛሬውኑ ከመቅፅበት ምግብ አምጡልኝ ማለቱ እንደማይቀር ሁሉ፤ «ነገ» የሚባለው ነገርም ከ24 ሰአት በኋላ፤ «ዛሬ» መባሉ አንደማይቀር ቢያገናዝብና የሩቅ አላማ ይዞ ለስራ ቢበረታ ምን አለበት? የዛሬ ቅፅበትን ለብቻ ባይነጥል ኖሮኮ... አሳዎቹ ለዚህ ሁሉ ጊዜ አልነበራቸውም። የተመናመነውን ተክል ቀድሞ ለመብላት ይራኮታሉ።

የአሳዎቹ ቁጥር፤ እጥፍ ድርብ እየሆነ ቀጥሏል፤ የትንንሾቹ አሳዎች ብዛት ግን ይበልጥ ያስደነግጣል። የቁሳር እያት፤ ይህንን በመመልከት፤ «ትንንሾቹ አሳዎች በዝተው ተባዝተው ከድርሻቸው በላይ ምግብ እየበሉ ነው» አለ - ትልልቅ አሳዎችን ሰብስቦ።

የበርጊ እያት ደግሞ ትንንሾቹን አሳዎች ጠርቶ፤ «ትላልቆቹ አሳዎች እያንዳንዳቸው ብዙ ምግብ ይጠቀማሉ» ብሎ ተናገረ።

በአንድ በኩል «ትንሽ»፣ በሌላ በኩል «ትልቁ» በሚል የተቧደኑ አሳዎች፣ አንዱ ሌላውን መወንጀልና ማውገዝ ጀመሩ። እናንተ ዳኛ ብትሆኑ ለማን ትፈርዱ ነበር? የሁለቱም ቡድኖች ንግግር ልክ ይመስላል። ታዲያ ችግሩ የማን ነው? «የጋራ» ምግብ፣ የፈጠረው «የጋራ» ችግር ይሆን?



አንዱ ቡድን ወቀሳ ሲሰነዝር፤ በምላሹ ሌላኛው ቡድን ውንጀላ ይወረውራል። ይህንንም ተከትሎ የመጀመሪያው ቡድን፤ በመረረ ውንጀላ በአፀፋ ይመልሳል። የመልስ መልስ፤ የአፀፋ አፀፋ እየተባባሉ መተጋተግ ነው።

በቡድን መተጋተግ!

ከዚህ ጊዜ በኋላ አሳዎቹ ደስተኛ ሊሆኑ አልቻሉም። ከስጋትና ከችግር ነፃ የነበረው የአሳዎች ኑሮ «በአንዴ» ተመሳቀለ። «በአንዴ» የተመሳቀለ ይመስላል እንጂ፤ ከቀን ቀን፤ ከሳምንት ሳምንት ችግር እየተባባሰና እየተበራከተ ቆይቶ ነው፤ ድንገት ገሃድ የወጣው። አሁን፤ አሳዎቹ ያለስጋት በፍቅርና በነፃነት መቀላቀል አቁመዋል። ልጆቻቸውም እንደድሮው አብረው እንዳይጫወቱ አድርገዋል። በቅርፅና በቀለም (በዘር) የተለየ አሳ ሲያጋጥማቸው፤ በጣም በመጥፎ አይን የሚመለከቱና የሚጠረጥሩ ሆነዋል - አሳዎች።

አይገርምም?! ቢተዋወቁም ባይተዋወቁም በዘር የተለየ ዓሣ ሲያጋጥማቸው ምንም ሆነ ምን፤ «ጠላታችን ነው» ወይም «የጠላት ወገን ነው» ይሉታል። በዘር የሚመሳሰል አሳ ሲያገኙ ደግሞ፤ ጥሩም ይሁን ክፉ፤ «ወዳጃችን ነው»፤ «የኛ ዘመድ ነው»፤ «የኛ ወገን ነው» ይሉታል።

በአሳዎች ዘንድ ያልነበረ አዲስ አስተሳሰብ ነው። ትንሽ ቆይቶ ልማድ ሆነባቸው። ቀጥሎም ባህል ሆኖ አረፈው። በመጨረሻም የተፈጥሮ ህግ እየመሰለ መጣ። እንዲያውም «ደም ከውሃ ይወፍራል» "Blood is thicker than water" የሚባል ተረት፤ የብዙዎች መፈክር ሆነ!!

የአሳዎች አይን ለምን ሁልጊዜ ወዲያና ወዲህ እንደሚንቀለቀል አያችሁ?





ከሚወዳት በርጊ ጋር በድብቅ እንኳ እንደልብ መገናኘት ያልቻለው ወጣቱ ቄሳር፤ ምርር ብሎታል፡፡ ደግሞም ዝም አላለም፡፡ መጠየቅና ምላሽ መስጠት የሚችልበት እድሜ ላይ በመድረሱ፤ እናቱን ጠየቃት፡፡ «ከበርጊ ጋር እንዳልጫወት ለምን አከለከላለሁ? ከ3 ቀን እድሜዬ ጀምሬኮ ነው፤ ከበርጊ ጋር ስጫወት ያደግኩት» ብሎ ጠየቀ።

እናትየው፤ «አንተ መጫወት የምትችለው ከዘሮችህ ጋር ብቻ ነው» ብላ መለሰችለት፡፡ የሰጠችው መልስ በጭራሽ እንዳላረካው ግን ውስጧ አውቋል፡፡

«እኮ ግን ለምን?» - እንደገና ጠየቀ ቄሳር፡፡

«እንግዲህ ነገርኩህ፡፡ የኛ ጎሳ እንደዚያ ወስኗል፡፡ የቃላላቆቹ ትእዛዝ ነው» አለችው፡፡

ይሄ ዊዝ (ጥበቡ - ጥቤ) ይባላል።



እስተዋይነት ስለሚያገናዝብ፤ አዋቂ ሆኗል፡፡ የወጠነውን አላማና የጀመረውን ስራ ስለማይለቅም የሙያ ልምድና በራስ የመተማመን መንፈስ አዳብሯል፡፡ ብቃት ይሉሃል እንዲህ ነው፡፡

ለነገሩማ ብቃትኮ እንዲህ በአያንዳንዱ ቀን ጥረት የሚገኝ እንጂ፤ በመኖር ብቻማ እርጅና እንጂ ብቃት (እውቀት፤ በራስ መተማመን፤ ልምድ) እንደማይገኝ ቢያንስ በሰዎች እናውቅም እንዴ?

የዊዝ ብልህ ስለሆነ፤ አሳዎች ችግር ሲገጥማቸው እንዲያግዛቸው ይጠይቁታል።

ዊዝ አሳዎችንና ማኅበረሰቡን በአጠቃላይ እንደራሱ ስለሚያይ፤ አሁን የተፈጠረው የምግብ እጥረት አሳስቦታል፡፡ በጭፍን «ትልቆ» እና «ትንሾ» በሚል እየተቧደኑ መናቆራቸውም አስጨንቆታል፡፡ በድሮ ዘመን፤ የአሳ ዘሮች በሰላም፤ በደስታና በብልፅግና ይኖሩ እንደነበር ከታሪክ መፃህፍት አንብቧል፡፡ ትምህርት ቢቆምም፤ በራሱ ጥረት ማንበብና መፃፍ ችሏል፡፡

«ሓሳ መሆንኮ ትልቅ ክብር ነው» ይላል ዘወትር - የቀድሞውን ስልጣኔ እያሰበ። አሁን ግን የምግብና የቡድን ጥላቻ ተፈጥሯል።

«ይህ መሆን የለበትም። አንዳቸውም መጎዳት የለባቸው። ሁኔታው የከፋ ደረጃ ከመድረሱ በፊት የሆነ ነገር ማድረግ አለብኝ» በማለት በጭንቀት ተነፈሰ - ዊዝ።

«ግን ምንድነው የማደርገው?»

«ግን ምን?»

መፍትሄ ይዘን መጥተናል የሚሉ የተወሰኑ አሳዎችን አይቷል። «አንድነትን እናጠንክር፤ በፍቅር እንዋደድ፤ በእኩልነት እንተሳሰብ» እያሉ ተናግረዋል። እውነትም፤ ለአንድ ለሁለት ቀን ትልልቆቹም ሆኑ ትንንሾቹ አሳዎች አብረው መዋል ይጀምራሉ።



ነገር ግን በተራቆተው የጋራ ማሳ ውስጥ ምግብ ፍለጋ ሲሻሙ፤ በጥቂት አሳዎች መካከል ፀብ ይነሳል። ብዙም ሳይቆይም የመቧደን ጥላቻው ያገረሻል - ለዚያውም ተባብሶ። ከሁለት ቀን በላይ ሊቆይ የማይችል የማስታገሻ መፍትሄ፤ ከሁነኛና ከመሰረታዊ መፍትሄ ጋር አብሮ ካልመጣ፤ ብዙም አይጠቅምም። እንዲያውም ያዘናጋል። ሁነኛና መሰረታዊ መፍትሄ የመፈለግ ሃላፊነትንና ጥረትን ገሸሽ የሚያደርግ ይሆናልና።

ዊዝ ሁነኛ መፍትሄ ይፈልጋል። በድሮ ጊዜ አሳዎች እንዴት በደስታና በብልፅግና

አሳዎቹ ይቅር ከተባባሉ በኋላ፣ ሲጋገሩ አመሹ:: ለመግባባት አላስቸገራቸውም:: በግላቸውና በህብረት ነገሮችን እያገናዘቡ፣ አላማዎቻቸውን ለማስከበርና ለማስረፅ የሚረጡ ይመስላሉ:: ወዲያው በስምምነት ወደ ስራ ገቡ:: ነገር ግን ለረጅም ጊዜ አልዘለቀላቸውም::

ከሁን በፊት በአስተዋይነት ብዙ እውቀት በማካበት፣ ነገሩ ሁሉ ውስብስብ ሆኖ ታያቸው:: በብርታት የስራ ልምድ ባላዳበሩ፣ ዕፀዋት መትከል ራሱ ከበድና አስቸጋሪ ሆነባቸው:: በዚያ ላይ የአየር ፀባይና በራስ የመተማመን መንፈስ በማጣት፤ ስራው አድካሚና አሰልቺ እየሆነ ትእግስታቸውን ተፈታተነው::

ዕፀዋት በደንብ በቅለው ምርት እንዲሰጡ፣ ከአፈርና ከውሃ በተጨማሪ የፀሃይ ብርሃንም እንደሚያስፈልጋቸው ዋዘ አስተምሯቸዋል:: ጥዋት ስራ ሲጀምሩ፣ የእለቱ ግባቸው፣ የፀሃይ ብርሃን ባለበት ግን ዕፀዋት ለመትከል ነበር:: አንዳንዶቹ ግን፣ እየረፈደ ሲመጣ ፀሃዩ መረረቻው:: ፀሃዩ አቃጠለን ብለው፣ ከመጀመሪያው ግባቸው ተሸራርተውና፣ ጥላ ፍለጋ ዋሻ ስር ሄደው መትከል ጀመሩ::



ዋሻ ውስጥ ተክለው እንደጨረሱ በደስታ ወደ ሰፈራቸው ሲመለሱ፣ ሌሎች አሳዎች በፀሃይና በሙቀት እየተጠበሱ ሲሰሩ አይተው፣ እየሳቁ አፌዙባቸው:: ቀለዱባቸው:: ፈንጠዝያቸውና ኩራታቸው ግን በአጭር ጊዜ ነው የተቀጨው::

በማግስቱ ሄደው ሲመለከቱ፣ ዋሻ ውስጥ የተከሉት ዕፀዋት ሁሉ በፀሃይ ብርሃን እጦት ጠውልጎ ረግፏል ::

በዘመቻ ተከሎቹን ሲጎትቱ ከዋሉ በኋላ፤ ተከሎቹ ሲታዩ... በእርግጥም ወዲያውኑ እድገው የረዘመ መስለዋል።

አሳዎቹ ዘዴያቸው ስለሰራላቸው በጣም ፈነደቁ።



ግን ብዙም ሳይቆይ ደስታቸው ደበዘዘ። ወደ ላይ የተጎተቱት ተከሎች፤ መጠውለግ ጀምረዋል።

በመጨረሻም ተከሎቹ ሞተውና በስብሰው አገኙአቸው፤ ፈጣን የአቋራጭ ሙከራቸው ከሸፈ።

አንዳንዶቹ አሳዎች ፀሃይ ላይ ላለመስራት ዋሻ ውስጥ መትከልን ሲመርጡ፤ ግሚሶቹም የተከሉት ዕፀዋት እንዲያድግ መንተትን መርጠዋል:: ውጤቱንም አይተነዋል:: የማያዛልቅ አቋራጭ ዘዴ፤ ለችግራቸው መፍትሄ አልሆነም::

ሌሎች አሳዎች ደግሞ እሱ - ለመስራት ያልሞከሩ:: በርትቶ መስራት ሞኝነት ሆኖ ስለተሰማቸው፤ ምግብ ፍለጋ በየቦታው መዞርን ተያይዘውታል:: አንግልቱ ብዙ ቢሆንም፤ የሚቀመስ ነገር አላጡም:: ያገኙትን ሁሉ እየበሉ የዛሬ ረሃባቸውን አስታግሰዋል፤ ዕፀዋት ሲተከሉ ለዋሉት አሳዎችም አዘኑላቸው::

በማግስቱ ግን....



በማግስቱ ግን፤ እነሱም ራሳቸው የሚታዘንላቸው ሆነው አደሩ:: ያገኙትን ነገር ሲበሉ የነበሩ አሳዎች በከባድ በሽታ ታመው በጣም ተጎዱ - የሞት ያህል::

ታውቃላችሁ? አሳዎችም ይታመማሉ:: እነዚህ የታመሙ አሳዎች ምን አይነት ምግብ እንደተመገቡ ማሰቡ እኔን ያስጠላኛል::

ዋሻ ውስጥ የተከሉ አሳዎች፤ ማሳ ላይ የተከሉትን የነቀሉ አሳዎች፤ የወዳደቁ ነገሮችን ሊመገቡ ተመርዘው የታመሙ አሳዎች ሁሉ፤ በደረሰባቸው ጉዳት (ራሳቸው በራሳቸው ላይ ባደረሱት ጉዳት) አዝነው አንገታቸውን እንደደፉ ነው ወደ ዊዝ የመጡት:: የየራሳቸውን ውድቀት ተናዘዙ:: ዊዝ በሁኔታው አዝና ራሱን ነቀነቀ::

አሳዎቹ ሁሉ በአስከሁት ጉዳት ተስፋ ሳይቆርጡ፤ በአስተዋይነት፤ በአላማ ፅናትና፤ በትጋት፤ እንደገና ዕፅዋት መትከል እንዲጀምሩ መከሯቸው - ዊዝ:: «ተክሎቹ በፍጥነት እንዲያድጉ ማዳበሪያ ጨምሩ» በማለትም፤ የማዳበሪያ አጠቃቀምን አስተማራቸው::



ብዙ አሳዎች፡ የዊዝን ምክር በመቀበል፡ ብዙ ማዳበሪያ ሰበሰቡ:: በታላቅ ተስፋም ማዳበሪያውን ወደ አፈሩ እየጨመሩ ዕፅዋት ተከሉ::

ማዳበሪያውን ከየት እንዳገኙት፤ እናንተ እንድታስቡት ልተውላችሁ::

## የአሳዎቹን ስራ የሚገልፅ ሪፖርት

በአንደኛው ቀን-----

ማዳበሪያ ጨመሩበት። ተክሎቹ በትክክል ከመብቀላቸዉም በላይ፣ ብዙዎቹ በሚደንቅ ሁኔታ ማደጋቸው ታየ።

በሁለተኛው ቀን——

ተጨማሪ ማዳበሪያ አፈሰሱበት። በተክሎቹ ላይም፣ በትክክል ይበልጥ ተጨባጭ ዕድገት ታየ።

ዊዝ ሲያስተምር እንደሰማነው፣ ተክሎቹ በፍጥነት እያደጉ ነው።

በሶስተኛው ቀን——

የተክሎቹን ዕድገት ይበልጥ ለማፋጠንና በአንዴ ለምግብነት እንዲደርሱ ለማድረግ፣ ማዳበሪያውን በሙሉ ሞጀሩበት። ጉድ ፈላ። ተክሎቹ በሙሉ ሞቱ። ለምን?

በትክክል ገምታችኋል። ለሁሉም ነገር ልክ አለው። ማርም ሲበዛ ይመርራል ይባል የለ? አሳዎቹ ያደረጉትም ይህንኑን ነው። ተክሎቹ በማዳበሪያ ብዛት ተመርዘው ተቃጥለዋል።

የምግብ እጥረቱ ስለተባባሰ አሳዎቹ በጣም ተርበዋል። ጭንቀታቸው ጨምሯል። ግራ መጋባትና አለመረጋጋት እየነገሰ ስለመጣ፣ አሳዎቹ ደህንነት አልተሰማቸውም። ስጋት ሰፍኗል።

አሳዎቹ፣ ራሳቸውን ለመጠበቅ በቡድንና በመንጋ መደራጀት ጀምረዋል፤ እርስ በርስ ለመጣበቅ። የተጣበቁት በሙጫ ሳይሆን፣ በአዲስ እምነትና በአዲስ አመለካከት ነው - «ከብዛትና ከመንጋ፣ ደህንነት ይገኛል» የሚል እምነትና አመለካከት።





እንዲያም ሆኖ፤ የሚቆርጣቸውን ርሃብ ለማስታገስ፤ ምግብ የሚያገኙበትን መንገድና ብልሃት መፈለግ አልቀረላቸውም። በየቦታው የተራረፈ ምግብ ሲገኝም፤ ሽሚያው አልተቻለም።

የተራረፈ ምግብ ለመብላት ሽሚያ፣ ትንቅንቅ፣




ትንንሾቹ አሳዎች በቀላሉ የሚረቱ አልሆኑም:: እነሱም እፀፋ ለመመለስ ተሰባሰበው፤ ጥምረት ፈጠሩ:: በግዙፍነቱና በጡንቻው ተመክቶ የነቀራቸውን አሳ ለይተው ባያውቁትም፤ ማንኛውንም ለመቅጣትና ለመበቀል ሲወሰኑ እንደሚሳካላቸው አልተጠራጠሩም፤ በብዛታቸው ተመክተዋል:: በእርግጥም ፈሪዎች አልነበሩ::

«የቡድን 99 ምክር ቤት» (G99) በሚል ስያሜ የሚታወቀው ቡደን የተቋቋመው የዚህ ጊዜ ነው:: የትንንሾቹን አሳዎች ደህንነት ለማስጠበቅና ስሜታቸውን ለማነሳሳት የተመሰረተው ይሄው ቡድን፤ አባላቱ ወዲያውኑ ተፈጻሚ የሚደርጓቸው የተግባር ዕቅዶችን በመዘርዘር ነው ስራ የጀመረው።

በእቅዱ መሰረት፤ መጀመሪያ በትላልቆቹ አሳዎች ላይ ስለላ ተካሄደ:: ትንንሾቹ አሳዎች ስለላውን ያካሄዱት፤ ጥንቃቄ በጎደለውና ሚስጥራዊ ባልሆነ መንገድ አይደለም:: በእቅድ ነው::

ከዚያም፤ የጥቃት እቅድ አዘጋጅተው በድብቅ ተሰማሩ - ያጠረቃቀሙትን ምግብ ይዘው:: ሊበሉት አይደለም፤ ትልልቆቹን አሳዎች በምግብ ለማታለል እንጂ:: ምን እንደተደገሰላቸው ያልጠረጠሩ አንዳንድ ትልልቅ አሳዎች ምግብ ያገኙ እየመሰላቸው በተናጠልና በየተራ ወጥመድ ውስጥ ገቡላቸው::

ትንንሾቹ አሳዎች ወጥመድ ውስጥ የገባው ትልቅ አሳ ላይ ተረባርበው በመስፈር እየተጨፈጨፉ ከየአቅጣጫው ይቦጫጭቁታል:: አሳው ትልቅ መሆኑ ብቻ በቂ ነው፤ ፀባዩ ጥሩም ይሁን መጥፎ ልዩነት የለውም:: ጠላት ነው:: እንደኛውን ገድለው ሲጨርሱ፤ እንደገና ሌላ ትልቅ አሳ ወጥመድ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ተረባርበው እየነከሱ ይገድሉታል::



ገደሏቸው!?

ወሬው በአጭር ጊዜ አገር ባህሩን አዳረሰው:: ወሬውን የሰሙ ትልልቅ አሳዎች፤ ስጋት አደረባቸው:: «ወንጀሉን የፈፀሙት እነማን ናቸው» ብለው ለማጣራት አልሞከሩም:: በአጠቃላይ፤ ትንንሽ አሳዎች ላይ ቁጣቸው ነደደ:: ከእንግዲህ ከንፋቸውን አጣጥፈው እንደማይቀመጡ ዝተዋል::

«ትንንሾቹ አሳዎች እንዲህ ሲያሸብሩን በዝምታ አናልፍም፤ በሽብር ጥቃት እየሰጋን አንኖርም» አሉ በርካታ ትልልቅ አሳዎች፡፡ «ትናንሾቹ አሳዎች ደም መቃባትና ደም መፋሰስ ከፈለጉ ያገኟታል!» አለ የቁሳር ኢያት፤ «ይሄ ጦርነት ነው!»

መጀመሪያ ላይ፤ አንዳንድ ትልልቅ አሳዎች፤ ምግብ ለመቀማት ትንንሾቹን ያስፈራሯቸውና ያሳድዷቸው ነበር፡፡ በአፀፋው ፀ99ን የመሰረቱ ትንንሽ አሳዎች፤ በሽምቅና በድብቅ ማንኛውንም ትልቅ አሳ እያጠቁ መግደል ጀመሩ፡፡

በዚህ የተቆጡ ትልልቅ አሳዎች፤ በማስፈራራትና በማሳደድ ብቻ የሚመለሱ አልሆኑም፡፡ ትንንሾቹን ለመብላት ዘመቱ፡፡ የመልስ መልስ፤ የአፀፋ አፀፋ... እያለ፤ ተቀጣጠለ፡፡



በትልልቆቹ አሳዎች ዘመቻ፤ ብዙ ሺ ትናንሽ አሳዎች ሰለባ ሆነዋል፡፡ ትንንሽ አሳዎች፤ አስቸጋሪና ትልቅ ጠላት ነው የገጠማቸው፡፡

ትልልቆቹ አሳዎች ዘመቻቸውን አላቋረጡም፡፡ እየሄዱ... ትንንሾቹን ዋጥ ነው፡፡/ ትንንሾቹን እየዋጡ፤ ጡንቻቸው እያበጠ መጥቷል፤ ታዲያ ትንንሾቹ በባዶ ሆዳቸው እንዴት ይቻሏቸው?

የመበላላት ምህዋር ውስጥ፤ ስኬት ማለት እንዲህ ነው፡፡ በአንዱ ኪሳራ ብቻ ነው፤ ሌላኛው የሚሳካለት፡፡

ኦርMAP

ዊዝ፤ የባህር ውስጥ ህይወት እንዲህ መተራመሱ ግራ አጋብቶታል፡፡ ለጊዜው ማድረግ የቻለው ስለሁኔታው መፈላሰፍ ብቻ ነው - «ትልቁ አሳ ትንሹን አሳ የሚበላው ከሆነ፤ ትንሹ ዓሳም ጥቃቅን ትላትሎችን መብላት ይጀምራል»



በእርግጥም ዊዝ የገመተው ነገር መሆኑ አልቀረም፡፡ ይሄው ባህር ውስጥ፤ የመበላላት ተግባር እስከ ዛሬ ጸንቶ አናያለን፡፡

ቁሳርና በርጊ ከጓደኞቻቸው ጋር፤ የራሳቸው የሆነ ፍልስፍና ነበራቸው፡፡

«ምንም ይሁን ምን፤ እኛ እውሬ አንሆንም፡፡ እርስ በርስ እንጣበቃለን፡፡ ከዚህ ከፉ ዘመን ለመውጣት አንድ ላይ እንሆናለን» ብለዋል፡፡

አንድነታቸውን ለማረጋገጥም ዋሻ ውስጥ በሚስጥር እየተገናኙ ይነጋገራሉ፡፡

እኛ ሰዎች፤ ከእነዚህ ወጣት አሳዎች፤ አንድ ወይም ሁለት ነገር መማር እንችላለን፡፡



ወጣቶቹ አሳዎች ዋሻ ውስጥ ተገናኝተው እየተነጋገሩ ኢያሉ! ቁሳር ድንገት ሆዱ ተገላበጠበት:: ሆዱ ሲያጉረመርምና ሲጮህ ጓደኞቹ ሰምተው ሳቁበት:: የእነርሱም ሆድ በጣም እየተገላበጠ ነው:: ሁሉም ርቧቸዋል:: ነገር ግን የትንንሾቹ አሳዎች ሆድ ሲጮህ ያን ያህል ጮኾ አይሰማም:: ረሃባቸውን ለመርሳት ይሳሳቃሉ::

ቁሳር በርጊን በፈገግታ አያት:: በፈገግታ አየችው:: አፍጥጦ አያት::

ለማመን ያስቸግራል! ያቺ የሚወዳት በርገር፤ ቆንጆየዋ በርጊ፤ አፍጥጦ እያያት...

እዚያው እያያት... አፍንጫው ስር በሚገርም ሁኔታ ወደ ‹‹አሳ በርገር››ነት ተለወጠችበት::





ቁሳር ከመቅፅበት ተወነጨፈ::

ምን እንደሆነ ሳያውቅ፤ ምን እያደረገ መሆኑንም ለማወቅ ጊዜ ሳይሰጥ፤ አፍንጫው ስር ያገኘውን «ሐሳ በርገር»፣ እንዳለ ወደ አፉ ከትቶ ዋጠው::

ዋጥ!

በጣም ርቦት ነበር:: ማንስ ሊፈርድበት ይችላል?

የቁሳር ጓደኛ የነበሩ ሌሎች ትንንሽ አሳዎች በመብረቅ ፍጥነት እዚያው ጨለማና ቀዝቃዛ ዋሻ ውስጥ ለብቻው ጥለውት ተፈተለኩ:: ቁሳር በጓደኞቹ አዘነ::

«ቢቃ፤ የአሳ በርገር ስላላካፈልኳቸው ሸሹኝ:: ጓደኞቼ ሸሹኝ:: ሌሎቹስ እሺ፤ በርጊም እኔን ጥላ ሄደች?!» አለ ቁሳር::

ሚስኪን በርጊ:: ምን አይነት ወዳጅ ነው የገጠማት!



ባሆኑ ምንኛ ግራ የሚያጋባ አለም ሆኗል! በእንዲህ
አይነት ታሪክ ነው፤ ዛሬ በአሳዎቹ መካከል
መከፋፈልና መበላላት የሰፈነው።

በዚህም ነው፤ ዛሬም ድረስ አሳዎች ፀባያቸው
እንዲያ ሆኖ የቀጠለው።



ከዚህ ምን እንማር ይሆን?

# ክፍል 2

# ስኬታማ መንገድ

## የተሟላ አስተሳሰብ ፡ ለውጤታማ ሃሳቦችና ለውጤታማ ተግባሮች

ስኬት፤ የሆነ ቦታ ላይ ደርሶ የሚቆምና የሚደነዝዝ አይደለም፤ እየተነቃቃና እየጨመረ የሚቀጥል እንጂ። የስኬት ምህዋር እንለዋለን - በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወት።

የስኬት ሞተራችን፤ ሌላ ሳይሆን አእምሯችን ነው። መሪያችን ሌላ ሳይሆን፤ አእምሯችን በመጠቀም የምናሰላው የራሳችን ሃሳብ ነው። እንቅስቃሴያችን ሌላ ሳይሆን፤ የራሳችን ስራና ጥረት ነው።

በአጭሩ፤ "ማሰብ" እና "መስራት"! ወይም "እያሰቡ መስራት"!

አእምሯችንን በአግባቡ በመጠቀም ለማሰብ ግን፤ ትክክለኛ አስተሳሰብ ሊኖረን ይገባል። በየአገሩ የምናያቸው አስገራሚ የስልጣኔ ብልፅግናዎችና አስደናቂ የስኬት ህይወቶች፤ ከትክክለኛ አስተሳሰብ የሚመነጩ ናቸው።

ስኬትን የሚያስገኝ ተአምር የለም። ትክክለኛ አስተሳሰብ ግን "ተአምር!" የሚያሰኙ ስኬቶችን ያቀዳጀናል።

እንደየዝንባሌያችን በምናፈቅረው የኑሮ መስክ ሁሉ፤ በተግባር የምንሰራባቸው ስኬታማ ሃሳቦች እንዲኖሩን እንፈልጋለን?

እንግዲያውስ፤ ትክክለኛ አስተሳሰብ እንቅረፅ - አእምሯችን በአግባቡ እንዲሰራ የሚያደርግ "ስኬታማ የህይወት ሶፍትዌር"! ሲስተምስ ቴንኪንግ (ቅንብራዊ አስተሳሰብ) በሚል ስያሜ እንተዋወቀው። ይህን ስኬታማ አስተሳሰብ ለመንናፀፍ፤ መንገዱ ብሩህ ነው - ህጎቹ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው - በጣም ቀላልና ግልፅ።

የሚበለፅግ አስደሳች የህይወት ምህዋር፤ በእጅህ ነው! በእጅሽ ነው!

# ህይወትህ በእጅህ ነው

# መንገዱም ከፊትህ ነው

ስላለፈው ታሪክና ስላለፈው የኑሮ ዘመን አንዳንዴ እናወራ ይሆናል። ዋናው ትኩረታችን ግን የዛሬውና የወደፊቱ ህይወታችን ነው። ዛሬ ምን እናድርግ፤ ህይወታችን የብልፅግናና የደስታ እንዲሆን ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው? ይሄ ነው ዋናው ቁም ነገር።

አዎ፤ ያለፉት ጥረቶችና ስኬቶች ያኮራሉ፤ ግን ህይወትን በትዝታ መተካት የለብንም። ያለፉት ስህተቶችና ውድቀቶች ያስቆጫሉ፤ ግን ለወቀሳና ህይወትን በቁዘማ ለመተካት መሆን የለበትም። የትናንት ጥረቶችና ስኬቶች፤ ለዛሬ የብቃት መሰረትና የመንፈስ ብርታት እናድርጋቸው። ለምን? የትናንት ስህተቶችና ውድቀቶችም፤ ለዛሬ የብቃት ትምህርትና የመነሳሳት ቁጭት እናድርጋቸው። ለምን? የሁለቱም ጥያቄዎች መልስ አንድ ነው - በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወትን ለመቀዳጀት።

እውኑ ተፈጥሮ (reality)፤ በራሱ ጊዜ እውቀት ወይም አላማ አይሆንልንም - አእምሮአችንን ተጠቅመን ካልመረመርነውና ካላመዛዘነው በቀር። በራሱ ጊዜ ምግብ፣ መኪና፣ ቤት፣ መብራት፣ ቴሌፎን አይሆንልንም - አእምሮአችንን ተጠቅመን ካልጣርንበትና ካልሰራንበት በቀር።

እውኑን ተፈጥሮ በስሌት እንዲያውቁትና እንዲሰሩበት አእምሮአቸውን መጠቀም ትተው፣ "መሰለኝ ደስ አለኝ" ወይም "መሰለኝ ቅር አለኝ" በሚል ጭፍን ስሜት መነዳት የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። እውኑ ተፈጥሮ (reality)፤ በራሱ ጊዜ እውቀትና ምግብ አይሆንላቸውም። ውድቀታቸው ሲታይ፤ "እውኑ ተፈጥሮ የእጃቸውን ሰጣቸው" ማለት ይቻላል - እጃቸው ስራ ስለፈታ። "የአንጎላቸውን ቅጣት ሰጣቸው" ቢባል ደግሞ በጣም ትክክል ይሆናል - አንጎላቸው ነዋ ስራ የፈታው። ታዲያ እውኑ ተፈጥሮ፤ እጅግ ፍትሀዊ ዳኛ አይደለም?

አእምሮአቸውን ተጠቅመው መማር፣ ማወቅና ማሰብ ለሚፈልጉ፤ አላማ መያዝ፣ ግብ መጨበጥና በፅናት መወሰንን ለሚመርጡ፣ በተግባር መጣር፣ መስራትና መትጋት ለሚሹ ሰዎች ደግሞ፤ እውኑ ተፈጥሮ ወለል ብሎ የተከፈተ የስኬት ጎዳና ነው።

በእውነ ተፈጥሮ ላይ የተመሰረተው ጥንቅራዊ አስተሳሰብ (ST)፤ ውድቀትን ለማስወገድና ስኬትን ለመቀዳጀት የሚያስችሉ መሳሪያዎችን የሚያስታጥቀንም በዚሁ ምክንያት ነው።

መሳሪያዎቹን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመልከት ይበልጥ ከራሳችን ጋር ልናዋህዳቸውና ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ለዚህም ነው፤ በጥናት የተደረሰባቸው ❘❘ የST ህጎችን በአጭሩ እንደ መነሻ የምናቀርብላችሁ - በአሳዎቹ ታሪክና ከተጨባጭ ኑሮአችን ጋር እያያዝን። በዚህ መነሻነትም ወደ ቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST) መሰረታዊ ምንነት እንሻገርና፤ እንራቀቅበታለን።

ነገር ግን ዋጋ መቀነስ ላይ ብቻ ካተኮርን፤ የጥራት ደረጃው ይወርድብንና ገር እናጣለን። እየደጋገሙ ዋጋ መቀነስ መፍትሄ አይሆንም - ከግንብ ጋር እንደመጋጨት ነውና። በቅናሽ ዋጋና በተሻለ የጥራት ደረጃ ምርት ማቅረብ የሚያስችል መፍትሄ መፈለግ ይኖርብናል።

ከሲስተሙ ፈርጆች መካከል አንዱ እንኳ፤ የገደብ ልኩ ሲዛባ፤ እድገትን ይገድባል። ሌሎች ፈርጆች ሲንቀሳቀሱ፤ አንዱ ፈርጅ ተዛብቶ ከተቸከለ ታኮ ሆኖ እድገትን ይገታል። ከታች ቀርቶ እድገትን ቁልቁል ይጎትታል። ሌሎቹን ፈርጆች ስናጠናክር ብንከርም ዋጋ የለውም። ታኮ ሆኖ የገደበንን ነገር በማስተካከል ነው እድገትን የምናስቀጥለው።

እንዳንዴም አንዱ ለብቻው እየሸመጠጠ ሌሎቹን ያቀጭጫል ወይም ከላይ ተከማችቶ እድገትን ወደ ታች ይጫናል። የዚህን ጊዜ፤ እንደገና ያንኑ መግፋትና መታገል ሳይሆን፤ ሲስተሙ ላይ ሸክም የሆነውን ነገር ዞር ማድረግና ሌሎቹን ፈርጆች ማጠናከር!

ኤችአይቪን ለመከላከል ከሚያስፈልጉ የጥረት ፈርጆች መካከል አንዱ ላይ ብቻ በቁንፅል ትኩረት ሲደረግ ነበር - የመረጃ አቅርቦት (ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት) በሚል። በዚሁ መንገድ የተወሰነ ያህል አወንታዊ የእድገት ለውጥ የታየ ቢሆንም፤ የለውጥ እድገቱ ቆሟል።

ገዳቢ ምህዋር ውስጥ ገብቷል። ያንኑ ትምህርት እየደጋገሙ መውቀጥ እያቀጣም። እየተጃጨ ነጥር እንደመመለስ ይሆናል። ገትሮ እድገትን የገደበው ሃይል ምን እንደሆነ ተረድተን የቀመርነው የማኅበረሰብ ወይይትና ተግባራዊ ምላሽ ፕሮግራም (community conversation)፤ በተጨባጭ የእድገት ለውጥ ያስመዘገበው በST ታግዞ ነው።

# 3. ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ፤ ስኬት ሲመጣ እየተፈታተነ

## Behavior grows better before it grows worse and vise versa

ጉድና ጅራት ከወደኋላ ነው ይባላል። ውድቀት ያታልላል - በተለምዶ ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው እንደሚባለው፡፡ ስኬት ደግሞ፤ በቅድሚያ ዋጋ ያስከፍላል - ከድል በፊት ግብግቡ ያስጨንቅ የለ?

አንዱን ፊርጅ ብቻ በቁንፅል የሚያይ፣ የዛሬዋን ቅፅበት ብቻ የሚመለከት፤ በቁንፅሉና በቅፅበቱ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ተግባር፤ መጀመሪያ ላይ ውጤቱ ሲታይ ስኬታማና አትራፊ ይመስላል። ስለሚመስልም በፍጥነት ድጋፎችን፤ በብዛት ተከታዮችን ያፈራል። አድሮ ውሉ ግን ውድቀት ይከተላል፡፡

አሳዎቹ የጋራ ማሳ አቋቁመው፤ ሁሉም እንዳሻው እየገባ ይበላል፤ እንዳሰኘው እየተጋባ ይባዛል፤ ምግብ ለማምረት ማሰብና መስራት የለም። ቀኑን ሙሉ አብሮ መብላትና እየተሳሳቁ መቦዘን ለጊዜው ህይወት እያበበች ይመስል ነበር። ከርሞ ጉድ ፈላ እንጂ - ርሃብና መበላላት።

በተቃራኒው፤ ዘላቂና ጠቃሚ ሲስተሞች፤ መጀመሪያ ላይ ህይወትን እየጎሸሙ አከሳሪ ይመስላሉ። አሳዎቹ ለምርት ስራ ሲነሱ እንዴት ህይወት እንደጨለመባቸው አስቡ። በኑሮ የተቸገረ ሰው ህይወቱን ለማሻሻል ሲወስን፤ ለኢንቨስትመንት ገንዘብ መቆጠብና ለብቃት ግንባታ ገንዘብ ማውጣት ይኖርበታል። በዚህም የእለት ኑሮው ይበልጥ ይቆጠቁጠዋል፤ ቤተሰብ ቅሬታ ያሰማል፤ የመጠጥ ጓደኞች ይሸሹታል።

ጠቃሚ ሲስተሞች ከአጀማመራቸው ያስጨንቃሉ። ተቃውሞም ይበዛባቸዋል። በፅናት ታግሰን ካለፍናቸው ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ አስደሳች ይሆናሉ፡፡

ሁሉም ወንጀሎች፣ ሱሶች፣ ስንፍናዎች ወዘተ ሲጀምሩ አስደሳችና ጠቃሚ ቢመስሉም፤ ሲጠናቀቁ ዘግናኝ ናቸው፡፡ ሁሉም የስኬት ታሪኮች ደግሞ ሲጀምሩ፤ የሚያጨናንቁና የሚያጎሳቁሉ ቢመስሉም፤ ሲጠናቀቁ አስደሳች ናቸው።

# 4. “ቀላል” የማምለጫ መንገዶች፣ ወደነበርንበት ይመልሱናል

## The easy way out usually leads back in

የፈሩት ይደርሳል እንደሚባለው ነው። "ቀላል" የማምለጫ መንገዶች፣ መልሰው ወደነበርንበት ይወስዱናል። "ቀላል ማምለጫ" በቀላሉ ውጤት አያስገኝም። ነገሮችን ማካበድም፤ ከባድ ውጤትን አያስገኝም።

ለሁሉም ጠቃሚ ግብ፤ ተስማሚ የሆነ ተገቢና ውጤታማ መንገድ ያስፈልገዋል። የሚነጣጠሉ አይደሉም። አንዳንድ ሰዎች ግን፤ ውጤታማ ባልሆነ መንገድ ሲለፉና ሲደከሙ በመዋላቸው ብቻ ትርፍ የሚያገኙ ይመስላቸዋል፤ ግን ኪሳራ ነው። ድካምዎን ቆጥሮ እያዘነልዎት በራሱ ጊዜ "ልሳካ" የሚል ግብ የለም። ስለዚህ፤ ውጤታማ መንገድ መምረጥ ያንተና ያንቺ ኃላፊነት ነው። ድካምና ልፋት ብቻውን በቁንፅል ሳይሆን ከግብ ስኬት ጋር በትስስር መታየት አለበት።

ሰካራሙ ሰውዬ፣ በእኩለ ሌሊት አስፋልት መሃል ላይ አጎንብሶ ፍለጋ ጀምሯል። ምንድነው ሲሉት፤ "የቤቴን ቁልፍ ጥዬ ነው አፋልጉኝ" ይላል። አስፋልቱ ላይ ግን ቁልፍ የለም። “አስታውስ! ቁልፉን ሌላ ቦታ ጥለህ እንዳይሆን” አሉት። ሰካራሙም ድቅድቅ ወዳለው ጭለማ እየጠቆመ፤ “እዚያ ጨለማ ውስጥ ወድቄ ነበር፤ መብራት ያለው እዚህ ስለሆነ ነው እዚህ የምፈልገው” አላቸው።

ተገቢ ባልሆነ መንገድ በአቋራጭ በቀላሉ ያለ ጥረት ግባቸውን የሚያሳኩ ይመስላቸዋል - አንዳንድ ሰዎች። አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ እንደሚባለው ነው። አቋራጩን መንገድ የሚመርጡት ቀላል ሆኖ ስለሚታያቸው እንጂ፤ ውጤታማነቱንና ተገቢነቱን አመዛዝነው አይደለም። ግን፤ እንደቀልድ ያለፍነው ነገር በሙሉ ተመልሶ መምጣቱ አይቀርም።

የተሰነጠቀውን ወይም የተዛባውን ነገር በተገቢው መንገድ ሳያስተካከሉ ሸፋፍኖ “መጠገን”፤ ቀላል የማምለጫ ዘዴ ሊመስል ይችላል። ግን እንደገና ይሰበርና ችግሩ ተመልሶ ይመጣል። በምግብ እጥረት የተቸገሩ አሳዎቹ ፀሐይ ላይ ከመስራት ይልቅ በየዋሻው እፅዋት መትከልን በመምረጣቸው፤ ምን ውጤት እንዳገኙ አይታችኋል። ለምን ዋሻ ውስጥ እንደተከሉ ብትጠይቋቸው፤ መልሳቸው “ስለቀለለን”፤ “መስለን ደስ አለን” የሚል ይሆናል። ተመልሰው እዚያው የምግብ ችግር ውስጥ ገብተዋል።

# 5. “መድሀኒቱ” ከበሽታው ሊከፋ ይችላል
## “The cure” can be worse than the disease

ማንኛውም ችግር (በሽታ) ሲያጋጥመን፣ ታቅፈነው መቀመጥ የለብንም። ከመባባሱ በፊት፣ መፍትሄ (መድሃኒት) ልናበጅለት ይገባል። ነገር ግን፤ በእውነታ ላይ ያልተመሰረቱ መፍትሄዎች (መድሃኒቶች)፤ ልናስወግድ ከምንፈልገው ችግር (በሽታ) የባሱ ሊሆኑ ይችላሉ።

በአሳዎቹ ታሪክ ውስጥ፤ የምግብ እጥረትና ረሃብ ሲከሰት፤ ዊዝ ምን አይነት መፍትሄ ይዞ እንደመጣ አስታውሱ። ብቻውን እያመረተ ሁሉንም አሳዎች ለመመገብ ሞክሯል (እርዳታ ለማከፋፈል)። የማታ ማታ ግን አላማረም። የዊዝ መፍትሄ፤ አሳዎችን ለምርታማነት አላነሳሳም። እንዲያውም አሳዎች ለችግራቸው የምርታማነት መፍትሄ እንዳይፈልጉ፣ የሕይወት ክህሎታቸውን እንዳያሳድጉ የሚያዘናጋ ሆኗል - የዊዝ መፍትሄ።

በቁንፅሊና በቅፅበቴ አስተሳሰብ እየተመራን፤ ... ማለትም እንዱን ፈርጅ ብቻ በቁንፅል እያየን፣ የዛሬዋን ቅፅበት ብቻ እየተመለከትን የምንጓዝ ከሆነ፤ ችግሮችን እናባብሳለን። ረሃብ ሲያስቸግረን እርዳታ ማከፋፈልን ብቻ የምናይ ከሆነ፤ ለጊዜው ጥሩ ቢመስልም፤ ሰዎች ራዕይ እንዲኖራቸውና የሕይወት ክህሎት እንዲያዳብሩ ስለማያደርግ (ጨርሶም ስለሚያጠፋ) ከበሽታው የባሰ የረዥም ጊዜ ችግር ይወልዳል - ጠባቂነትን!!

ሰዎች ጭንቀትን ለመቀነስ ብለው የሚጀምሩት የመጠጥ ሱስ፤ በመጨረሻ ከጭንቀታቸው የባሰ ሌላ በሽታ ይሆናል። ተማሪ እንዳይወድቅ ማስኮረጅ፤ ሌባው ታስሮ ቤተሰብ እንዳይቸገር በዝምታ ማለፍ፤ የተቸገሩ ሰዎችን ለመርዳት የሌሎችን ሃላፊነት መሸከም፤ ከበሽታው የከፉ መድሀኒቶች ናቸው። የችግሮች ዘላቂ መድሃኒት፤ የህይወት ክህሎት ነው።

አብዛኞቹ የኑሮአችን ችግሮች የሚመነጩት፤ ይህንን ህግ ካለመረዳት ነው። የትምህርት ውጤት ከአመት አመት በትጋት ከሚዳብር እውቀት የሚመነጭ ነው። ኢንቨስትመንት፤ ለበርካታ አመት በታታሪነት እያመረቱ ከመቆጠብ የሚገኝ ውጤት ነው። የኦሎምፒክ ሜዳሊያ ለብዙ አመታት በልምምድና በጥረት ከገነቡት ብቃት የሚወለድ ነው። ብልፅግናና ዝና፣ ፍቅርና ደስታ ... ሁሉም ትልልቅ ስኬቶች፤ መንስኤያቸው የረጅም ጊዜ ትጋትና ፅናት ነው። በዚህ ህግ መሰረት የትም ይሁን መቼም፤ የዘራነውን እናጭዳለን፤

ማሳውና ጎተራው ሊራራቅ ይችላል። በመዝራትና በማጨድ መሃልም፤ ጊዜ አለ። የዘራነው እህል ለአዝመራ እስኪደርስ ወራትን ይፈጃል። በወራት ውስጥ የማይደርስ ምርትም አለ - የአመታት ጥረትን የሚጠይቅ።

እያንዳንዷን ግንዛቤ ጨብጠን ስንዘራ ነው በአእምሮአችን የእውቀት አዝመራ የምናገኘው። ሀልውናን የማለምለም ግብ ይዘን አእምሮአችንን እየተጠቀምን፤ ጥረትን በትጋት ስንዘራ ነው፤ ከአመት አመት የሚጨምር አዝመራ የምናገኘው - የሕይወት ከህሎትን። የህይወት ክህሎትን ዘርተንም፤ የማያቋርጥ ምርት እናገኛለን - አስደሳች ሕይወትን።

በግንዛቤ ፋንታ ጭፍን ስሜትን፣ በጥረት ምትክ ስንፍናን፣ በክህሎት ቦታ አቅመቢስነትን የምንዘራ ከሆነም፤ አረም እንታቀፋለን - አስቀያሚ ህይወት። በቆሎ ዘርቶ የሚታጨደው በቆሎ ነው። ከፋት፣ የዘር ጥላቻ ወዘተ የዘራም ያንኑ ያጭዳል - በጣም አብዝቶ። ግን ወዲያውና እዚያችው ቦታ ላይ ላይሆን ይችላል።፡

# 8. ቀላል መፍትሄ ይኖራል፤ ነገር ግን በቀላሉ አይገኝም
## Small changes can bring big results; but they are the least obvious

ለከባድ ችግር "ቀላል" መፍትሄ፤ ለትልቅ ስኬትም "ቀላል" የለውጥ መንገድ ሊኖረው ይችላል። ግን ቀላል መፍትሄና ቀላል መንገድ በፍጹም በቀላሉ አይገኙም። Small changes can produce big results; but the areas of highest leverage are the least obvious.

ይሄ ለአሳዎቹ ምን ማለት ነው? መማርንና ማምረትን አርግፍ አድርጎ የተወ ማህበረሰብ ውስጥ፤ በዚሁ መንስኤ ከተወሰኑ አመታት በኋላ ከባድ ጥፋት እንደሚፈጠር ግልፅ ነው። መንስኤውና መዘዙ በጊዜ ሊራራቁ ይችላሉና። አጥብበን ደግሞ እንየው።

በዚሁ ደካማ ማህበረሰብ ውስጥ፤ የተራረፈ ምግብ ለማግኘት ሽሚያ ይፈጠራል። ለሽሚያውም፤ ጎራ ለይተው የሚቧደኑ መኖራቸው አይቀርም። የቡድን ጥላቻ ይስፋፋል።

ከዚያ በኋላ ከአለታት አንድ ቀን፣ በአንዲት ትንሽ መንስኤ፣ ወይም በጥቃቅን ትንኮሳና ፀብ መንስኤነት ታላቅ የጦርነት ጥፋት ይከሰታል። ሰበቧ ትንሽ ነች። ግን፤ ቤንዚን ከታርከፈከፈ በኋላ፣ አንዲት የክብሪት ብልጭታ በቂ ነች።

ለጅግ ስኬታማ የሳይንስ ግኝቶች፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችና የቢዝነስ ሃሳቦችም፣ ታሪካቸውን ስንሰማ ብዙውን ጊዜ ከጥቃቅን መንስኤዎች ጋር ተያይዘው የምናገኛቸው አለምክንያት አይደለም። ነገር ግን፤ ለአመታት እውቀት፣ ሙያና ክህሎት አዳብረው፤ ሁልጊዜ በትኩረት አእምሯቸውን ስለሚጠቀሙ ነው፤ ለስኬት ዝግጁ ሆነው የተገኙት።

የአርኪሜድስ ገላውን ለመታጠብ ወደ ገንዳው ሲገባ፤ በገዳው ውስጥ የነበረው ውሃ ወደ ላይ ከፍ ሲል አየ። በዚህም ታላቅ የፊዚክስ ግኝት ብልጭ ብሎለት "ዩሬካ፣ ዩሬካ" እያለ እርቃኑን እንደሮጠ በታሪክ ይነገራል። ግኝቱ የዲስፕሌስመንት ህግ ይባላል። በትንሽ መንስኤ ትልቅ ውጤት! ግንኮ፤ ማናችንም ብንሆን፣ ገንዳ ውስጥ በመግባት ውሃው ከፍ ሲል ማየት እንችላለን። እና የዲስፕሌስመንት ህግ ብልጭ ይልልናል?

እየተገበርን። ይሄ የምታነብቡት የጥንቅራዊ አስተሳሰብ (ST) መፅሃፍ፤ በዚህ በኩል በእጃችሁ እንደሚጠቅማችሁ እንተማመናለን።

የተለመደውን እየሰሩ ማግኘት የሚቻለው ያንኑ የተለመደውን የድሮውን ውጤት ነው፡፡ በቀላሉ ባይታዩንም፤አንጎላችንን ከተጠቀምን በርካታ ቀላል መፍትሄዎች ሞልተዋል።

ለምሳሌ ለኤችአይቪ መከላከል ስራ ከሚጠቀሱትና በተለምዶ ሶስቱ "መ" ከሚባሉት ዋነኛው "መጠቀም" ነው፡፡ በሲስተምስ ቲንኪንግ "መጠቀም" ሲባል፤ "ኮንዶም መጠቀም" ለማለት እንዳይመስላችሁ። ሲያስፈልግ ተጠቀሙበት። ዋናው ግን፤ "አንጎልን መጠቀም" ነው። አእምሮ ሲሰራ... ያኔ የማይቻል ነገር የለም።

# 9. ኬኩን በልቶ ባለ ኬክ መሆን ይቻላል፤ ነገር ግን በአንድ ጊዜ አይደለም

## You can have your cake and eat it too; but not at once

ልታርፍም ልትሰራም ትችላለህ፤ ግን በአንድ ግዜ አይደለም። ወይ ከስራ ዉጪ ከዕረፍት ምረጥ አይባልም፤ ሁለቱንም አመጣጥኖ ማሳካት ይቻላል። ልብስ ለመግዛት ስትወስኑ፤ በአጣብቂኝ ጥያቄ ልትቸገሩ ትችላላችሁ። ወጪ የሚቆጥብ ልብስ በ300 ብር ልግዛ ወይስ ጥራት ያለው ጥሩ ልብስ በ600 ብር ልግዛ? ዛሬውኑ፤ ሁለቱንም አማራጮች መፈፀም አይቻልም።

ወንድሜ በላከልኝ ገንዘብ አሜሪካን ለመጎብኘት ልሂድ? ወይስ ገንዘቡን ቆጥቤ ትንሽ የቢዝነስ ስራ ልጀምር? ገንዘቡ ለሁለቱም አማራጮች የማይበቃ ከሆነ አንዱን መምረጥ የግድ ነው። በእርግጥም፤ ኬኩን ከመብላት ወይም ኬኩን ይዞ ከመቆየት አንዱን መምረጥ ያስፈልጋል። በልተህ ስታበቃ፤ እጅህ ላይ ኬኩ እንዲኖር መጠበቅ... ተፈጥሮ ላይ የማመፅ አብደት ይሆናል።

ዛሬውኑ ወጪ መቆጠብ ከፈለግክ፣ ጥራት ያለው ልብስ ይቀራል። በአነስተኛ ዋጋ ደረጃው ዝቅ ያለ ልብስ ትገዛለህ። ጥራት ያለውን ልብስ ከገዛህ ደግሞ ወጪ ቁጠባው ይቀራል። አንዱን መምረጥ የግድ ነው - የዛሬውን ቁጠባና የዛሬውን ልብስ ብቻ ካሰብን።

ነገር ግን ጊዜውን አርዝሞ ማሰብ ይቻላል። በ300 ብር የተገዛው ልብስ ከአመት በላይ አያገለግልም። በየአመቱ መግዛት ያስፈልጋል - ለሶስት አመት 900 ብር ማለት ነው። በ600 ብር የተገዛው ልብስ ግን ለሶስት አመት ያገለግላል። ስለዚህ ጊዜውን ወደ ሶስት አመት አርዝመን ካሰብነው፤ ጥራት ያለው ልብስ መግዛትና ወጪ መቀነስ እንችላለን።

"ገንዘቡን ለአሜሪካ ጉብኝት ወይስ ለቢዝነስ ስራ ማዋል?" የሚለው አማራጭም ተመሳሳይ ነው። ዛሬ፤ ከሁለቱም አንዱን መምረጥ የግድ ነው። ነገር ግን፤ የቢዝነስ ስራ በመጀመር በአንድ ወይም በሁለት አመት ውስጥ ለአሜሪካ ጉብኝት የሚበቃ ገንዘብ ማፍራት ይቻላል።

በቢዝነስ ስራው ውስጥም፤ አጣብቂኝ ጥያቄዎች መፈጠራቸው አይቀርም። ምርጥ እቃ በከፍተኛ ዋጋ ለደንበኞች ማቅረብ ይሻላል? ወይስ ጥራቱ የወረደ እቃ በአነስተኛ

ዋጋ ማቅረብ? ምርጥ እቃ ለማቅረብ፣ ተጨማሪ ወጪዎችን ስለሚጠይቅ፣ በአነስተኛ ዋጋ ማቅረብ አይቻልም - ያከስራል። አንዱን መምረጥ ያስፈልጋል - የዛሬውን ትርፍ ብቻ የምናስብ ከሆነ።

የረዥም ጊዜ አትራፊነትን የምናስብ ከሆነ ግን፤ "ጥራት ወይስ ዋጋ" (either quality or price) የሚለውን አጣብቂኝ መፍታት ይቻላል። በተመጣጣኝ ዋጋ ጥሩ እቃ በማቅረብ በደንበኞች ዘንድ ተመራጭነትን ማግኘት ስለሚቻል፤ የቢዝነሱ ገበያ እየሰፋ ይሄዳል፤ ከእያንዳንዱ ሽያጭ የምናገኘው ትርፍ አነስተኛ ቢሆንም፣ ከብዛት እናተርፋለን።

አንዳንድ እናቶች ወንድ ልጃቸውን "ወይ ከሚስትህ ወይ ከኔ ምረጥ" ይላሉ። ቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST) የገባው ልጃቸው፤ የቅፅበቱና የቁንፅሌ አስተሳሰቦችን ስላስወገደ ጥያቄው አጣብቂኝ አይሆንበትም። "ሁለታችሁንም እመርጣለሁ፤ ግን በአንድ ጊዜና በአንድ ቦታ አይደለም። አላማችሁም ይለያያል። ህይወት ምሉዕ (Whole, Healthy) የሚሆነውም በሁለታችሁም ነው" ይላል።

# 11. "ወቀሳ" የሚባል ነገር አይኖርም
## There is no blame

ወቀሳ የሚባል ነገር አይኖርም።

አንደኛ፤ ያለፈው አልፏል፣ በወቀሳ አይለወጥም። ካለፈው ተምረህ የወደፊቱ ላይ አተኩረህ ዛሬን ስራበት። ሁለተኛ፤ ሌላ ወገን የህይወትህ አዛዥ ማድረግ እንደሌለብህ ሁሉ፤ ሌላውን ወገን በሃላፊነት ተወቃሽ ማድረግም የለብህም።

ለችግሮቻችን ተወቃሽ የሚሆን ሌላ አካል ሁሌም አናጣም። ልጆች ወላጅን፣ ወላጅ ልጆችን፣ ተማሪ አስተማሪን፣ አስተማሪ ተማሪንና ወላጅን፣ ማኔጅመንት ሰራተኞቹን፣ ሰራተኞች ማኔጅመንቱን፣ ለችግሮች ተጠያቂ እናደርጋለን። ከዚህም አልፈን ዖታችን፣ መልካችን ወይም ፈጣሪ ላይ እናሳብባለን።

ለማሰብ እየሰነፍንና በ"መሰለኝ ደሳለኝ" ስሜት እየተነዳን፣ ያለትምህርትና ያለ ስራ ጊዜያችንን አባክነን፣ ራሳችንን አደህይተንና በድለን፣ ወይም ሌላ ሰው በድለንና ወንጀል ሰርተን፣ ጥንቃቄ የጎደለው ወሲብ ፈፅመን ወዘተ እናበቃና፤ ለውጤቱ ሃላፊነት የመውሰድ ጥያቄ አፍጦ ሲመጣ፤ "ሰይጣን አሳስቶኝ ነው" እንላለን

በጣም የወረደና አለማችን ከ200 አመት በፊት የቀበረው የጨለማው ዘመን ባህል ነው።

የዛሬ ህይወታችን የትናንተ አስተሳሰባችንና ተግባራችን ወይም ምርጫችን ውጤት ነው። በዘልማድ መምረጣችንን ሳናውቅ ወይም ሌሎች እንዲነዱን ፈቅደን ይሆናል። ብቻ ያለኛ ሚና ህይወታችን እዚህ አልደረሰም።

ለራሳችን ችግር ሌሎችን በተጠያቂነት ተወቃሽ አናድርግ ማለት፤ የራሳችንን ስህተቶች በሌሎች አናሳብብ ማለት ግን፤ ራሳችንን ስንወቅስ የህይወት ዘመናችንን እንጨርስ ማለት አይደለም። ያለፈው ነገር አልፏል። በወቀሳ አይለወጥምም፣ ወይም አይመለስም።

ሊለወጥ የሚችለው የዛሬ ሃሳባችን፣ ግባችንና ስራችን፣ እንዲሁም የነገ ብቃታችን፣ የነገ ስብእናችን እና የነገ ህይወታችን ነው። ስለዚህ ሳናሳብብ የትናንት ስሁተታችንን ማወቅ የሚኖርብን፣ እንድንማርበትና ዛሬ ስህተቱን ሳንደግም፣ ችግሮቹን ለማስወገድና

በስኬት ጎዳና ለመራመድ ነው። ከእንግዲህ በአካልና በአእምሮ፣ በኑሮና በስብእና ሳያቋርጥ በየጊዜው የሚበለፅግ አሰደሳች ህይወት ለመጎናፀፍ ግስጋሴ እንጀምር።

"ወቀሳ ሚባል ነገር የለም!"ከፊታችን የህይወት ከህሎትና አስደሳች ህይወት አለ!

# ቅንብራዊ አስተሳሰብ System thinking

## የስኬት መሳሪያ ነው

ሰው በተፈጥሮው፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ በአእምሮ እና በአካል፣ በመንፈስና በሃብት እየበለፀገ የሚቀጥል፣ አስደሳች ህይወት መኖር ይችላል። ተፈጥሮው ነው - ለጀግንነትና ለፍቅር ተጣጥሞ የተቀናበረ ክቡር ተፈጥሮ።

ይሁንና፤ አስደሳች የብልፅግና ህይወት፣ እንዲያው በዘፈቀደ እውን አይሆንም። ስኬትን ለመጎናፀፍ፣ ከተፈጥሮ ጋር ተጣጥሞ የተቀናበረና በተጨባጭ ስራ ላይ ሊውል የሚችል ትክክለኛ አስተሳሰብ ያስፈልገናል። ይህንን የሚያሟላ ነው ቅንብራዊ አስተሳሰብ (System Thinking)።

ቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST)፤ በደፈናው "አስተሳሰባችንን እናስተካከል" ብሎ የማውራት ጉዳይ አይደለም። "ቀና አስተሳሰብ ይኑርህ"፣ "ትልልቅ ነገሮችን ለማሰብ አስተሳሰብህን ቀይር" የሚሉና ተመሳሳይ አባባሎችን በደፈናው ማቅረብ ብዙም አያራምድም። ትርጉማቸው አሻሚ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ በተግባር እንዴት ስራ ላይ እንደሚውሉ ለማወቅ ይከብዳል። በተጨባጭ ለህይወታችን የሚያመጡት ለውጥም ኢምንት ይሆናል።

ቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST)፤ የተበጣጠሱ የምክር ሃሳቦችን የመደርደር ጉዳይም አይደለም። "እንዲህ አይነት ችግር ሲያጋጥምህ፣ ይህንን አድርግ"፣ "እንዲያ አይነት ችግር ሲመጣብህ፣ ያንን አድርግ"፣ "ለአንትን ስኬት ደግሞ እንደዚያኛው" የሚሉ ሚሊዮን ነጠላ ምክሮች፣ ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ሊያመዝን ይችላል። ሰው፣ ሮቦት አይደለም። ለሚሊዮን አይነት አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች፣ ሚሊዮን አይነት ምክር መከመር፣ ግራ መጋባትን ከማምጣት ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም።

ለዚህም ነው፤ በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወት ለመጎናፀፍ፣ ቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST) ተመራጭ የሚሆነው። እንዴት? የነጠሩ፣ የተጣሩ፣ የተቀመሩ ግልፅ ሃሳቦችን እጥር ምጥን አድርጎ ማቅረቡ ብቻ ሳይሆን፣ ሃሳቦቹንም አቀናብሮ ይዟል። የችግር መንስኤዎችንና የስኬት መሰረቶችን ለማወቅ አስተማማኝ የአእምሮ ብቃት ማስጨበጥ ብቻ ሳይሆን፣ በተግባር ችግሮችን ለማስወገድና ስኬቶችን ለመቀዳጀት የሚያስችሉ መሳሪያዎችን ያስታጥቃል።

- በ16ኛው ክፍለዘመን። ለምን? ከኮፐርኒከስ በኋላ፣ በትያትር አጀብ የሚያሰኝ እድገት የተመዘገበውስ? ይህን ተከትሎም ነው የልብወለድ ድርሰት መሰረት የተጣለው። ለማመን የሚያስቸግሩ አስደናቂ ድርሰቶች የተፈጠሩት ከ16ኛው ክፍለዘመን ወዲህ ነው።

ለሺ አመታት ባልታየ ሁኔታ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለምን ተአምረኛ አርቲስቶችና አስደናቂ ስኬቶች ድንገት ጎረፉ? የሰው ልጅ በትክክለኛ አስተሳሰብ መራመድ ከጀመረ፣ ማንም አያቆመውም። ድንቅ የተፈጥሮ አቅሙን ወደ አስደናቂ ብቃት በማሸጋገር፣ "ተአምር" የሚያሰኙ ስኬቶችን የሚቀዳጁ ሰዎች በብዛት በየአካባቢው ይፈጠራሉ።

ከዚያን ጊዜ በፊት፣ ለሺ አመታት፣ ያን ያህል ለወሬ የሚበቃ የሳይንስ ግኝትና እድገት አልነበረም። ታዲያ ድንገት የሳይንስ አባቶች በየቦታው እየተፈጠሩ አለምን ማዳረስ የጀመሩት ለምን ይሆን?

በሳይንስ፡ ጋሊሊ ጋሊልዮና ጆሃን ኬፕለር፣ ከዚያም አይዛክ ኒውተንና ጎትፍሬድ ሌብኒዝ፣ እነሱንም ተከትለው ካርል ጋውስና ማይክል ፋራዳይ፣ ዳልቶንና አቮጋድሮ፣ ከዚያም ማክስዌልና ኸርዝ፣ ኬልቪንና ጁል ፣... በአጭር ጊዜ በተከታታይ የሳይንስንና የሂሳብን ታሪክ የሚቀይሩ ድንቅ ግኝቶቻቸውን ለአለም አስነብበዋል።

በፊዚክስና በሂሳብ መስኮች ብቻ ሳይሆን፣ በኬሚስትሪና በባዮሎጂ፣ በህክምናና በኢንጂነሪንግ፣ በኢኮኖሚክስና በፖለቲካ ሳይንስ መስክም ጭምር ከ16ኛው ክፍለዘመን አንስቶ በየቦታው ብዙ ሳይንቲስቶችና ተመራማሪዎች፣ ስኬቶችና ግኝቶች እንደአሸን መፍላት የጀመሩት ለምንድነው? እውነታና ስሌት ላይ የተመሰረተ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ይዞ መራመድ ነው የስኬቶች ሚስጥር።

ከዚያ በፊት በነበሩ 1500 አመታት እንደነዚህ አይነት ሳይንቲስቶችና ስኬቶች ያልተፈጠሩትስ ለምን ይሆን? እምነትና ስሜት ላይ የተመሰረተ ጭፍን አስተሳሰብ ነው የውድቀቶች ሰበብ።

በየመስኩ የሳይንስ አባቶች ተብለው የሚታወቁት ሳይንቲስቶች አለምን በሚያንቀጠቅጡ ግኝቶች የሰው ልጅ በእውቀት እንዲራመድ ያደረጉት በአብዛኛው በመቶ አመታት ውስጥ ነው፣ በ16ኛው ወይም በ17ኛው ክፍለዘመን። ግን ብቻቸውን አልነበሩም። በዙሪያቸው አልፍና አልፍ ሳይንቲስቶች በየቦታው ተፈጥረዋል - ትክክለኛ አስተሳሰብ በተስፋፋባቸው ቦታዎችና ወቅቶች፣ በትክክለኛ አስተሳሰብ መራመድ በጀመሩ ሰዎች። ይህም ብቻ አይደለም።

በቴክኖሎጂ ፈጠራ፡ እንዲህ በአጭር ጊዜ የዳበረውን የሳይንስ እውቀት፡ ህይወትን በሚያሻሽልና ኑሮን በሚያበለፅግ መንገድ ስራ ላይ የሚያውሉ አልፍና አልፍ የስኬት ሰዎችም ተፈጥረዋል - የኢንዱስትሪ አብዮት ይሉታል። ዋና ዋና የፈጠራ ውጤቶች ተብለው በኢንካርታ የተመዘገቡትን 278 የስኬት ስራዎች ተመልከቱ። ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱ ብቻ (ከ1% በታች) ናቸው፣ ከ16ኛው ክፍለዘመን በፊት የተፈጠሩት። ከ99 በመቶ የሚበልጡት ፈጠራዎች ከዚያ ወዲህ የተሰሩ ናቸው፣ አሁንም በፍጥነት ቀጥሏል። ለምን? ትክክለኛ አስተሳሰብ የመያዝና

ያለመያዝ ጉዳይ ነው። አንተም አንቺም በቴክኖሎጂ ፈጠራ ስኬታማ መሆን ትችላላችሁ። ይህም ብቻ አይደለም።

**በብልፅግና፡** ከ16ኛው ክፍለዘመን ወዲህ በአሜሪካና በአውሮፓ የሰው ልጅ ምርታማነት በሙቶ እጥፍ ጨምሯል። እውነታ ላይ የተመሰረተ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ሲኖር፣ በማሽኖችና በእውቀቶች ብቻ ሳይሆን፣ በፈጠራዎችና በቴክኖሎጂዎችም፣ በኢንዱስትሪና በእርሻም፣ በአጠቃላይ በምርታማነትና በቢዝነስ መስኮች ብዙ ሚሊዮን ሰዎች ስኬትን ይጎናፀፋሉ። እንደ ሄንሪ ፎርድና ቶማስ ኤድሰን የመሳሰሉ ስኬታማ ሰዎች፣ ከድህነት ተነስተው በልፅገዋል። አሁንም ሚሊዮኖች እየበለፀጉ ነው። አንተም አንቺም በቢዝነስ ስኬታማ መሆን ትችላላችሁ - ሃብት መፍጠርና መበልፀግ። ይህም ብቻ አይደለም።

**በነፃነት፡** በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወት ለዘለቄታው አስተማማኝ የሚሆነው፣ የማሰብ እንዲሁም ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ሲከበር ነው። በራስ ጥረት ለመበልፀግ የመስራት መብት ተከብሮ፣ የራስን ህይወት በራስ ምርጫ የመምራት ነፃነት ሲረጋገጥ ነው። በጥረት ውጤትህ የመጠቀምና የማዘዝ የባለቤትነት መብት ተከብሮ፣ ከሌሎች ጋር ምርት የመለዋወጥ የቢዝነስና የኢኮኖሚ ነፃነት ሲከበር ነው። ይህ እውቀት የተገኘው በአብዛኛው ከ16ኛው ከፍለዘመን ወዲህ በነበሩ የተወሰኑ አመታት መሆኑን ልብ በሉ - ያስገኘውንም ውጤት።

ከነፃነት አስተሳሰብ ያፈነገጠ፣ የአፈና አስተሳሰብ እየተስፋፋ ሲሄድ ምን አይነት ውድቀት እንደሚፈጠርም በግልፅ ታይቷል - አንደኛ እና ሁለተኛ የአለም ጦርነቶች፣ ፋሺዝምና ኮሙኒዝም...። በትክክለኛው የነፃነት አስተሳሰብ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካ መስክ ከሳይንቲስቶች የተገኘው እውቀት፣ በአውሮፓና በአሜሪካ በተለያየ መጠንና ደረጃ ተግባራዊ በሆነባቸው ጊዜያትስ? በዚያው መጠንና ደረጃ ስኬታማ ሆነዋል - ነፃነትና ሰላም፣ ብልፅግናና አስደሳች ህይወትን እውን በማድረግ።

አእምሮን በመጠቀም፣ አስተዋይነትን መጨበጥና እውቀትን ማዳበር፤ ... እውቀትን ለቴክኖሎጂ፣ ለምርትና ለቢዝነስ ማዋል፤ በነፃነት ተከባብሮ በራስ ጥረት ሙያንና ሃብትን ማበልፀግ፤ በውጤቱም መጠቀምና ህይወትን ማሻሻል... እነዚህ ሁሉ፣ ከትክክለኛ አስተሳሰብ የሚመነጩ ናቸው። ለራስ የሚኮሩበትና የሚረኩበት ክቡር ስብእና፣ የደስታና የፍቅር ጣፋጭ ህይወት፤ በአጠቃላይ ምሉእ የስኬት ስብእና ... ከንቱ ወሬ ሳይሆን፤ ተጨባጭ እውነታ ነው። ይሄ ነው ከሰው ተፈጥሮ ጋር የተጣጣመ ህይወት።

## ቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST) - በአጭሩ

ጥቂት የውድቀትና የስኬት መረጃዎችን ከታሪክ የጠቃቀስነው፤ "ከሰው ተፈጥሮ ጋር የተጣጣመ ህይወት" ማለት የስኬት ህይወት ማለት እንደሆነ ለማሳየት ብቻ አይደለም። ከቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST) ጋር ግንኙነት ስላላቸው ነው።

የቅርብና የሩቅ ታሪኮችን፣ የውድቀት መንስኤዎችንና የስኬት መሰረቶችን፣ የድሮና

## 2. ከሂደት አቅጣጫ

እንደገና የፋብሪካውን የምርት ክፍል እናንሳ። ማሽን፣ ባለሙያና ጥሬ እቃ ብለን ያደራጀናቸውን ፈርጆች ከነመስተጋብራቸው ተመልክተናል። ለምሳሌ፣ የማሽን መበላሸት ባለሙያውን እንደሚያዳክም፣ የባለሙያ ድክመት ደግሞ ማሽኖችን ለብልሽት ሊዳርግ እንደሚችል አይተናል። የዚያኑ ያህል ደግሞ፣ የማሽን ብቃት የባለሙያውን ምርታማነት ያሳድጋል። የባለሙያው ብቃትም፣ ማሽኑ በከፍተኛ ደረጃ ግልጋሎት እንዲሰጥ ያደርጋል። መስተጋብራቸው ግን ይህ ብቻ አይደለም።

ዛሬ የምናየው የባለሙያ ብቃትና የማሽን አቅም ላይ ብቻ ማተኮር የለብንም። ሂደትን (ቆይታን) ማስተዋል አለብን። ባለሙያዎች ማሽኖቹ ላይ እየሰሩ በጊዜ ሂደት በሚያገኙት ተሞክሮ ስልጠናም ታክሎበት፣ በጊዜ ሂደት ተጨማሪ እውቀት፣ የሙያ ፍቅርና ልምድ እያዳበሩ ይሄዳሉ። በእርግጥ፣ የባለሙያዎቹ የብቃት ለውጥ ወዲያውኑ ጎልቶ ሳይታይ ይችላል። በቅፅበት ውስጥ የጎላ ለውጥ ስላልታየን፣ በጊዜ ሂደትም የጎላ ለውጥ አይታይም ወደሚል ስሜት የሚገቡ ሰዎች ብዙ ናቸው - የዛሬውን ብቻ በሚያይ የቅፅበቴ አስተሳሰብ። እውኑ ተፈጥሮ ግን በመስተጋብራዊ ሂደት የሚመራ ነው።

ወዲያውኑ ጎልቶ ባይታይም፣ ከቆይታ በኋላ ባለሙያው የብቃት እድገት ሲያስመዘግብ፤ ከቆይታ በኋላም ብቃቱን ተግባራዊ ማድረግ ሲችል፤ በማሽኑ ሊፈበረክ የሚችለው የምርት ጥራትና መጠን ይጨምራል። ይህን የስኬት መስተጋብር መገንዘብ የምንችለው፣ ዛሬንና አሁንን ብቻ በመመልከት ሳይሆን፣ የጊዜ ሂደትን የሚያካትት ጥንቅራዊ አስተሳሰብ በማጨበጥ ነው።

በጊዜ ሂደት የሰራተኞች ብቃት እየጨመረ መምጣቱን ብቻ ማየት የለብንም። ጊዜውን ይበልጥ አርዝመን እንመልከት። ከቆይታ (delay) በኋላ፤ ማሽኖቹ እያረጁና የአገልግሎት ብቃታቸው እየቀነሰ እንደሚሄድ ማየት አለብን። ግን ደግሞ በስራ ሂደትና በስልጠና ብቃታቸውን ያዳበሩ ባለሙያዎች፣ በአዳዲስና በተሻሻሉ ማሽኖች ላይ ይበልጥ ምርታማ እንደሚሆኑም ጭምር ማገናዘብ አለብን።

## 3. ከግብ አቅጣጫ

ከእውኑ ተፈጥሮ ጋር የማይጣጣሙ ቁንፅሌና ቅፅበቴ አስተሳሳቦችን በማስወገድ፤ "ምን? እንዴት?" በሚሉ ጥያቄዎች እየመረመርን፤ የነገሮችን መስተጋብርና ሂደታቸውን ያገናዘበ ጥንቅራዊ አስተሳሰብ ሊኖረን ይገባል ብለናል። ግን ለምን? ጥንቅራዊ አስተሳሰብ ለምን?

"እውኑ ተፈጥሮ፤ የመስተጋብር ሂደት ጥንቅር ስለሆነ፤ ከእሱ ጋር ለመጣጣም ነዋ" በማለት

ለጊዜው አስቸጋሪ ሃሳብ፣ ፈታኝ ውሳኔ፣ ከባድ ጥረት ቢጋረጥብንም፣ ከህይወት ግባችን ጋር ያለውን መስተጋብራዊ ትስስር ካገናዘብን፣ የዛሬውን ችግር የመቋቋም አስተዋይነት፣ ፅናትና ብርታት እንላበሳለን - በስኬት ጉዞ። "ለምን?" የሚለውን ጥያቄ፣ ሰባት ጊዜና ሰባ ሰባት ጊዜ እየደጋገምን መጠየቅ የሚኖርብንም፣ ውድቀትን በማስወገድ በስኬት ለመራመድ ነው - በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወት የምናፈቅር ከሆነ።

ከእውኑ ተፈጥሮ ጋር የተጣጣመ የእውነት፣ የህይወትና የፍቅር መንገዶችን የሚያመላክቱ ሶስት አቅጣጫዎችን አይተናል። መስተጋብር በዋና ዋና ነገሮች እይታ፣ መስተጋብር በሂደት እይታ፣ መስተጋብር በግብ እይታ። ከሶስቱም ጋር የተያያዙ ሶስት የቅንብራዊ አስተሳሰብ መሰረታዊ ንድፎች አሉ - ምህዋር (loop)፣ ቆይታ (delay)፣ ለውጥ (Impact)... ልንላቸው እንችላለን።

## ምህዋር

ቀደም ብለን የጀመርነውን ምሳሌ እንቀጥል። ለተማሪዎች ስኬት ዋናው ነገር፣ የእለቱን ትምህርት በጥሞና ለመከታተልና በተነሳሽነት መወሰናቸው ነው? ወይስ መረጃዎችን በማያያዝ ከፅንሰሃሳቦች ጋር እያሰላሰሉ ግንዛቤ መጨበጣቸው ነው ዋናው ነገር? ወይስ በሰአት ለመድረስ፣ ኖት ለመፃፍ፣ የክፍል ስራ ለመስራት ጥረት ማድረጋቸው ነው ዋናው ነገር? በቁንፅል አንዱን ነጥሎ ሌላውን መዘንጋት ተገቢ አይደለም። የዛሬ ግንዛቤ፣ የዛሬ ውሳኔና የዛሬ ጥረት በመስተጋብር የተሳሰሩ ናቸው። በፋብሪካው የምርት ክፍልም እንዲሁ፣ የዛሬው የማሽን፣ የባለሙያ እና የጥሬ እቃ ሁኔታዎች በመስተጋብር ተሳስረዋል። አንዱ በሌላው ላይ ለውጥ የሚያመጣ አስተዋፅኦ ወይም ተፅእኖ አላቸው - ሶስቱም ፈርጆች።






ሰአት የምናየው፣ የሰራነውን የምንቆጥረው፣ የቀረንን የምናሰላው ... የምንፈልገውን መጠን ለማሟላት ነው - በግቦቻችን መሰረት። በሰራንና በሄድን ቁጥር፤ ስራችንና እርምጃችን በጨመረ ቁጥር፤ ግቦቻችን ጋ ለመድረስ የሚቀረን ርቀት እየቀነሰ ይሄዳል። ከዚሁም ጋር የስራ መንፈሳችንና ብርታታችን ሊዳከም ይችላል። የጀመሩትን መጨረስ፣ ያጋመሱትን ማጠናቀቅ የማይሆንላቸው በርካታ ሰዎችን እናያለን።

ለእንዲህ አይነት መቀዛቀዝ ከሚዳርጉን ምክንያቶች አንዱ፤ "እንደ አገሌ መሆን፣ እንትና ጋ መድረስ" በሚሉ ግቦች መመራት ነው። ወደ ግቦቹ ስንቃረብ ወይም ግቦቹ ጋር ስንደርስ፤ መሄጃ ጠፍቶን እንቆማለን፤ ውስጣዊ ሃይላችን ይሞታል። የህይወት ትርጉም ይጠፋብናል። ሁነኛው መፍትሄ፤ የየሰአቱም ሆነ የየእለቱ፣ የየወሩም ሆነ የየአመቱ ግቦቻችን፤ እንዳይነጣጠሉ ማድረግ ነው። እንዴት? እነዚህን ግቦች በሙሉ፤ "በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወትን መቀዳጀት" ከሚለው ዋነኛ የህይወት አላማና ግብ ጋር የተሳሰሩ እንዲሆኑ ማድረግ አለብን። ያኔ፤ የአንድ ግብ መሳካት፤ ለሌላ ተጨማሪና ከፍተኛ ግብ መሸጋገሪያ ይሆናል። በአንድ ስኬት የምንቀዳጀው ደስታ፤ ለላቀ ደስታ ያነሳሳናል - በመጋቢ ምህዋር።

በሌላ በኩልም፤ መጋቢ ምህዋሮች፤ ከጊዜ በኋላ ወደ ገዳቢ ምህዋርነት ሊለወጡ እንደሚችሉ ልብ ማለት ይኖርብናል። የእርሻ መሬትና አዲስ ሬስቶራንት አዘጋጅታችኋል እንበል። ለእርሻው መሬት ሰራተኞችን እየቀጠራችሁ ማምረት ጀምራችኋል። በዚህ ከምታገኙት ትርፍ፤ ተጨማሪ ሰራተኞችን ለመቅጠር ያስችላችኋል። ሰራተኛ በጨመራችሁ ቁጥር፤ ትርፋማነታችሁ ይጨምራል። ትርፋማነትና የሰራተኞች ቅጥር በመጋቢ ምህዋር ጉዞአቸው ፈጥኗል። በሬስቶራንቱም ደንበኞችን ባበራከታችሁ ቁጥር፤ ትርፋማነታችሁ እያደገ ይሄዳል። ነገር ግን፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እድገታችሁ እየቀነሰ ባለበት መርገጥ ይጀምራል። ለምን?

ገዳቢ ምህዋር ውስጥ ገብታችኋል ማለት ነው። የእርሻ መሬቱ፣ ከተወሰኑ ሰራተኞች በላይ ማስተናገድ አይችልም። ሰራተኞችን ብትጨምሩ እንኳ፣ ምርታማነት አያድግም። ሬስቶራንቱም ከተወሰኑ ደንበኞች በላይ የማስተናገድ አቅም የለውም። የእነዚህን ነገሮች መስተጋብር ከዘነጋን፣ የጊዜ ጉዳይ እንጂ በትርፋማነታችን ላይ ገዳቢ ምህዋር መፍጠራቸው አይቀርም።

ሀ. የሌሎች ዋና ዋና ነገሮችን መስተጋብር እየዘነጋን በቁንፅል፤ የሰራተኛ ቅጥር ወይም የደንበኞች ቁጥር ላይ ብቻ ማተኮር አልነበረብንም። አንድ ቁንፅል ነገር፤ ሌሎቹንም ነገሮች የሚተካ አይደለማ። ሁሉንም ዋና ዋና ነገሮች በቁንፅል ነጣጥሎ ማየትም በቂ አይደለም፤ ከነመስተጋብራቸው እንጂ። እውኑ ተፈጥሮ የቁንፅል ነገሮች ከምር አይደለም። እውኑ ተፈጥሮ መስተጋብራዊ ጥንቅር ነው።

ለ. በተጨማሪ ሰራተኞችና በተጨማሪ ደንበኞች ትርፋማነታችን ጨምሯል - ለዛሬ ችግር ባይኖረው፣ በሂደት ግን የእርሻ ቦታው ወይም የሬስቶራንቱ ስፋት ካላደገ ችግር ይገጥመናል። ከጊዜ ቆይታ (delay) በኋላ የሚፈጠሩ መስተጋብራዊ ውጤቶችን በማያገናዝብ ቅፅበታዊ አስተሳሰብ እየተመራን፤ የዛሬውን ክንውን ወይም ከስተት ብቻ ማየት የለብንም። እውኑ

ተፈጥሮ፤ የቅፅበት ጉዳይ አይደለም። እውኑ ተፈጥሮ የመስተጋብራዊ "ሂደት" ጥንቅር ነው።

ሐ. የሬስቶራንቱ ወይም የአርሻ ቦታው አለመስፋፋት የእድገት ምህዋራችንን እስኪገድብ ድረስ መጠበቅና ተገድበን መቆም አለብን? በጭራሽ። የህይወት ግባችን አንዳች የስኬት ደረጃን ብቻ የሚመለከትና እዚያ የሚቆም አይደለም። ዋነኛው የህይወት ግብ፣ በየጊዜው ሳይቋረጥ የሚበለፅግ አስደሳች ህልውናን መቀዳጀት እንደሆነ በመገንዘብ፤ የእድገት ምህዋሩ ወደ ገዳቢ ምህዋር ሳይለወጥ በግስጋሴው እንዲቀጥል ማድረግ አለብን። እውኑ ተፈጥሮ ውስጥ የሚገኝ ህይወት፤ ግብ ተኮር የመስተጋብራዊ ሂደት ጥንቅር ነው።

## ከቁንፅሌ፤ ከቅፅበቴና ከአዛ ተጠበቁ

**ምህዋር፡** አንዱን ነገር ነጥለን በማፍጠጥ የምንደነዝዝ ቁንፅሌ አንሁን። ዋና ዋና ነገሮችን ከነመስተጋብራቸው የምናገናዝብበት መሳሪያ መያዝ አለብን።

**ሂደት (ቆይታ)፡** የዛሬ ከንውንና የአሁን ክስተት ላይ ብቻ እየተንበራጨቅን የምንሰምጥ ቅፅበቴ አንሁን። ደቂቃና ሰአት፣ ቀንና ወር፣ አመትና ዘመንን በሂደት አስተሳስረን፤ ዋና ዋና ነገሮችን ከነመስተጋብራዊ ሂደታቸው የምናገናዝብበት መሳሪያ ያስፈልገናል።

**መጋቢና ገዳቢ ምህዋር፡** በትንሽ ግብና በነጠላ ስኬት ጉዞአችንን የምንገታ፣ ያለተጨባጭ ግብ የምንተከዝ ወይም በዘፈቀደ የምንደናበር "አዛ" አንሁን። አንዱ ግብና አንዱ ስኬት፣ ለከፍተኛ ግብና ስኬት እያሸጋገረ መሄድ አለበት - በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወትን (የህልውና ግብን) ለመቀዳጀት። ዋና ዋና ነገሮችን ከነመስተጋብራዊ ሂደታቸው የምናገናዝብበትና የምንመዝንበት ግብ ተኮር መሳሪያ ያስፈልገናል። (ግብ ከሌለን የነገሮች መስተጋብር ቢገደብ ወይም ቢጠዝ ደንታ አይኖረንም)።

እነዚህን በሃሳብ ደረጃ የሚያሟላና በተግባር ደረጃም ውጤታማ የሆነ መሳሪያ ማስታጠቅ፤ የጥንቅራዊ አስተሳሰብ አስኳል ነው።

**የሚያሟላ?** አዎ። መስተጋብርን፣ ሂደትንና ግብን አጠናቅሮ ይዟል - እውኑ ተፈጥሮንና ህይወትን በትክክል፣ በግልፅ፣ በምልአት ከመገንዘብ የሚነሳ ነውና።

**ውጤታማ?** አዎ። በእውኑ ተፈጥሮና በህይወት ላይ የተመሰረቱ ሃሳቦችን ከያዝን፣ ግብ ተኮር መስተጋብራዊ ሂደቶችን (ምህዋሮችን) ማገናዘብ ከቻልን፤ ያለጥርጥር በእውኑ አለም ውስጥ፣ ለህይወታችን ልምላሜ በተጨባጭ ተግባራዊ ልናደርገው እንችላለን።

**መመዘኛችን፤** የህይወት ግባችን ነው - በየጊዜው በአካልና በአእምሮ የሚበለፅግ አስደሳች ህይወትን የመቀዳጀት አላማ።

**ተግባራችን፤** የውድቀት ምህዋሮችን መበጠስና ማስወገድ፤ የስኬት ምህዋሮችን መፍጠርና ማጠናከር ነው።

# አርኪታይፐስ - የተግባር መሳሪያና ንጥር ሃሳቦች

እንደ ቤት መስሪያ ብሎኬት፤ የቅንብራዊ አስተሳሰብ መሰረታዊ ብሎኬቶችን አይተናል - በህይወት ውስጥ የእውኑ ተፈጥሮ መስተጋብርንና ሂደትን የሚያሳዩ ምህዋሮች። መስተጋብራዊ ቆይታ (delay) ሳይዘነጋ፤ ምህዋሮቹ ሁለት አይነት ናቸው - ገዳቢ (የስክነት) ምህዋር እና መጋቢ (የጡዘት) ምህዋር።

እነዚህ ምህዋሮችን እንደ መሰረታዊ የተግባር መሳሪያ ልንጠቀምባቸው እንችላለን። መጋቢ ወይም ገዳቢ ምህዋሩ ለህልውና ልምላሜ የሚጠቅም ከሆነ እንዳይሰናከል እንጠብቀዋለን ወይም እናጠናክረዋለን። መጋቢ ወይም ገዳቢ ምህዋሩ ለህልውና ልምላሜ የማይጠቅምና የሚያጠወልግ ከሆነ እንበጥሰዋለን። በሌላ ጠቃሚ ምህዋር እንተካዋለን።

ነገር ግን በእነዚህ መሰረታዊ ብሎኬቶች ብቻ፤ የተሟላ የህይወት ክህሎት መሳሪያ ታጥቂያለሁ ማለት አይቻልም። እውኑ ተፈጥሮና ህይወት ውስጥ፣ ለቁጥር የሚያስቸግሩ የተለያዩ ነገሮችና ክስተቶች፣ ሁኔታዎችና ግቦችን እናገኛለን።

የእነዚህ ሁሉ መስተጋብራዊ ሂደቶችም፤ በመጋቢ ምህዋር ብቻ ወይም በገዳቢ ምህዋር ብቻ የተጠናቀሩ ላይሆኑ ይችላሉ። በርካታ መስተጋብራዊ ሂደቶች፤ የመጋቢ እና የገዳቢ ምህዋሮች ጥንቅር ናቸው።

ለቁጥር የሚያስቸግሩ ብዙ አይነት ነገሮችና ክስተቶችን፣ ሁኔታዎችና ግቦችን በመዘርዘር፤ ለእያንዳንዱም በተናጠል ተግባራዊ መሳሪያ ለመስጠት መሞከር ስህተት ነው። ሰው፤ ትእዛዝ ተቀባይ ግኡዝ ሮቦት አይደለም ወይም በሌላ አነጋገር ሰው አስቀድሞ የታዘዘውን የተሞላውን ብቻ እንዲፈጽም የተፈረደበት ሮቦት ወይም ማሽን አይደለም። ሰው ከመረጠ ማገናዘብ ይችላል።

ስለዚህ በእውኑ ተፈጥሮና በህይወታችን ውስጥ ያሉ እልፍ አእላፍ ነገሮችና ክስተቶችን፣ ሁኔታዎችና ግቦችን በማጥናት፤ ልዩነትና ተመሳሳይነታቸውን፣ ዋና ዋና ባህርያቸውንና መስተጋብራቸውን በመመርመር፤ ነጥረው የተጣሩና ተመጥነው የተቀመሩ መሳሪያዎችን መጨበጥ ያስፈልጋል፡፡

በእውኑ አለም በእልፍ አእላፍ ሁኔታዎች ውስጥ ለህይወት ልምላሜ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሳሪያዎችን የምናገኘውም በጥንቅራዊ አስተሳሰብ (ST) ነው። እነዚህ ንጥር ሃሳቦች፣ አርኪ ታይፕ ይባላሉ።

Rainforcing feedback, balacing feed back, delay በውስብስብ system ውስጥ ተደበላልቀው ይመጣሉ፡፡ እነዚህ 3ቱ የST አረፍተ ነገሮች የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ አረፍተ ነገሮቹ

የቴሌግራም
ቻናላችንን
ለመቀላቀል ና
ሌሎች
መጽሐፍት ና
ትረካዎች ለማግኘት
@amharicbooks24
ወይም
ይሄን ይጫኑ

ተከማችተው ምዕራፍና ሙሉ ታሪክ (STORY) ይፈጥራሉ:: የST STORY ARCHETYPE ይባላል::

ከላይ የጠቀስናቸውን ጨምሮ፤ እስከዛሬ ተጠንተው የተቀመጡ የአርኪይታፖች ቁጥር 12 ናቸው። ነገር ግን በ8 አርኪታይፖች በማጠቃለል በዚህ መፅሃፍ ቀርበዋል። የአባዎቹን ታሪክ እልፎ እልፎ እያስታወስን፤ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የቀን ተቀን ችግሮችን ለመተንተንና መፍትሄ ለማበጀት፤ ግቦቻችንን ለመቅረፅና ስኬት ለመቀዳጀት አርኪታይፖቹ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆኑ በሚያሳይ መንገድ ተተንትነዋል::

ስለመጪው ሕይወታችን እርግጠኛ መሆን የምንችልበት ብቸኛው መንገድ፤ ዛሬ ላይ ሆኖ መጪውን ጊዜ መገመት ሳይሆን፤ ዛሬ በእርግጠኝነት ወሰኖ ነገን መፍጠር ነው። ዛሬ የትናንት ልጅ እንደሆነ ሁሉ ነገም የዛሬ ልጅ ነው። ዛሬ ላይ ሆነን የተሻለ የነገ ህይወትን አሳምረን በST እንፍጠር።

# ክፍል 3
# የስኬት መሳሪያዎች

ከትክክለኛ አስተሳሰብ ጋር በጥቅሉ ብንተዋወቅም፤ በቂ አይደለም። በትክክለኛ አስተሳሰብ ነጥረው የተጣሩና ተመጥነው የተቀመሩ መሳሪያዎችን መጨበጥ ያስፈልጋል:: እነዚህ ንጥር መሳሪያዎች፣ አርኪታይፕ ይባላሉ።

"የስኬታማ አስተሳሰብ አዲስ ቋንቋ" ልንላቸውም እንችላለን - "ስኬታማ የህይወት ሶፍትዌር" ለመገንባት የምንጠቀምበት የፕሮግራሚንግ ቋንቋ።

በማንኛውም የኑሮ መስክ ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ሁሉ በግልፅ ለይቶ በማወቅ ይጀምራሉ - አርኪታይፖቹ። በዚህ አያቆሙም። ችግሮችን ከስረመሰረታቸው ለመንቀል ብቻ ሳይሆን፣ የስኬት መንገዶችን ለማወቅና በተግባር ስኬትን ለመቀዳጀት የሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸውና።

8ቱ አርኪታይፖች፣ ከእለትተእለት ኑሯችን፣ ከገጠመኞቻችንና ከምናውቃቸው የዘውትር ታሪኮቻችን ጋር እየተዛመዱ ቀርበዋል - በተጨባጭ ምን እንደሚመስሉና እንዴትስ በተግባር ልንጠቀምባቸው እንደምንችል ለማየት በሚያመች መንገድ።

አዲስ ቋንቋ

- ❖ ከሻፊ ጥገና - Fixes that fail (ታጭቦ ጭቃ እንደገና?)
  - ➢ ወደ ሁነኛ መፍትሄና ወደ አስተማማኝ እርምጃ መሸጋገር
- ❖ ሃላፊነትን እንደሸክም ማንፏቀቅ - Shifting the Burden (አለባብሶ ማረስ፣ በአረም ለመመለስ)
  - ➢ ለስኬት ሃላፊነትን መጨበጥ
- ❖ ግቦችን መሸርሸር - Drifting Goals (ሰበብ ፈጣሪ፣ ቅርብ አዳሪ)
  - ➢ ግቦችን በፅናት ማሳደግ
- ❖ መተጋተግ፣ መበላላት - Escalation (የእልህ ቤት፣ ሳይዘጋ ያድራል)
  - ➢ በአነቃቂ ፉክክርና ትብብር ስኬትን ማፋጠን
- ❖ የማህበር ብሬ አሳዛኝ አወዳደቅ - Tragedy of the Commons (የሁሉም የሆነ፣ የማንም ሳይሆን ይቀራል)
  - ➢ የጋራ አእምሮ የለም፤ የራስህን ተጠቀምበት
- ❖ ስኬት ለስኬታማ መሳይ - Success to the Successful
  - ➢ ተጨማሪ ስኬት፤ ለእውነተኛው ስኬታማ
- ❖ የስኬት ገደቦች - Limits to Success (ኋላ ቆሞ ከመገተር፤ አስቀድሞ ማሳመር)
  - ➢ የማያቋርጥ የስኬት ምህዋር መፍጠር
- ❖ ብቃትን የማይገነባ እድገት - Growth and Underinvestment (ሳይመግቡ ማለብ)
  - ➢ እያበለፀገ ብቃትን የሚገነባ ስኬት

# 1. የማያዛልቅ ጥገና ታጥቦ ጭቃ (Fixes that fail)

የኮንስትራክሽ ኩባንያውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሳደገ የመጣ ወጣት መሃንዲስ፤ ኩባንያውን ይበልጥ የሚያሳድጉ ሶስት ፕሮጀክቶችን በኮንትራት ተረክቦ ግንባታ ጀምሯል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ አይደለም፡፡ የስኬት መንገድ ላይ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥማሉ። መፍትሄ በማበጀትና የስኬት ጥረቱን በመቀጠል ነው ስኬቶችን እውን ማድረግ የሚቻለው።

ወጣቱ መሃንዲስ የስራ ማስኬጃ ገንዘብ ቢያጥረውም፤ ከባንክ ብድር ለማግኘት ጊዜ የሚፈጅ ስለሆነበት፤ በግል ከሚያውቀው ሰው፤ በተወሰነ ጊዜ ከወለድ ጋር የሚመለስ ገንዘብ ተበድሯል፡፡ ችግሩ፤ በተስማሙበት መሰረት እዳውን ለመመለስ አልቻለም፡፡ አበዳሪው እንዳያገኘው መሸሸና ስልኩን መዝጋት፤ እንደ መፍትሄ ሆኖ ታይቶታል፡፡

መፍትሄው ግን ሌሎች መዘዞችን ጎትቶ አምጥቷል፡፡ አንደኛ፤ ሌሎች ደንበኞቹና ተባባሪዎቹም በስልክ ሊያገኙት ስላልቻሉ፤ የተለያዩ ጥቅሞችን እያጣ ነው፤ እየተጎዳ ነው፡፡ ሁለተኛ፤ ከአበዳሪው ሰለሸሸ ብቻ ችግሩን ያስወገደ ይመስል፤ እዳውን ለመክፈል የሚያስችል ዘዴ ማፈላለግ አቁሟል፡፡ ሶስተኛ፤ መፍትሄው ከአንድ ሳምንት በላይ አልዘለቀም፡፡ መቼም፤ ከሰው ተደብቆ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን መምራት አይችልም፡፡

አበዳሪው፤ በሰው በሰው አጠያይቆ፤ የግንባታ ቦታው ድረስ መጥቶ አፋጠጠው፡፡ አሁንስ መፍትሄው ምንድነው? ምናልባት፤ በድርድር ለማግባባት ጥረት ቢያደርግና፤ ወለዱን በማሻሻል የክፍያ ጊዜውን ለማራዘም ቢስማሙስ? ያኔ ወጣቱ መሃንዲስ ፕሮጀክቶቹን አጠናቅቆ፤ በቀላሉ እዳውን መክፈል ይችላል - የተወሰነ ያህል ተጨማሪ ጥረትና ገንዘብ ቢያስፈልገውም፡፡ ወጣቱ መሃንዲስ፤ ይህንን መፍትሄ አልመረጠም፡፡

አበዳሪውን በፈገግታ ተቀብሎ፤ ከከተማ ውጭ ስልክ የማይሰራበት ቦታ ሄዶ እንደነበር በውሸት ለማሳመን ከሞከረ በኋላ፤ ቼክ ፈርሞ ሰጠው፡፡ ቢቃ በዚሁ ተገላገለ፡፡

ግን እስከመቼ? ባንክ ውስጥ የነበረው ገንዘብ ለስራ አውጥቶ እንደጨረሰው ያውቃል፡፡ ቢሆንም ለጊዜው፤ ከአበዳሪው ተገላግሏል፤ ችግሩን ፈታ፡፡ ምን ዋጋ አለው? መፍትሄው አልሰራም፡፡ አበዳሪው ቼኩን ለመመንዘር ወደ ባንክ ከሄደ በኋላ ባዶ እጁን ወደ ወጣቱ መሃንዲስ ተመለሰ፤ እዳውን ለማስከፈል፡፡ ብቻውን አይደለም፡፡ ፖሊስም ጭምር እንጂ፡፡

ወጣቱ መሃንዲስ በደረቅ ቼክ አጨበርብረሃል ተብሎ ተከሰሰ፡፡ ከተፈረደበት ብዙ ነገር

ያጣል፤ አዳውን ከካሳ ጭምር ይከፍላል፤ ለጠበቃና ለቅጣት ተጨማሪ ገንዘብ ያወጣል - የገንዘብ እጥረቱን ይበልጥ የሚያባብስ:: በዚያ ላይ ፍ/ቤት በመመላለስና በእስር፤ የስራ ጊዜውን ያባክናል፤ ፕሮጀክቶቹ ይዳከማሉ - የገንዘብ ምንጮቹን ይጎዳል:: «የማያዛልቅ ጥገና» እንዲህ ነው::

ዋናውና መሰረታዊው ችግር፤ የገንዘብ እጥረት ቢሆንም፤ ወጣቱ ግን ሁነኛ መፍትሄ እንደመፈለግ፤ በቁንፅል የችግሩ ውጫዊ ምልክት ላይ አተኮረ - የአበዳሪ ጭቅጭቅ ላይ:: ለአሁኗ ቅፅበት፤ ወይም ለዛሬ ብቻ፤ ከአበዳሪ ጭቅጭቅ ለመገላገል ጊዜያዊ መፍትሄዎችን (የማያዛልቁ ጥገናዎችን) መርጧል:: ውሳኔውንና ድርጊቱን ከነገ ህይወቱ ጋር አያይዞ ለማየት አልሞከረም:: የገንዘብ እጥረት ችግሩን ከማባባስ አልፎ፤ የገንዘብ ምንጩን የሚጎዳ ተጨማሪ ችግር እንደሚያመጡበት ለማሰብ አልፈለገም::

የማያዛልቅ ጥገና፤ የተለመደ የሰዎች ባህርይ ነው:: ብዙዎቻችን፤ የዋና ዋና ነገሮችን መስተጋብር በማገናዘብ፤ መሰረታዊውን ችግር ከመጋፈጥ ይልቅ፤ የችግሩ ውጫዊ ምልክት ላይ ብቻ እናተኩራለን::

ውጫዊው የችግር ምልክት፤ ለብቻው በቁንፅል ጎልቶ ስለሚያስጨንቀን፤ በአሁኗ ቅፅበት ለብቻው ገንኖ ስለሚያዋክበን፤ ፈጣን የህመም ማስታገሻና የችግር ማብረጃ ለማግኘት እንጣደፋለን - ሌሎች ዋና ዋና ነገሮችንና ነገን ሳናስብ::

በጊዜያዊ ማብረጃ፤ የችግሩ ምልክት እንዲጠፋ ያደርግልናል:: ግን፤ ዋናው ችግር ስላልተወገደ፤ ምልክቱም ከጊዜ በኋላ መልኩን ቀይሮ ወይም ከቀድሞው ገዝፎና በርክቶ እንደገና መከሰቱ አይቀርም:: በጊዜያዊ ማስታገሻ ራሳችንን በማታለል፤ ለመሰረታዊው ችግር ሁነኛ መፍትሄ ስላላበጀንለት፤ የችግሩ ምልክት ተባብሶ ሲመጣብንስ? ድሮ የለመድነውን ጊዜያዊ ማስታገሻ (ችግር መሸፈኛ) መጠኑን ከፍ አድርገን፤ ሌላም ማስታገሻ ጨምረን እንሞክራለን:: ይህም ተመልሶ ችግሩን እያባባሰ፤ እዙሪቱ እየከረረ ይሄዳል:: አንዳንድ ሰዎች ሱስ እስኪመስልባቸው ድረስ ይቀጥላሉ::

ካነበብነው የአሳዎች ታሪክ እንዳየነው፤ ለምግብ የሚሆን የባህር ዕፀዋት የተከሉት አሳዎች፤ የምግብ እጥረትን ለዘለቄታው ለማስወገድ ሳይሆን ለቅፅበት ረሃባቸውን ለማስታገስ ነበር የጓጉት:: ዕፀዋቱ ደግሞ፤ ለማደግ ጊዜ ያስፈልገዋል::

አሳዎቹ፤ «ለሁሉም ጊዜ አለው:: ለማረሥም፤ ለመዝራትም፤ ለማጨድም ጊዜ አለው» የሚለውን የተፈጥሮ ህግ(እውነት) አልገባቸውም፤ የአሁኗ ቅፅበት ላይ ብቻ ነው ያተኮሩት:: በዚያ ላይ፤ ለማደግም ሆነ ለመፍጠን፤ አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ነገሮች አሉ - ለምሳሌ ውሃ፤ አፈርና ማዳበሪያ ሊያገኝ የሚችል ጠንካራ ስራስር፤ እንዲሁም የፀሃይ ብርሃንን መቀበል የሚችል ጤናማ ቅጠል:: አሳዎቹ ግን፤ በቁንፅል የተከሉቹ ግንድ መርዘምን ብቻ ነው የፈለጉት::

አሳዎቹ፤ እንዲህ ራሳቸውን የቅፅበታዊነትና የቁንፅልነት እስረኛ በማድረግ፤ ተክሎቹን ወደ

ላይ በመንተት እድገታቸውን ለማፍጠን ሞክረዋል። ዘዴያቸው፤ ለጊዜው የሠራ ቢመስልም፤ የተከሉቹ እድገት አልፈጠነም። የተከሉቹ ስራስር ተጎድቶ እድገታቸው ተገቷል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ጭራሽ፤ ተክሉቹ ጠውለገው መሞት ጀመሩ - በማያዘልቅ ጥገና ወደ ባሰ ውድቀት።

አንዳንዶቹ አሳዎች፤ የፀሃይ ሃሩር ሲያስቸግራቸው፤ ሃሩሩን ተቋቁመው ወይም የፀሃይ መከላከያ ባርኔጣ በመጠቀም፤ ተክሎቹ ፀሃይ ሊያገኙ በሚችሉበት ማሳ ለመትከል አልመረጡም። ተከሎቹ አፈር ላይ መተከላቸውን ብቻ በቁንፅል በማየት፤ ዛሬ ከሃሩር ማምለጣቸውን ብቻ በመመልከት፤ ዋሻ ውስጥ ለመትከል ሄደዋል። ግን የሚያዛልቅ አልነበረም። ተክሉ ፐ፣ ጠወለጉ፤ ረሃቡም ከፋ፤ በየእለቱ ምግብ ፍለጋ በፀሃይ ሲንቃቁና በሃሩር ሲጠበሱ ይውላሉ።

ረሃባቸውን በቅፅበት ለማሸነፍ ጓጉተው፤ የወዳደቁ ነገሮችን ለቃቅመው የበሉ አሳዎች፤ ለጊዜው ረሃባቸው የታገሥ ቢመስልም፤ ወዲያው ታመሙ። ረሃብ የሚያስታግስ ምግብ ለመፈለግ መንቀሳቀስ አቃታቸው። የማያዛልቅ ከሻፊ ጥገና (የደመነፍስ መፍትሄ) በወድቀት ነው የሚቋጨው። ለዚህም፤ የዛሬ «ችግሮች»፤ ትናንት «መፍትሄ» የነበሩ ናቸው የሚባለው። የማያዛልቁ መፍትሄዎች፤ ችግርን ያስከትላሉ።

ህይወት ሂደት ነው። ብዙዎቻችን ግን፤ ዛሬን ከመጪው ጊዜ ጋር ሳናስተሳስር፤ የዛሬ ፍላጎታችንን ከዘላቂ አላማችን ጋር ሳናገናዝብ፤ የአሁኗን ቅፅበት ብቻ ለመገላገል ወይም ለመርካት በመጓጓት፤ ወደ ማያዛልቅ ጥገና እንቸኩላለን።

ህይወት መስተጋብር ነው። ብዙዎቻችን ግን፣ አንዳች ችግር ሲያጋጥመን፣ ከዋና ዋና ነገሮች ጋር (ለምሳሌ ከችግሩ ስረመንስኤ ጋር) ያለውን መስተጋብር በጥልቀት ሳናጤን፤ የችግር ምልከትን ብቻ በቁንፅል ለማጥፋት በደመነፍስ እንሮጣለን።

የዛሬ ችግርና የዛሬ ፍላጎት፤ ከመጪው ጊዜና ከዘላቂ አላማ ጋር በማቀናጀት የሂደት አካል አድርገን ካልተገነዘብነው፤ ከሌሎች ዋና ዋና ነገሮች ጋር በሚኖረው ትስስር ውስጥ መስተጋብሩን ካልተረዳነው፤ ፍላጎታችንን ወይም ችግራችንን አውቀነዋል ማለት አይቻልም።

ቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST) እንዲህ የሚል ህግ አለው - "if you don't know it, don't fix it !!" ችግሩን ካለወቅኸው በፍጹም አትንካው። «አላወቅኩትም» ማለት፤ አንድም ለመማርና ለሁነኛ መፍትሄ በር ይከፍታል፤ ሁለተኛም ቢያንስ ቢያንስ ችግሩን ከማባባስ ያድናል። የማያዛልቅ ጥገና ግን፤ የመፍትሄን በር ይዘጋል፤ ችግርን ያባብሳል።

ፈተና ሲከብድ - ለማለፍ በኩረጃ፣ ጉዳይ ሲዘገይ - ለማስፈፀም በሙስና፣ ስራ ሲጠፋ - ለመቀጠር በፎርጅድ ዲግሪ፤ … ችግርን ተገላግሎ ጊዜያዊ ፍላጎትን ለማርካት በማያዛልቅ ‹አቋራጭ› መንገድ የሚጓዙ ሰዎች ጥቂት አይደሉም።

ህመም ሲያጋጥም - በሽታን ባለመመርመር፤ ወሬሽን ሲከሰት - ስጋትን በአድልዎና ማግለል... እንዲህ በማያዛልቅ ጥገና ችግርን ለመሸፈን የሚሞከሩም ብዙ ናቸው:: ነገር ግን የማያዛልቅ ጥገና፣ የችግር ምልክቶችን ቢያስታግስም፣ ችግርን ከማባባስ አልፎ ያልተጠበቁ ተጨማሪ ችግሮችን ይፈጥራል እንጂ፤ ችግሮችን አያቃልልም::

ትምህርትን እዩ:: ከእውቀትና ከወደፊት ሙያ ጋር ያለውን ትስስር ባለመገንዘብ፤ ከክፍል ክፍል መሸጋገርን ብቻ በቁንፅል የሚመለከት ወጣት፣ ኩረጃ «መፍትሄ» ይመስለዋል:: የማይኮረጅ ፈተና ሲመጣስ? ያኔ፣ «መፍትሄ»ው ከውድቀት የሚያድን አይደለም:: የጥናት ልምድና የማስተዋል ብቃት ለማዳበር የሚያስችል «መፍትሄ» ባለመሆኑ፤ እውቀትንና የወደፊት ሙያን የሚያሳጣ መዘዝ ይዞ ይመጣል:: ኩረጃ፣ ዞሮ ዞሮ ምሁር መሳይ መሃይሞችን የሚፈለፍል ውድቀት የመሆኑን ያህል፣ ሌሎች የማያዛልቁ ጥገናዎችም፤ የከፋተኛ ውድቀት ምንጮች ናቸው::

በየቢሮው ስንጉላላ፤ ለጊዜው ጉቦ በመስጠት ጉዳይ ማስፈፀም ቀላል መፍትሄ ይመስላል:: ጉዳይ ማስፈፀማችንን ብቻ በቁንፅል እየተመለከትን፤ የዛሬውን ለማሳካት ብቻ እንጓጓለን:: ግን፤ ጉቦ በሰጠን ቁጥር፤ ባላየነው መንገድና ባልጠበቅነው ጊዜ ችግሮች ይባባሳሉ:: ተጨማሪ ጉቦ ለማግኘት፤ ይበልጥ ሊያጉላሉን ይበረታታሉ። ቀስ በቀስ፤ ሰውን በማጉላላት ጉቦ ለመቀበል የሚፈልጉ ሙሰኞች ይበራከታሉ::

ቀላል መፍትሄ ስለመሰለን የፈፀምነው ተግባር፤ ጉቦኞች እንዲያጠናከሩ በማድረግ፤ ያለጉቦ የማይሰራና ያለጉቦ መኖር የማይቻልበት ሥርዓት ይስፋፋል:: እኛን ያሾለከ የመሰለን የሙስና ቀዳዳ ለልጆቻችን የማያፈናፍን ወጥመድ ይሆባቸዋል::

ተምሮ የእውቀት ዲግሪ ለማግኘት ከመጣር ይልቅ፤ ስራ መቀጠርን ብቻ በቁንፅል ማየት፤ ለጊዜው የሚያስገኘውን ገቢ ብቻ በመመልከት፤ ፎርጅድ ዲግሪ ማዘጋጀትም አያዛልቅም:: ለጊዜው ባይታየውም፤ ከተቀጠረ በኋላ፤ ያለእውቀትና ያለሙያ ለመስራት ሲሞከር ወደ ጥፋት ማምራቱ አይቀርም:: ድክመቱን ለመሸፈን ከሚያባክነው ጊዜ በተጨማሪ፤ አስቀድሞ ባልጠበቀው መንገድ፤ ከርቸሌ ሊወርድ ይችላል - ለትምህርት ቤት መዋል የነበረበት ጊዜ ለእስር ቤት ይሆናል::

በእንዲህ አይነት የማያዋጡ ‹መፍትሄዎች› የምንጠመደው፤ አንድን ነገር ለብቻ ነጥሎ የሚያይ የቁንፅል አስረኛ (አቶ ቁንፅሌ) ስንሆን ነው፤ ወይም አሁንንና ዛሬን ብቻ የሚመለከት የቅፅበት አስረኛ (ወ/ሪት ቅፅበቴ) ስንሆን ነው::

1. በቁንፅል የተመለከትናቸው የችግርና የስኬት ምልክቶች ሲያጨናንቁን ወይም ሲያጓጉን፤ አብዛኞቻችን የአሁኗ ቅፅበትና ምልክቶቹ ላይ ብቻ ያተኮረ ቀላልና አቋራጭ መንገድ ማራኪ ሆኖ ይታየናል::

የስኬትን ስረመሰረት የመገንባትና የችግርን ስረመንስኤ የመፍታት ጥረትን የቀነሰልን

ስለዘዴዎቹ ግንዛቤ ስለሌላቸዉ ነዉ፤ ወይስ አገልግሎቱን ስለማያገኙ ነው፡ የወሊድ መቆጣጠሪያ መንገዶችን በተመለከተ የተሳሳቱ አመለካከቶች ስላላቸዉ ነው፡ በባህላዊ ወይም ኃይ ልማዳዊ ተፅዕኖዎች ስር ኖረው ነው፤ እነዚህና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እያነሳን እስከመጨረሻው ዘልቀን መንስዔዎችን መመርመርና በየደረጃው ላገኘናቸው ምላሾች ተገቢዉን መፍትሄ ማስጠት አለብን፡፡ «ሁሉን አቀፍ ዘላቂ ምላሽ» ማለትም ይህ ነው፡፡

እኛ ግን ብዙውን ጊዜ የከስተቶችን ስረ-መሠረት ሳይሆን ላይ ላዩን ስለምናይ የምንሰጠው ምላሽም ዘለቄታዊ ውጤት አያመጣም፡፡ ዘለቄታዊ ውጤት ለማምጣት ከከስተቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ውስብስብ ሁኔታዎችን ዘልቀን መመርመርና ቁልፍ መንስኤዎችን ማወቅ አለብን፡፡ ይህ ደግሞ ነገሮችን በጥልቀት መመርመርን፣ ከነገሮች ጀርባ ያሉ ስር የሰደዱ ሁኔታዎችን መረዳትና በእስተዋይነትና ከስሜታዊነት ወጥተን መጠየቅ ይጠበቅብናል፡፡

ይህም ማለት ችግሮችን አንዴ ብቻ «ለምን?» ብለን በመጠየቅ በምናገኘው መልስ ጠልቀን መረዳትና መሰረታዊ መንስኤዎችን ማወቅ ስለማንችል እስከ ሰባት ጊዜ «ለምን?» እያልን በመጠየቅ ስር የሰደዱና የችግሮቻችን ቁልፍ መንስዔ የሆኑ አስተሳሰቦችን፣ አሰራሮችንና፣ ከስተቶችን፣ ወዘተ መረዳት አለብን - 7ቱንም ቀናት «ለምን?» እያልን በመጠየቅ።

በእርግጥ ይህ አይነቱ ነገሮችን ጠልቆ የማየት ጉዳይ ችግሮችን ብቻ ሳይሆን የስኬታማ ውጤቶቻችንን መሰረታዊ ምክንያቶች ለመረዳትም ጠቃሚ በመሆኑ እያንዳንዳችን ልንለምደው፣ ሊኖረንና በእለት ተዕለት ኑሮአችን ልንጠቀምበት የሚገባ የህይወት ክህሎት አካል ነው፡፡

ለአላማ ስኬት የሚያበቃ ስረመሰረትን (ለምሳሌ እውቀትና ሙያን) እንዲሁም፤ ለችግር የሚዳርግ ስረመንስኤን (ለምሳሌ ዝርክርክ አሰራርን) ጥምር ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይ፤ ሰፋ አድርገንና አቀናጅተን በማሰብ፤ ስኬትን ከስረመሰረቱ አጠንክሮ ለመገንባት፤ ችግሩን ከስረመንስኤው መንግሎ ለመጣል የሚያስችል የተቀናበረ አስተሳሰብ፤ ዝግጅትና ጥረት ሊኖረን ይገባል - የማያዛልቅ ጥገና አዙሪት ለመበጠስ፤ የስኬት ምህዋር ለማጥበቅ።

# 2. ሸክምን ማንፏቀቅ
# አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ
# (Shifting the Burden)

ልናጠናው የሚገባ ትምህርት፤ ልንሰራው የሚገባ የቤት ሰራ፤ ማድረስ የሚኖርብን መልእክት፤ መጀመር ያለብን ጉዞ፤ መቆጠብ የሚኖርብን ገንዘብ፤ ልንታከመው የሚገባ ህመም፤ ማስተካከል ያለብን ስህተት... ሁሌም በዙሪያችን ይኖራሉ፡፡ ብዙዎቻችን ግን፤ ሃላፊነትን ገሸሽ ማድረግ፤ የሚያዋጣ ይመስለናል፡፡

ግብን ለማሳካት ወይም ችግርን ለመፍታት፤ በጊዜውና በቦታው የራስን ሃላፊነት መወጣት ይገባል፡፡ ሃላፊነትን እንደ ሸክም፤ ለሌላ ጊዜ፣ ለሌላ ቦታ፣ ለሌላ አካል ለማስተላለፍ መሞከር፤ Shifting the Burden ይባለል- ሸከምን ማንፏቀቅ-አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ፡፡

አለባብሶ ማረስ፤ ላይ ላዩ ሲታይ፤ በቀላሉና በፍጥነት እንድንዘራ ያስቻለን ይመስላል፡፡ በአግባቡ የማረስ ሃላፊነትን ለጊዜው ብንሸሸውም እውነታውን ልንሸውደው አንችልም፤ ጊዜውን አንፏቀቅነው እንጂ፤ አናመልጠውም፡፡ ቀን ጠብቆ በከፋተኛ አረም ይመለስብናል፡፡ ልፋቱን (the Burden) ወደ ሌላ ሰው ማንፏቀቅና መጫንስ? አባወራ አለባብሶ ሲያርስ፤ አረም የበዛ ጊዜ ሸክሙ በእመወራና በልጆች ላይ ይሆናል፡፡ ሸከሙን እንፏቅቆ ጫነባቸው ማለት ነው፡፡

በአሣዎቹ ታሪክ ብዙዎቹን እንደታዘብናቸው፤ የማምረት ሃላፊነትን ገሸሽ አድርገው፣ በቁንፅል የስኬት ምልክትን (ሙብላትን) ብቻ ነበር የሚያዩት፡፡ ለቅፅበት የችግር ምልክትን ማስወገድ (ረሃብን ማስታገስ) ላይ ብቻ ነበር ያተኮሩት፡፡

የምግብ እጥረቱ እየከፋ ሲመጣ፤ ታታሪው ዊዝ ዝም አላለም፡፡ የሌሎቹን አሳዎች ሃላፊነት በራሱ ላይ ጭኖ፤ የባህር ዕፅዋት እየተከለ ምግብ ሊያመርትላቸው ችሏል፡፡ ሌሎቹ አሳዎች በተገኘው ምግብ ሲቦርቁ፤ ዊዝ ግን ደስተኛ አልሆነም፡፡ የሁሉንም አሳዎች ሃላፊነት ወደ ራሱ እንፏቅቆ መሸከሙ፣ ብልህነት እንዳልሆነ አውቋል - ጥበበኛው ዊዝ፡፡

ጥበበኛ በመሆኑም ነው፤ ለምግብ እጥረት ሁነኛ መፍትሄ ምን እንደሆነ ማሰላሰል የጀመረው፡፡ አንደኛ ነገር፤ ዊዝ ለተወሰነ ጊዜ ካልሆነ በቀር የሁሉንም ሃላፊነት ተሸክሞ መቆየት አይችልም፡፡ ሁለተኛ ነገር፤ ሸከሙን ችሎ፤ በህይወት እስካለ ድረስ ሁሉንም መመገብ ቢችል እንኳ፤ አሣዎቹ ለዘላለሙ ሃላፊነት የመወጣትና የማምረት ብቃት ሳይማሩ ይቀራሉ፡፡ አምርቶ የሚያጎርስ ያጡ ጊዜ ምን ይውጣቸዋል?

ምልከቶችን ለመላበስም፤ የሌሎችን ሰዎች ሃብት የመመኘት የጥፋት መንገድን ያመቻቻሉ - የሌላ ሰው ሸክም እንዲሆኑ።

ሌላው ችግር፤ የእናትና አባትን ኃላፊነት ያለ እድሜ ወደ ልጆች በማስተላለፍ፤ ልጆች ከሚችሉት በላይ ቤተሰብን የመደገፍ ኃላፊነት እንዲሸከሙ ማድረግ ነው - ሌላው አይነት shifting the burden። ቤተሰብ ለጊዜያዊ ችግሩ ሲል ልጆችን ከህሎት በማያዳብር ሥራ ይጠምዳቸዋል። በዚህ ሰበብ፤ የትምህርት እድል ያጣው ልጅ፤ እውቀት ሳያካብት፤ ሁሌም ከህሎትን በማያዳብር ስራ ላይ ተጣብቆ በዝቅተኛ ገቢ ኑሮ የሚገፋ ይሆናል። እንደወላጆቹ፤ እሱም በዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ሆኖ የሚወልዳቸው ልጆች ተመሳሳይ እጣ ይገጥማቸዋል - ወላጅ እየጠሩ በድህነት አዙሪት መዝቀጥ።

ልጆች፤ በተለያዩ ምክንያቶች የተጎዱ ወላጆቻቸውን መደገፋቸው ጥሩ ነው። ልጅ የሚወለደው ወላጆችን ለመጦር ነው ብሎ፤ በልጆች ላይ ሃላፊነት መጫን ግን ስህተት ነው። «ይጦረኛል» የሚለው አስተሳሰብ በአገራችን እንደባህል ስለተያዘ፤ ብዙ ሰዎች ያለእቅድ ይወልዳሉ። ለእርጅና ጊዜ መጦሪያ ገንዘብ የማይቆጥቡም ብዙ ናቸው። እንዲህ አይነቱ ጠቃሚ መሳይ ባህል፤ ኃላፊነትን እንደ ሸክም እንዲቀቅ ወደሚቀጥለው ትውልድ የሚጭን ጐጂ ባህል ነው።

ልጆች፤ የማገናዘብና የማመዛዘን፣ የመወሰንና የመተግበር የህይወት ከህሎት እንዲያዳብሩ፤ ዲሲፕሊን ላይ የተመሠረተ የነፃነት መንፈስ እንዲጎናፀፉ ከተፈለገ፤ ማንኛውም ወላጅ የልጆችን ሃላፊነት ወደ ራሱ ማንሸራተትና መጫን የለበትም። የራሱንም ሃላፊነት ወደ ልጆች አንሸራትቶ መጫን አይኖርበትም። አለበለዚያ ቤተሰብም ሆነ አገር ከድህነት አይወጣም።

በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደር ወላጅ፤ የራሱን ሃላፊነት በልጆቹ ላይ ስለሚጭን፤ የተፈጥሮ እውቀትና የህይወት ከህሎትን የማዳበር እድል አጥተው የድህነት አዙሪቱ ይቀጥላል። ሻል ያለ ገቢ የሚያገኝ ወላጅም፤ የልጆችን ሃላፊነት ወደ ራሱ ጎትቶ እየጫነ፤ እውቀትና ከህሎት እንዳያዳብሩ እድል ይዘጋባቸዋል። በኢትዮጵያ ከተሞች በየጊዜው የምናየውን ድራማ መጥቀስ ይቻላል። ሃብት ያፈራ ወላጅ ሲያረጅና ሲሞት፤ ብዙም ሳይቆዩ የፈረሱ፣ የተዘጉ፣ የብጥብጥ ምክንያት የሆኑ የንግድ ድርጅቶችን ማየት የተለመደ ነው። ልጆች ከህሎትን አላዳበሩማ። ለምን? ወላጅ የልጆችን ሃላፊነት ደርቦ የመሸከም ስህተት ስለሚፈፅም ነው - shifting the burden።

## እርዳታ - ፀረ ብልፅግና ሲሆን

ድርቅ ሲከሰት መንግሥትና መያዶች፣ ለረሃብተኛ የምግብ እርዳታ መስጠታቸው ትክክል ነው። ምግብ መብላትና ረሃብን ማስታገስ ያስፈልጋል። በቁንፅል መብላትን ብቻ፤ ለየቅፅበቱ ረሃብ ማስታገስን ብቻ ከተመለከትን ግን፤ ማምረት የሚባል ነገር መኖሩን እንረሳዋለን።

ማንኛውም ቆሻሻ ነገር ወላጅ አለው:: የቆሻሻው ባለቤት፣ የማፅዳት ኃላፊነቱን ሳይወጣ በቀረ ቁጥር በዘመቻ ስናፀዳለት፣ እሱም ዞር ማለታችንን ጠብቆ ተጨማሪ ቆሻሻ ይጥልልናል:: እንደገና ዘመቻውን ይበልጥ ወደ ማጧጧፍ ስንገባ፣ እሱም ይበልጥ ግድ የለሽ እየሆነ፣ ቆሻሻውን ያበራክታል - ሸክሙን ለዘመቻ ትቶ:: ሃላፊነትን እንደሸክም ማሸጋገር (shifting the burden) በየመስኩ በሽ በሽ ነው።

ደግነቱ ከዚህ አባዜ በመላቀቅ፣ ችግሮችን ማስወገድና አላማዎቻችንን ማሳካት እንችላለን:: ለዚህም፣ በቅድሚያ ያጋጠመንን ችግር ወይም የምንፈልገውን አላማ፣ ከተለያየ አቅጣጫ በብዙ የአመለካከት መነፅሮች መመርመር ይኖርብናል:: በቁንፅሉና በቅፅበቱ፣ ያስጨነቀንን የችግር ምልክት ወይም ያጓጓን የስኬት ምልክት ብቻ ሳይሆን፣ የችግር ስረመንስኤ እንዲሁም የስኬት ስረመሰረትንም በማስተሳሰርና በረዥም ጊዜ እይታ በትኩረት ማገናዘብ ያስፈልጋል::

በሌላ መነፅርም፣ ከችግሩ ተጎጂነትና ከስኬቱ ተጠቃሚነት ጋር፣ በቀዳሚነት የማን ሃላፊነት እንደሆነና ማን እንደሚሳተፍ መለየት ያስፈልጋል:: ጊዜያዊ ምልክቶችን ረገብ የሚያደርግ ማስታገሻ ቢያስፈልግ እንኳ፣ በዚሁ ከመሰረታዊ መፍትሄ አንዘናጋም:: ለምን?

አንደኛ፣ ከቁንፅልና ከቅፅበት እስረኛነት በመላቀቅ፣ የነገሮችን ትስስርና የረዥም ጊዜ መስተጋብርን ያጣመረ አስተሳሰብ አግኝተናል:: ሁለተኛ፣ ችግሮችን ከውጫዊ ምልክትና ከስረመንስኤ፣ ስኬቶችን ከውጫዊ መገለጫና ከስረመሰረት ጋር ያቀናጀ አስተሳሰብ ይዘናል:: ሶስተኛ፣ ሃላፊነትን ከተሳታፊነትና ከቀዳሚ ባለቤትነት ጋር አንጥሮ ያስተነተነ አስተሳሰብ ጨብጠናል:: በአጠቃላይ፣ ለእውነታ ታማኝ የሆነና ህይወትን ለማበልፀግ የሚያስችል ቅንብራዊ አስተሳሰብ ታጥቀናል::

በቁንፅልነት፣ የነገሮችን ትስስር ላለማየትና በቅፅበታዊነት የነገሮችን የረዥም ጊዜ መስተጋብር ላለመመልከት አይናችንን ብንጨፍን፣ አእምሮአችንን ብንደፍን፣ እውነታውን ሊቀይር አይችልም:: የችግር ምልክቶችን ስንሸሽ ብንውል፣ መቼም የትም ከችግር አናመልጥም:: የችግሩ ስረመንስኤ በአንዳች ተአምር አይወገደማ፤ «አናይህም» ብንለው እንኳ፣ ሁልጊዜ በሁሉም ስፍራ ከኛው ጋር ይሆናል:: የስኬት ምልክቶችን ስናሳድድ ብናድር፣ መቼም የትም ከስኬት ጋር አንገናኝም:: የስኬት ስረመሰረት በአንዳች ምትሃት እውን አይሆንማ፣ ሁልጊዜ በሁሉም ቦታ ከኛው ጋር አይደለም::

የችግርን ስረመንስኤ ማስወገድና የስኬትን ስረመሰረት መገንባት ያስፈልጋል:: የእነዚህ ተግባራት ባለቤት ማን መሆን አለበት? የችግሩ ቀዳሚ ባለቤት የሆነው አካል እንዲሁም የስኬት ባለቤት መሆን የሚፈልገው አካል ነዋ:: ሌሎች አካላት በጊዜያዊነት ድጋፍ መለገሳቸው ባይከፋም፣ ቀዳሚ ባለቤቱ የመፍትሄው አካል ካልሆነ፣ ችግሩ ከስረመንስኤው አይነቀልም፤ ስኬት ከስረመሰረቱ አይገነባም::

# 3. ግብን መሸርሸር - ትግልን ለመሸሽ መነሳሳትና መቀዛቀዝ (Drifting Goals)

በማያዛልቅ ጥገና እንዲሁም ሸክምን በማሸጋገር፤ ከችግር ተላቅቆ ስኬትን መቀዳጀት አይቻልም፡፡ ለምን? የችግርን ስረመንስኤ ለማስወገድና የስኬትን ስረመሰረት ለመገንባት እንዳንጥር ስለሚያደርጉ፣ ወደምንፈልገው ግብ አያደርሱንም፡፡

ታዲያ ምን ይሻላል? በቅንብራዊ አስተሳሰብ፤ የችግርን ስረመንስኤ እያስወገዱና የስኬትን ስረመሰረት እየገነቡ ግቦችን መምታት ይቻላል፡፡ ብዙ ሰዎች ግን በማያዛልቅ ጥገና ሲወራጩ ወይም ሸክምን ለማሸጋገር ሲራወጡ ይከርሙና አልሳካ ሲላቸው፤ ግባቸውን ማሳነስ፤ ማጥበብና ማደብዘዝ ይጀምራሉ፡፡

አብዛኞቻችን አሁን ካለንበት ደረጃ እጅግ የሚበላልጡ ትላልቅ አላማዎችና ግቦች፣ ብዙ ምኞቶችና ህልሞች ኖረውን ያውቃል - አዳዲስ ስኬቶችን ለመጎናፀፍ ያለሙ፡ አዲስ ስኬት እውን እንዲሆን ግን፤ በየጊዜው እውቀትን ማዳበርና አዳዲስ ግንዛቤዎችን መጨበጥ ያስፈልጋል፤ በየጊዜው ልምድን ማዳበርና በጥረት አዳዲስ ሥራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ ወይም ቢያንስ ቢያንስ የድሮውን እውቀት በአዲስ መንገድ መጠቀም፣ አሮጌውንም ስራ በአዲስ መንገድ መስራት ያስፈልጋል።

ትልቅ ማለም ስህተት አይደለም። እንዲያውም ትልቅ ምኞትና አላማ፤ ትልልቅ ግቦችና እቅዶችን መያዝ በጣም ተገቢ ነው፡፡ ችግሩ ምን መሰላችሁ? ትልልቅ ግቦችን ይዘን ከተነሳን በኋላ፤ እነዚያን የሚመጥን ግንዛቤ ለመጨበጥና እውቀት ለማዳበር፤ ፅናት ለመላበስና በራስ የመተማመን መንፈስን ለመገንባት፣ ጥረት ለማሳደግና ልምድ ለማካበት ራሳችንን አናነሳሳም፡፡

አልያም በየቦታው እንቅፋትና ፈተና ሲያጋጥመን፤ ተነሳሽነትን ይበልጥ ከማጋጋል ይልቅ፣ ተነሳሽነትን በማቀዛቀዝ ትልልቅ ግቦቻችንን ቀስ በቀስ እየሸረሸርን የቁልቁለት ምህዋር እንጀምራለን፡፡

መበልፀግን በማለም ከተነሳን በኋላ፤ ትንሽ ቆይተን «መሰረታዊ ፍላጎቶችን (ምግብ፤ ልብስና መጠለያን) ካሟላን ይበቃል» ብለን አላማችንን እናሳንሳለን፡፡ ከዚያም ይበልጥ አላማችንን ከማደብዘዝ አልፈን አላማችንን ሸርሽረን ስንጨርስ፤ «ይህችን አታሳጣኝ፤ የባሰ አታምጣ» ወደ ማለት እንገባለን፡፡

እንደ አንትና ዝነኛ መሃንዲስ፤ የተከበረ የቢዝነስ ሰው፤ ወይም ታዋቂ ሃኪም ለመሆን አልሞ ይነሳል፡፡ ግን ብዙም አይቆይም፡፡ «በምህንድስና፤ በቢዝነስ፤ በህክምና ትምህርት ዲግሪ ካገኘሁኝ በኋላ፣ በሙያዬ የመንግስት ተቀጣሪ፤ የእቃ ግዢ ሃላፊ፤ ወይም የወረዳ አስተዳዳሪ ብሆን በቂ ነው» ይላል፡፡ ትንሽ ቆይቶ፤ «ዲግሪ ማግኘትምኮ ራሱ ትልቅ ቁም ነገር ነው» ወደ ማለት ይገባል፡፡ «ለነገሩ 12ኛ ክፍል መጨረስም ቀላል ነገር አይደለም» … እንዲህ እንዲህ እያለ፤ «ተምረናል የሚሉ ሰዎችስ የት ደረሱ?» በማለት አላማውን ሸርሽሮ ይጨርሳል፡፡

የእውነትን መንገድ በፅናት ይዤ ስኬታማ እሆናለሁ ብሎ ይጀምርና፤ «እኔ ንፁህ ልሁን እንጂ አጭበርባሪዎችንና ሙሰኞችን ለመከላከል ጣጣ ውስጥ አልገባም» ብሎ ራሱን ያዳክማል፡፡ «እጄን እስካላስገባሁ ድረስ፤ ከሙሰኞቹ ጋር ብበላና ብጠጣ፤ ቢጋብዙኝና ቢገዙልኝ ምን ጨነቀኝ» ወደ ማለት ያመራል፡፡ ከዚያም፤ «ብዙ ገንዘብ የማገኝበት ስለሆነ ለዛሬ ብቻ ባጭበረብር ወይም ሙስና ብቀበል ችግር የለውም» በማለት የተነሳለትን አላማ ሸርሽሮ ይጨርሳል፡፡

በዚህ አያበቃም፡፡ «ለትንሽ ጊዜ ኑሮዬን አስተማማኝ እስካደርግ ድረስ ብቻ እንጂ ከዚያ በኋላ በፅናት የእውነትን መንገድ እከተላለሁ» ማለት ይጀምራል፡፡ «ሁሉም ሰው አጭበርባሪና ሙሰኛ ነው፤ ከእያንዳንዱ ሃብት በስተጀርባ ወንጀል አለ፤ እኔ ግን እንደሌሎች መጥፎ ወንጀለኞች፤ ሰውን አልገድልም፤ አላሰቃይም» በማለት በወንጀል ይዘፈቃል፡፡

አላማና ግቦቻችንን ወደ መሸርሸር የምንገባው፤ እውነታን ለመሸወድ ስንሞክር፤ ለዚህም ራሳችንን «የቁንፅልነት እና የቅፅበታዊነት እስረኛ» ስናደርግ ነው፡፡ እውኑ መነሻችንን፤ የሩቅ አላማችንንና ዝርዝር ግቦቻችንን በትኩረት ሳናጤን፤ ከነትስስራቸውና ከነመስተጋብራቸው ሳንመረምር፤ አንዱ ነገር ላይ ብቻ በቁንፅል እናፈጣለን፤ በየቅፅበቱ ትኩረታችን እየተፈራረቀ መቅኖ እናጣለን፡፡

አሁን ያለንበትን ሁኔታ፤ ወደፊት የምንመኘውን ግብ፤ እና ሂደቱን አስተሳስረን ካልመረመርን፤ የአሁኗ ቅፅበት ላይ ብቻ የምንደፋደፍ፤ ወይም ምኞት ተሟልቶ የምናይበትን ቅፅበት እየናፈቅን የምንጠብቅ እንሆናለን፡፡

## እውቀት፣ አላማ፣ ሙያ

ጥቅል ምኞት፤ ዋና አላማ፤ የየደረጃው ግብ፤ የየእለቱና የየደቂቃው ውሳኔ… ሁሉም የምርጫ ውጤቶች ናቸው፡፡ ከዚህኛውና ከዚያኛው፤ ከእንዲህኛውና ከእንዲያኛው፤ ከማድረግና ካለማድረግ… ከበርካታና ከተለያዩ አማራጮች መካከል ነው የምንመርጠው፡፡

ነገር ግን ጥሩና ጠቃሚ የሆነውን አላማ ወይም ግብ ለመምረጥ፤ ትክክለኛና እውነተኛ የሆነ ግንዛቤ ያስፈልጋል፤ እውቀትን ይጠይቃል፡፡ ከግንዛቤና ከእውቀት በመነሳት ስንመርጥና ስንወስን፤ በዚያው ልክ በየትኛው ዘርፍ ግንዛቤያችንን እስፋተን መጨበጥ እንዳለብን፤ በየትኛው

መስከ አውቀታችንን በጥልቀት ማዳበር እንዳለብን የትኩረት አቅጣጫችንን እየወሰንን ነው።

የመሃንዲሶችን የህንፃና የድልድይ ስራዎች አይቶ ግንዛቤ የጨበጠ ወጣት፣ በመሃንዲስነት ሙያ ለመሰማራት መርጦ አላማ ይይዛል። በዚህ ምርጫውም እማካኝነት በውስጠ ታዋቂነት ምን እየወሰነ ነው? በምህንድስና መስክ ላይ በማተኮር፣ ግንዛቤ ማስፋትና እውቀት ማዳበር እንዳለበት እየወሰነ ነው። መማር፣ ማጥናት፣ መመራመር ይኖርበታል። እንዲህ ግንዛቤው እየሰፋና እውቀቱ እየዳበረ ሲሄድ፣ አላማውን ይበልጥ እያጠነከረና እየወደደ ይሄዳል። ይህም ይበልጥ የሙያ ትኩረቱን ያጨምርለታል - መረጃ ለመሰብሰብ ማስተዋልን፣ ግንዛቤ ለመጨበጥ ማሰላሰልን፣ እውቀት ለማዳበር መመራመርን እንዲወድ ያደርገዋል።

አላማና እውቀት፣ ግብና ግንዛቤ፣ ውሳኔና አስተውሎት፣ እንዲህ እርስበርሳቸው የተያያዙ ናቸው፣ የሚወደዱ፣ የሚያስደስቱ። ከተግባር፣ ከጥረት እና ከልምድ ጋርም የተሳሰሩ ናቸው። ውሳኔዎቹን እየተገበረ፣ ግቦቹን ለማሳካት በጣረ ቁጥር፣ አላማውን የሚያሳካ የሙያ ልምድ ያዳብራል። ይህም የአላማ፣ የግብ እና የውሳኔ ፅናትን ያጎናፅፈዋል። በራስ የመተማመን የአላማ ፍቅርን ያጠናክርለታል። ለአላማው መሳካት የሚያውለው የጥረት ጊዜም በጣም ተወዳጅና አስደሳች ይሆንለታል።

አላማው ከእውቀትና ከልምድ ጋር፣ ግቦቹ ከግንዛቤና ከጥረት ጋር፣ ውሳኔው ከአስተውሎትና ከተግባር ጋር ... እርስ በርስ በተመጋጋቢ መስተጋብር የተሳሰሩ ናቸው። አንዱ ሲበለፅግ፣ ሌላውን ያበለፅጋል።

መረጃ ማስተዋልን፣ ግንዛቤ መጨበጥን፣ እውቀት ማዳበርን ካልመረጠ፣ አላማው ከባዶ ህልምነት ጋር እየተመሳሰለ፣ የአላማ ፅናቱ ይዳከማል። ከዚያም ቀስ በቀስ ይሸረሸረዋል። በየጊዜው መተግበርን፣ በሂደት መጣርን፣ የሙያ ልምድ ማዳበርን ካልመረጠም፣ አላማው ወደ ባዶ ምኞትነት እየተቀየረ፣ በአላማ የመተማመን ፅናት ይርቀዋል። ቀስ በቀስ አላማውን ይሸረሽራል።

ወጣቱ በራሱ አእምሮ ከመመራት ይልቅ፣ በሌላ ሰው ግፊት አላማውን ወይም ግቦቹን ቢመርጥስ? በወላጆች ወይም በጓደኞች ግፊት ተመርቶ፣ ራሱ ከልብ የማይወደውን አላማ የሚይዝ ወጣት ጥቂት አይደለም። «እንደ እገሌ በህዝብ የሚከበር ሰው» የመሆን የዝነኝነት ጥም አሸንፎት፣ ያለዝንባሌው ሌላ የሙያ መስክ እንደ አላማ የሚመርጥም ብዙ ነው።

ይህን መንገድ የተከተለ ወጣት፣ አላማው ሸክም ይሆንበታል።በዚሁ የሙያ መስክ አተኩሮ መረጃዎችን ማስተዋል፣ ለግንዛቤ ማሰላሰል፣ ለእውቀት መመራመርም ከባድ ጭነት ይሆንበታል - አሰልቺና ደባሪ ሸክም። ውሳኔዎቹን መተግበር፣ ለግቦቹ መጣር፣ ለአላማው የሙያ ልምድ ማካበት፣ አድካሚና አታካች ሸክም ሆኖ ይታየዋል።

አስተውሎት፣ ግንዛቤና እውቀት፣ እንዲሁም ተግባር፣ ጥረትና ልምድ ሲጓደል፣ አላማን ማሳካት ከባድ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ በአላማ የመተማመን ፅናትም ይከዳዋል። በቤተሰብ፣

በጓደኛ፣ በህዝብ ወይም በባህል ግፊት ተመርቶ የያዘውን አላማ መሸርሸር ይጀምራል:: «እንደ እገሌ ባይሆንም እንደ እንትና እሆናለሁ»፤ «እንደ እንትና ለመሆን ባልበቃም፣ ከአብዛኞቹ መሰሎቼ እሻላለሁ»፤«ከአብዛኞቹ ባልሻልም፣ በሙያው እሰራለሁ»፤ «ባልሰራበትም፣ ተምሬ ተመርቄያለሁ»፤ «ደግሞስ ለየትኛው ህይወት ነው!»።

## አላማ፣ ግብ፣ ውሳኔ

ሌላኛው ስህተት፣ የአላማ፣ የግቦች እና የውሳኔዎችን መስተጋብር ባለማጤን ይከሰታል:: እያንዳንዱ አላማ፣ በርካታ ግቦችን ያካትታል:: የውበት ቁሳቁስ መሸጫ በመክፈት የመበልፀግ አላማ ለማሳካት፤ በርካታ ግቦችን አስተሳስሮ ማሳካት ያስፈልጋል:: በደንበኞች ተፈላጊና ጠቃሚ የሆኑትን ቁሳቁሶች ማወቅ፣ እነዚህንም በጥራትና በቅናሽ ዋጋ ለማግኘት ዘዴ ማበጀት አንዱ ግብ ነው:: ደንበኞችን የሚስብና የሚያረካ አቀራረብ ማደራጀት ሌላው ግብ ነው::. ወጪን የሚቀንስ ቀልጣፋና አስተማማኝ አሰራር መፍጠርም እንዲሁ::

እነዚህ ግቦች በውስጣቸው በርካታ ንኡስ ግቦች ይኖሯቸዋል:: ለምሳሌ ደንበኞችን የሚስብና የሚያረካ አቀራረብ፤ በርካታ ንኡስ ግቦችን ይይዛል - ደንበኞችን ለማርካት በፍጥነት ማስተናገድ፤ የዱቤ ሽያጭ ማመቻቸት ወዘተ:: ደንበኞችን ለማርካት በፍጥነት የማስተናገድም እንዲሁ፤ በውስጡ በርካታ ግቦችን ያካትታል:: የመስተንግዶ ፍጥነትን በእጥፍ ለመጨመር፤ ሰቁን ለመስተንግዶ አመቺ ማድረግ፤ ፈጣን አስተናጋጆችን መቅጠር፤ ለአስተናጋጆች ስልጠና መስጠትና በስራ ውጤታቸው አወዳድሮ መሸለም...::

በየደረጃውና በየአይነቱ የምንከፋፍላቸው የተለያዩ ግቦች፤ እርስበርስና ከዋናው አላማ ጋር የትስስር መስተጋብራቸውን ካላጤንን፤ ግቦቹን የማሳካት ተነሳሽነታችን ይዳከማል:: ግቦቹን የማሳካት ፅናት በማጣት፤ ቀስ በቀስ እንሸረሽራቸዋለን::

አስተናጋጆችን በስራ ውጤታቸው አወዳድሮ መሸለም፤ ከቀልጣፋ አሰራርና ከደንበኞች እርካታ ጋር፣ ከዚያም ከትርፋማነት ጋር አስተሳስረን ሳናጤን በቁንፅል የምናየው ከሆነ፤ አስፈላጊነቱ ይደበዝዛል:: የአስተናጋጆችን ስራ የመከታተልና የመመዘን ጥረት፤ አድካሚ ጣጣ ሆኖ ይታየናል::

በሂደት የምናገኘውን ትርፍ ሳይሆን፤ በአሁኗ ቅፅበት ለሽልማት ገንዘብ መስጠታችንን ብቻ በማየት፤ ወጪው ያስጠላናል:: በየወሩ የነበረውን ሽልማት፤ በየሁለት ወሩ፤ ከዚያ በግማሽ አመት ብቻ እየሆነ፤ በየአመቱ መሸለምም እንተወዋለን - ግቡ ተሸርሽሮ ያልቃል::

በቁንፅልነትና በቅፅበታዊነት ግቦችን እንዳንሸረሽር፤ የተዋረድ (የላእላይና የታህታይ) እንዲሁም የጎንዮሽ መስተጋብሮችን ማጤን ያስፈልጋል:: ይህን ለማድረግ የሚረዳን አንዱ ቀላሉ መንገድ፤ «ለምን» የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ነው - «ይህ አላማ ለምን አስፈለገ?»፤ «ይሄስ ግብ ለምን አስፈለገ?»:: ማንኛውም ግብና አላማ፤ «ለምን?» ተብሎ መጠየቅ አለበት::

አላማውን ይሸረሽራል፡፡ 

ግብን የመሸርሸር አርኪታይፕ ውስጥ የምናገኘው መሠረታዊ ባህሪ፤ ለውጥ በስሜት ብቻ እንደማይመጣና በስሌት መመራት እንዳለበት ነው፡፡ ይህን ስህተት አንጥሮ የተገዘበ ቅንብራዊ አስተሳሰብ(ST)፤ የስኬት መንገድን ያሳያል - በ2 ጥያቄዎች፡፡

አንደኛ፤ አላማና ግብ ለማሳካት ምን ምን ያስፈልጋሉ? ቁሳቁስ፣ ፋሲሊቲ፣ ጥሬ እቃ... ካፒታል፣ የሰው ሃይል፣ አስተዳደር... መዝሬት፣ መንከባከብ፣ ማጨድ... አቅድ፣ አሰራር፣ ሙያ ...ወዘተ፡፡ አስፈላጊ ነገሮችን በደረጃውና በአይነታቸው ለይቶ ማወቅ ብቻ በቂ አይደለም። መስተጋብራቸውንም አቀናጅቶ ማጤን ያስፈልጋል - በቅንብራዊ አስተሳሰብ፡፡

ሁለተኛ፣ ለመሆኑ ይህ አላማ፣ ይህ ግብ፣ ይህ ውሳኔ ለምን አስፈለገ? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ አላማው፣ ግቦቹና ውሳኔዎቹ እንዲሁ በዘፈቀደ የተመረጡ ሳይሆኑ፣ በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወት ለመቀዳጀት የግድ አስፈላጊ መሆናቸውን በእርግጠኝነት የምናውቀው፣ «ለምን» የሚለውን ጥያቄ ደጋግሞ በመመርመር ነው፡፡ እርግጠኛ ስንሆን፤ የአላማ ፅናትና ፍቅራችን ይጨምራል፤ ከፍተኛ ሃይል ይሰጠናል፡፡ ለአላማ ስኬት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማከናወን ብርታት እናገኛለን።

ለምን የሚለው ጥያቄ በቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST)፤ «ማን ለምን» 7 ጊዜ ተደጋግሞ

# 4. መተጋተግ፣ መነቋቆር የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል (Escalation)

አላማዎን ሳይዘነጉ በፅናት እንደያዙ፣ እየተወዳደሩ አብሮ ማደግ፣ የስኬት ምህዋር ነው። አላማዎን የሚያሰናክል ጥቃት ሲያጋጥምዎ፣ አፀፋውን በመመለስ ጥቃቱን ማስቆም ያስፈልጋል። ብዙዎቻችን ግን፣ በማይረባ አላማ እየተነዳን ከአላማችን በሚያዘናጋ ጭፍን ስሜት እየተገፋፋን፣ በአላስፈላጊ ፉክክር እንተጋተጋለን። የሁለቱ ልዩነት፣ የገደልና የተራራ ያህል ነው - አንዱ ወደ ታች፣ ሌላው ወደ ላይ።

በኢትዮጵያ በጣም የሚከበር አንድ ኩባንያ የገጠመውን ችግር እንመልከት። ኩባንያው የተቋቋመው፣ ከአሜሪካ ተመሳሳይ ኩባንያዎች ጋር በሚስተካከል ግሩም የአሰራር ስርአት ነው። ለበርካታ አመታትም ስኬታማ ሆኗል - በአገልግሎት ጥራቱና በቴክኒክ ብቃቱ።

ኩባንያው፣ በየጊዜው የቴክኒክ ባለሙያዎችን ይቀጥራል፣ ያሰለጥናል። የቴክኒክ ብቃቱን ለመጠበቅ ዘመናዊና ጠንካራ ማሽኖችን ይጠቀማል። ብልሽት ሲከሰት ከማሽኖቹ ፈብራኪዎቹ መለዋወጫ መሳሪያዎችን እያስመጣ ይጠግናል።

አርባ አመታት አለፉ። አንዳንዴ እንደሚያጋጥመው፣ ከቴክኒክ ማሽኖቹ አንዱ ተበላሸና፣ መለዋወጫ ለማስመጣት አሜሪካ ለሚገኘው የማሽኑ ፈብራኪ የግዢ ትእዛዝ ተላለፈ። ፈጣን ምላሽ አልመጣም። ከሳምንት በኋላ፣ ምላሽ ለመስጠት ስለዘገየን ይቅርታ እንጠይቃለን የሚል መልእክት መጣ።

«የመለዋወጫ እቃው፣ ምን እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ ጊዜ ፈጅቶብናል፣ ምክንያቱም የምትጠቀሙበትን የማሽን አይነት መፈብረክ ካቆምን 30 አመት ሆኖናል። ድሮ የፈበረክነው ማሽን፣ እናንተ ጋ እስከ ዛሬ አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱ፣ ምርቶቻችን ከፍተኛ የጥራት ደረጃ እንዳላቸው ይመሰክራል።

ነገር ግን ለበርካታ አመታት ያንን ማሽን መፈብረክ ስላቆምን፣ መለዋወጫ እቃ ልናቀርብላችሁ ባለመቻላችን እናዝናለን። ባለፉት 30 አመታት፣ የተሻሻሉ ሞዴሎችን በየጊዜው ፈብርከናል። እነዚህም ጊዜያቸው አልፏል። አሁን፣ ኮምፒዩተራይዝ የሆነ፣ በርካታ አገልግሎቶችን የሚያከናውን አዲስ ሞዴል፣ በቅናሽ ዋጋ እየፈበረከን ነን። ይህን አዲስ ሞዴል ብትገዙ፣ ብዙ ጥቅም እንደምታገኙበት የሚያብራሩ ተጨማሪ መረጃዎችን በደስታ ልከናል»

በአስተማማኝ መሰረት ላይ ተቋቁሞ በስኬት ሲጓዝ የቆየው የኢትዮጵያ ኩባንያ፣ ለካ

በአንዳንድ መስኮች ከአለም የቴክኖሎጂ እድገት ጋር አብሮ አልተጓዘም። የውጪዎቹ ኩባንያዎች፣ በየጊዜው አዳዲስ ቴክኖሎጂ በመፍጠርና በማካተት የተሻሻሉ ሞዴሎችን ይፈበርካሉ። የኢትዮጵያው ኩባንያ ግን፣ እዚያው የድሮው ሞዴል ላይ ቆሟል። ማሽኑ ሲበላሽ፣ ለእድሳት መለዋወጫ እቃ ማግኘት አልቻለም። ከምፒዩተራይዝ የሆነ አዲስ ሞዴል እንዳይገዛ ደግሞ፣ እንቅፋቶች አሉበት። በቂ ገንዘብ ካለማጠራቀሙም በተጨማሪ፣ ለአዲሱ ሞዴል በሚመጥን የቴክኒክ እውቀት የሰለጠኑ ባለሙያዎችን አላዘጋጀም። ችግሩ ምንድነው? «ሳይቀልቡ የማለብ ችግር ነው» ሊባል ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ «አላማውን ይዞ በትጋት ባለመወዳደሩ የተፈጠረ ችግር ነው» ሊባል ይችላል።

## ፉክክር፣ የስኬት ምህዋር

አንድ የፓስታ አምራች፣ የብረት ፋብሪካ፣ ወይም የአውቶቡስ ኩባንያ የሚፎካከረው ያንኑ ምርት (አገልግሎት) ከሚያቀርቡ ኩባንያዎች ጋር ብቻ አይደለም። የፓስታ እማራጭ ማካሮኒ፣ የብረት አማራጭ ሲንቴቲክ ፋይበር፣ የአውቶቡስ አማራጭ ታክሲና ባቡር ከሚያቀርቡ ኩባንያዎችም ጋር ይፎካከራል። ይህም ብቻ አይደለም።

የፓስታ አምራች ኩባንያ፣ የፓስታ ማምረቻ ማሽኖችን ከሚያመርቱ ኩባንያዎች ጋር መፎካከር አለበት፣ በቴክኖሎጂ አብሯቸው ለማደግና ለመጓዝ መትጋት ይኖርበታል። እንዲህ አይነቱ ውድድር፣ በየጊዜው ተጨማሪ እድገቶችን የሚያጎናፅፍ የስኬት ምህዋርን ይፈጥራል - አንዱ ሲያድግ፣ ሌላውን እያነሳሳ፣ የአንዱ ስኬት ሌላኛውን እያባነነ።

አትሌቶች፣ ሪከርድ ለመስበር አሯሯጮችን ሲጠቀሙ አናይ የለ? አትሌቶቹ ፍጥነታቸውን አስተካክለው ብቃታቸውን ውጤታማ ለማድረግ አሯሯጮችን ይጠቀማሉ። መምህራን እርስበርስ ይወዳደራሉ፣ ተማሪዎችም እርስበርስ። ተማሪና አስተማሪም ይፎካከራሉ። ተማሪ በጣም ፈጣንና ጎበዝ እየሆነ ሲመጣ፣ ይህንን የሚመጥን ብቃት ለመያዝ አስተማሪ ይተጋል። የአስተማሪ ብቃትም እንዲሁ፣ ተማሪውን ያነሳሳል።

ሆቴሎች እርስበርስ ይፎካከራሉ፣ ስጋ አቅራቢዎችም። ነገር ግን አንድ ሆቴል፣ የአገልግሎት ጥራቱን ባሳደገ ቁጥር፣ ስጋ አቅራቢውም ያንን የሚመጥን ብቃት ማዳበር ይኖርበታል። አለበለዚያ፣ ሆቴሉ ሌላ የተሻለ ስጋ አቅራቢ ጋ ይሄዳል።

አምራችና አከፋፋይ፣ አርቲስትና የሂስ ባለሙያ፣ ሾፌርና ረዳት፣ ማኔጀርና የሽያጭ ሰራተኛ፣ ሃኪምና ነርስ፣ አቃቤ ህግና ጠበቃ፣ ... እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን አላማ እንደያዙ ሲፎካከሩ፣ አንዱ ሌላውን ያነቃቃል። «የትብብር ምህዋር»፣ «የስኬት ምህዋር» ነው። ተፎካካሪ አይጥፋ፣ አሯሯጭ አታሳጣኝ እንበል ይሆን?

ሌላ አባባልም አለ - «ምቀኛ አታሳጣኝ» የሚባል። ፉክክር ማለት ከሌላው በልጦ መገኘት ማለት ብቻ እንደሆነ የሚያምን ሰው፣ ፉክክርን ከምቀኝነት ጋር ያያይዘዋል። ያኔ የራሱን

አላማ ቸል እያለ ያዘናጋል:: በሌላ አነጋገር ከራስ አላማ በመነጠል፣ ፉክክርን ለብቻ በቁንፅል መመልከት ይጀምራል:: አላማውን በፍቅርና በፅናት መያዝ ያቆመ ሰው፣ ትኩረቱንና አቅሙን በሙሉ ተጠቅሞ በብርታት የመስራትና የመጣር ተነሳሽነቱ ይዳከማል:: እንደተመኘው፣ ከሌሎች ተቀናቃኞቹ ለመብለጥ የሚያስችል ስኬት አያገኝም:: የዚህን ጊዜ፣ አላማውንና ፉክክርን አስተሳስሮ በማገናዘብ ስህተቱን ማረም ይችላል:: ብዙዎች እንዲዚያ አያደርጉም።

በስኬት በልጦ መገኘት ካልተቻለ፣ «የበላይ መስሎ መታየት»ን የሚመርጡ ሰዎች ጥቂት አይደሉም:: መስሎ የመታየት ፉክክር ደግሞ፣ «የብክነት ምህዋር» ነው::

አንደኛው ወገን፣ ከተቀናቃኙ በልጦ ለመታየት ብቻ፣ የማይወደውን ውድ ልብስ ለመግዛት ብዙ ገንዘብ ያወጣል:: ይህን በመመልከት፣ ሁለተኛው ወገን ምን ያደርጋል? ለልጆቹ ትምህርት ያጠራቀመውን ገንዘብ ወስዶ፣ ተጨማሪ መኪና ይገዛና የበላይነቱን ያሳያል:: ያኛው እንጂቱ ያርራል:: የአንድ ሚሊዮን ብር ውድ መኪና ያስመጣል - ቢዝነስ ለማስፋፋት የመደበውን ገንዘብ አሟጥጦ:: የብሽሽቅ ፉክክሩ ይቀጥላል::

ለውድ ጌጣጌጥ፣ ለውድ መጠጥ፣ ለ«ቅምጥ» የመኪና ስጦታ፣... መስሎ ለመታየት የተጀመረው «የብክነት ፉክክር» ይጧጧፋል:: የአንዱ ድርጊት፣ ሌላኛውን እያነሳሳ፣ የብሽሽቅ ምህዋሩ ይሾራል - ከራስ አላማ የተነጠለ ፉክክር::

ነገር ግን፣ መስሎ የመታየት ፉክክር አያረካም:: «መስሎ በመታየት» ሌሎች ሰዎችን ማታለል ቢችልም፣ ራሱን በማታለል እውነታውን መሰረዝ አይችልም:: ተቀናቃኙን ማብሸቅ ቢችልም፣ ለራሱ ደስታን መጎናፀፍ አይችልም። ደስታ የሚገኘው በስኬት መንገድ ብቻ ነውና::

መስሎ የመታየት ውድድር፣ የብክነት ምህዋር እንደሆነ በማየት፣ የራሱን አላማ መዘንጋቱ ስህተት መሆኑን በማጤን፣ በቁንፅል ውድድር ላይ ብቻ ከማፍጠጥ መላቀቅ ይቻላል:: ብዙዎች ግን እንደገና ወደባሰ ስህተት ያመራሉ:: በልጦ መገኘት አልተቻለም:: «መስሎ የመታየት» ፉክክርም አላዋጣም:: ያኔ ተቀናቃኝን ወደ ታች ለማውረድ «የውድቀት ፉክክር» ይጀመራል - የመናከስና የመጠላለፍ ፉክክር::

አንዱ ወገን ተቀናቃኙን ለማሰናከል አንቅፋት ሲተክል፣ ሌላኛ በአፀፋው ገመድ ይዘረጋል - ጠልፎ ለመጣል:: እንደገና የመጀመሪያው ወገን አምርሮ የአፀፋ አፀፋ ይመልሳል። በዚህ የጦዘው ሁለተኛው ወገን፣ ጥርሱን አሹሎ ይመጣል፣ ሌላኛው ደግሞ ጦሩን ቀስሮ። እየተጧጧፈ ይቀጥላል::

ሁለቱ አካላት የየራሳቸው አስተዋፅኦ ስለሚያደርጉ፣ ውጥረቱ ይባባሳል:: የባልና የሚስት ቀላል አለመግባባት፣ በአስገራሚ ፍጥነት ሊጋጋል ይችላል:: በፍቅር ደስተኛ ህይወት የመምራት አላማቸውን ከዘነጉ፣ አነስተኛዋ አለመግባባት፣ በአፀፋ ምህዋር ትልቅ ፀብ ትሆናለች፣ ከዚያም «በቡድን ስሜት» እየጦዘች የቤተዘመድ ግጭት:: በበርካታ አገራት፣ የጥቂት ሰዎች

ጥቃቅን አለመግባባት፤ «በቡድናዊ ስሜት» እየጦዙ ነው፤ አሰቃቂ ጦርነትና ዘግናኝ እልቂት የሚቀሰቀሱት::

በአሳዎቹ ታሪክ፤ የጥቂቶች አለመግባባት፤ «በቡድናዊ ስሜት» ተጋግሎ ወደ ሽብርና ወደ ጦርነት ዘመቻ አምርቷል:: አሳዎቹ፤ በየጊዜው የሚበለፅግ ደስተኛ ህይወት የመጎናፀፍ አላማ ቢኖራቸው ኖሮ፤ ትምህርት ላይ፤ ስራና ምርታማነት ላይ በማተኮር ለጥረት ይነሳሱ ነበር:: አንዱ ብዙ ሲያመርት፤ ሌላኛውን በፉክክር መንፈስ እንዲበረታ የሚያነቃቃበት የስኬት ምህዋር በፈጠሩም ነበር::

ስኬትን ለስኬት በሚያበቃ (win - win) ምህዋር ውስጥ፤ አንዱ ለሌላኛው ገበያ ነው:: የአንዱ ስኬት፤ ለሌላኛው የምርት ገበያ ያሰፋለታል:: ኢንዱስትሪ ሲያድግ፤ እንደ ባንክ ለመሳሰሉ የፋይናንስ ተቋማት የእድገት ገበያ ይፈጥራል:: የፋይናንስ ተቋማት በስኬት ሲጠናከሩ፤ ለኢንዱስትሪ መስፋፋት የፋይናንስ ገበያው ይጨምራል::

የመበልፀግ አላማ ላለው አገር፤ ከሃብታም አገር አጠገብ መሆን ትልቅ እድል ነው። የአንዱ መበልፀግ፤ ለሌላኛው ገበያ ይሆናል:: በአፍሪካስ? በምርት የመበልፀግ አላማ ተዘንግቶ፤ ጎረቤትን ለማዳከም የመሞከርና ውድቀታቸውን የመመኘት አባዜ ጎልቶ ይታያል - «ድንበርንና መሬትን» ለመሻማት፤ «የተፈጥሮ ሃብት»ን ለመቀራመት:: እንደአሳዎቹ::

አሳዎቹ፤ የህይወት አላማቸውን ዘንግተው፤ የተረፈውን ምግብ የመሻማት ፉክክር ላይ ብቻ ነው በቁንፅል ያተኮሩት - zero sum game የሚባለው አይነት ውድድር:: አንዱ አሳ መብላት የሚችለው፤ ሌላኛውን እንዳይበላ በማድረግ ነው:: አንዱ ስኬትን ለማግኘት የሚሞክረው፤ በሌላኛው ውድቀት ላይ ብቻ ነው:: «ተቀናቃኝን መጣል» የሚል መፈክር ይተጋተጋሉ - «የውድቀት ፉክክር»።

በግዙፍነታቸው የተመኩ አንዳንድ ትልልቅ አሳዎች፤ የተራረፈውን ምግብ ለመብላት፤ ትንንሾቹን እያስፈራሩ አባረረዋል:: ስጋት የገባቸው አንዳንድ ትንንሽ አሣዎች፤ «የኛ ወገን በቁጥር ብዙ ነው» በሚለው መተማመኛ አፀፋውን መለሱ:: «ጂ99» በሚል ስያሜ የተደራጁ ትንንሽ አሳዎች፤ ማንኛውንም ትልቅ አሳ አድፍጠው በማጥቃት ሽብር ፈጠሩ:: በዚህ የጎሬላ ጦርነትና ሽብር ብዙ ትልልቅ አሣዎች ሞተዋል::

የተሸበሩና ጥቃት ያንገበገባቸው ትልልቅ አሣዎች፤ በቡድን ስሜት አዲስ የአፀፋ አፀፋ አዘጋጁ:: «ለምን በማስፈራራት ብቻ እናልፋቸዋለን፤ እንዋጣቸው!!» በማለት ዘመቻ አካሂደዋል:: በርካታ ጦርነቶች የሚቀሰቀሱትና የሚባባሱት በእንዲህ አይነት የመተጋተግ ምህዋር ነው::

የሌላው ወገን ውድቀት ላይ በማተኮር ከመተጋተግ ይልቅ፤ የየራሳቸው የህይወት አላማ በፅናት ቢይዙና፤ ለጦርነት የሚያወጡትን ሀይል ለምርታማነት ቢፎካከሩበት ኖሮ፤ እንደ ቅድመ አያቶቻቸው በሰላም በየጊዜው የሚበለፅግ ደስተኛ ህይወት ሲኖሩ አይችሉም ነበርን?

በሱማሌ ተወላጅነት የተቧደኑ ተማሪዎች «የኛ ሰው የተመታው እኛን ንቃችሁ ነው» በሚል ለፀብ ይነሳሉ:: እንዲህ እንዲህ እያለ ጡዘቱ ይቀጥላል...

የጡዘቱ ምክንያቶች ምንድናቸው?

1. በትምህርትና በእውቀት በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወት መቀዳጀት አላማቸው መሆን እንደሚገባው ስለዘነጉ፤ የብሽሽቅና የውድቀት ቁከከር ውስጥ ገብተዋል::
2. ጡዘቱን የሚያባብስ ሰበብ አግኝተዋል - የመንጋ አስተሳሰብን::
   - የብሄር፣ የሃይማኖት ቡድን መጠጊያና ዋስትና ሆኗል:: ከተቧደንክ፤ በቡድን ስም እንደፈለግህ መሆን ትችላለህ !
   - የግለሰብ ሀላፊነት ተረስቷል!
   - የት/ቤቱ አስተዳደርም እያንዳንዱን ተማሪ እንደየስራው ማስተናገድ፣ መምከርና መቅጣት ሲኖርበት፤ በቡድን ያስተናግዳቸዋል::

መፍትሄውስ?

አንድ ተማሪ በሰራው ጥፋት፤ በብሄር ተወላጅነት እየተሰላ ሌላው ተማሪ ባልሰራው ስህተት መቀጣት የለበትም። የአንድ ተማሪ እውቀትና የፈተና ውጤት፤ በብሄር ተወላጅነት ለሌሎች እንደማይከፋፈል ሁሉ፣ ጥፋት ሲፈፅምም ሃላፊነቱን በብሄር ተወላጅነት ወደ ሌሎች መጫንና መቅጣት የፍትህ ፅንሰሃሳብን የሚደመስስ ይሆናል:: እያንዳንዱ ሰው እንደየስራው የሚሸለምበትና የሚቀጣበት የፍትህ አስተሳሰብን በመገንባት ኋላቀሩን የመንጋ አስተሳሰብ ስናፈርስ፤ በብሄር የሚቧደኑ ጥቂት ሰዎች የጡዘት ምህዋር ለማባባስ የሚያገለግል ሰበብ ያጣሉ::

መፍትሄው ይሄ ብቻ አይደለም። ሰዎች የብሽሽቅና የውድቀት ምህዋር ውስጥ ገብተው የሚተጋተጉትና የሚናቆሩት፤ አላማቸውን ሲዘነጉ ነው። በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወት መቀዳጀት ዋነኛ አላማቸው መሆን እንደሚገባው ተገንዝበው፤ የስኬትና የብልፅግና ምህዋር እንዲፈጥሩ ማድረግ ይቻላል - በቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST)።

## በእውነታ ላይ የተመሰረተ ቅንብራዊ አስተሳሰብ፡ ለትክክለኛ የሰዎች ግንኙነት

‹ፊት አታሳዩት›› ሲባል በተደጋጋሚ ትሰማላችሁ:: የሰዎች ግንኙነት በጣም አስቸጋሪ ነው - በአገራችን:: ላይ ላዩን ስንመለከተው፤ ቀላል መስሎ ሊታየን ይችላል:: በእርግጥም አስቸጋሪ መሆን አልነበረበትም::

አንዳንድ ሰዎችኮ፤ ጓደኛቸው ትልቅ ስራ ሲሰራ፤ አላስፈላጊ አጣብቂኝ ውስጥ ይገባሉ:: «ትልቅ ስራ ስለሰራ ባደንቀው ጉረኛ ይሆንብኛል፤ ባላደንቀው ደግሞ ምቀኛ እንደሆንኩ እስቦ

# 5. የሁሉ የሆነ የማንም
# እኔ የሌለው እኛ፣ የእኔ የሌለው የእኛ
# (Tragedy of the Commons)

«ሁለት ሰዎች በድብቅ የህዝብ መናፈሻ ውስጥ ገብተው፣ አካባቢውን ሲያፀዱ ተገኙ» የሚል ዜና ሰምታችሁ ይሆን? «የህዝብ» ስለሆነ፣ በመናፈሻው ለመዝናናት ተሻምቶ የሚገባ ብዙ ይሆናል። አንዳንዱም ያለወረፋና ያለሰልፍ አታልሎ ለመግባት ይሞክራል። መናፈሻውን ለማፅዳት የሚሻማና የሚያታልል ግን አይኖርም። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ደግሞ ለመዝናናት የሚመጣም ይጠፋል - መናፈሻው በቆሻሻ ብዛት የአይጦች አርሻ ሆኗል።

«የሕዝብ ሜካ ውስጥ፣ ሁለት ሰዎች በሰውር ዛፍ ሲተከሉ ተያዙ» የሚል ዜናም አልሰማችሁም። በፍፁም! «ሲቆርጡ ተያዙ» የሚል እንጂ!! ለምን?

ነገሩ፣ «የቢፌው ጠረጴዛ ጣጣ» ይባላል። የቢፌ ድግስ ላይ ሰዎች መብላት ከሚችሉት በላይ በሳህናቸው ምን ያክል እንደሚከምሩ አይታችኋል። «ወረፋ ጠብቄ ከቢፌው ከማነሳ፣ ከንተ ሣህን ላይ ላንሳ» ብለው ጓደኞቻቸው እስኪያሾፉ ድረስ ማለት ነው።

የሁላችንም ቀለብ ከየቤታችን እየተሰበሰበ፣ ሁልጊዜ የጋራ ቢፌ እንዲዘጋጅና እንድንበላ ብንወስን፣ ምን እንደሚከሰት አስቡት። ለሸከም እስኪያስቸግር ድረስ ከቢፌው እያፈሰ የሚሄድ ሰው ይበራከታል። በሁለተኛው ወር ከየቤቱ የወር ቀለብ ለመሰብሰብ ስትሄዱስ? የሚሰበሰብ አታገኙም።

ቢፌው የጋራ ነው ቢባልም፣ የጋራ ሆድ ወይም የጋራ ጉርሻ ብሎ ነገር የለም። የየግል ነው። የሚበላና የሚጎረስ ነገር ለማግኘት ማምረትና መስራትም የግል ሃላፊነት ነው። መብላትና መስራት የግል ናቸው - እርስ በርስ የተሳሰሩ ተጠቃሚነትና ሃላፊነት። «የጋራ ቢፌ» ስንል ግን፣ መብላትንና መስራትን ይነጣጥላቸዋል። ከዚያስ? በቁንፅል በአሁኗ ቅፅበት ለተጠቃሚነት መሻማት፣ በቁንፅል በአሁኗ ቅፅበት ከሃላፊነት መሸሽ ይጀመራል።

ሁሉም ለቢፌው የሚሆን ነገር ለማቅረብ ሳይሆን፣ ከቢፌው ለማንሳት ነው የሚሻማው። ቢፌው የሁሉም ነው። ብዙም ሳይቆይ ቢፌው ባዶ ይሆናል።

እንዲህ አይነቱ የጋራ ብክነት፣ Tragedy of the Commons ተብሎ ይጠራል። የፅንሰሀሳቡ መነሻ፣ ፈረንጆቹ በየከተማው Commons በሚል ከሚከልሏቸው ቦታዎች ጋር የተያያዘ ነው። በኛ ሀገር green area ይሉታል። በአበባ አምረው፣ በሳርና በዛፍ አረንጓዴ የልምላሜ ቀለም

እንዲላበሱ የሚዘጋጁ ቦታዎች ናቸው።

በእርግጥ፣ በሁሉም ከተሞች የሚገኙ «ግሪን ኤሪያዎች» የሁሉም ስለሆኑ፣ ሁሉም ሰው ዛፍና አበባ ይተክልባቸዋል ማለት አይደለም:: ግን ብዙ ሰው ቆሻሻ ይጥልባቸዋል:: በግ ያሠማራባቸዋል እንጂ፤ ተሳስቶ ሳርና አበባ አይተክልም:: ለዚህም ነው፤ «ግሪን ኤሪያዎች» ስማቸው ብቻ እንጂ መልካቸው አረንጓዴ የማይሆነው:: አመዳማ ወይም ግራጫ ናቸው:: «ግሪን» ሳይሆን ብራውን::

አንድ ነገር «የጋራ ነው» ሲባል፤ ብዙውን ጊዜ የማንም ሳይሆን ይቀራል:: ሁሉም ሰው፤ «በጋራ ከተገኘው ነገር» እየቀነሰ ለመውሰድ ይሻማል እንጂ፤ «የጋራ ነው» የተባለው ነገር ሲጎድል፤ ለማሟላት የሚጨምር ብዙም አይኖርም:: በመጨረሻም ማለቁና መሞቱ አይቀሬ ነው::

በአሳዎቹ ታሪክ የተከሰተውም ይሄው Tragedy of the Commons ነው:: የአትክልት ማሳዎቹ የጋራ እንዲሆኑ ከተደረገ በኋላ፤ እፅዋት የሚተክል ጠፋ፤ ሁሉም አሣ የቻለውን ያህል ለመብላት ይሻማል:: «ያሊቃል» ብሎ በማሰብ የጎደለውን ለማሟላት የጣረና ለማምረት የሚሞክር ጠፋ:: ኃላፊነት የሚወስድ ባለመገኘቱ፤ አትክልቱ ቀስ በቀስ እያለቀ በመጨረሻም ሙሉ በሙሉ ስለተሟጠጠ አሳዎቹ ለአሰቃቂ ረሃብ ተዳርገዋል::

በአገራችን፤ ለዚህ በርካታ ምሳሌዎች አሉ:: የጋራ፣ የህዝብ ወይንም የመንግሥት በሚል ስም ተይዘው፤ «በጋራ ብክነት ምህዋር» የተተበተቡ የአገራችን ጉዳዮች ብዙ ናቸው - ደን፣ ወንዝ፤ ሃይቅ፣ ነፃ ሕክምና፣ ነፃ ትምህርት፣ የሙያ ማህበር፣ አንዳንዴም ኮሚቴ... እና ሌሎችም::

ደኖች፤ የሁሉም ዜጋ ንብረት ናቸው ስለሚባል፤ ማንም ሰው ዛፍ ይቆርጣል እንጂ አይተክልም:: ዛፍ መቁረጥ ቢከለከል እንኳ ተደብቆ ይቆርጣል:: ዛፍ ተከላ ግን በልመናና በትእዛዝም አይሳካም:: ስለዚህም ነው፤ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ከ40 አመት ባነሰ ጊዜ የአገሪቱ የደን ሽፋን ከ40% እያሽቆለቆ ወደ 3% የደረሰው:: የቢፌው ጠረጴዛ፤ ያነሱለታል እንጂ አይጨምሩበትም::

ወንዞችና ኃይቆች «የጋራ» ስለሆኑ፤ ሁሉም ሰው ውሃውን ይቀዳል፣ ከብት ያጠጣል እንጂ፤ በአፈርና ውሃ ጥበቃ ንፅህናው ተጠብቆ ለተሻለ ጥቅም እንዲውል የሚሰራ የለም:: በመጨረሻ ይቆሽሻል፤ ይበላሻል:: ያኔ፤ ማንም ሰው ውሃውን ለመቅዳትና ከብቶቹን ለማጠጣት አይችልም:: የሁሉ የሆነ፤ የማንም ሳይሆን ይቀራል:: ጭራሽ የበሽታ መንስኤ ይሆናል::

ኢትዮጵያ ውስጥ፤ በከፍያ ለመታከም አቅም የሌለው ሰው፤ ከቀበሌ «የነፃ ወረቀት» የሚባል ነገር ሲያመጣ በመንግሥት ጤና ድርጅት በነፃ መታከም ይችላል ይባላል:: ስለዚህም ደሀውም ሆነ መክፈል የሚችለው ሰው፤ «የነፃ ወረቀት» እየያዘ ይሄዳል:: ከዚያስ? በ«ነፃ የመታከም መብት» አለ፤መድኃኒቱ ግን አልቋል የሚል መልስ ያገኛል::

ከጋራ ብክነት ምህዋር (Tragedy of the Commons) ውስጥ ወጥመዱን ሰብረን መውጣት የምንችለው፤ «የጋራ ቢሌ» በሚል... መብላትንና መስራትን፤ ተጠቃሚነትንና ሃላፊነትን ነጣጥሎ በቁንፅል ለማየት መሞከርን ትተን፤ ትስስርና መስተጋብራቸውን ያገናዘበ አሠራር በመፍጠር ነው፡፡ «የጋራ» ተብለው የሚፈረጁ ነገሮች፤ በፍጆታ ሊያልቁ የሚችሉ ናቸው፡፡ ፍጆታን ብቻ ሳይሆን ምርትን፤ተጠቃሚነትን ብቻ ሳይሆን ሃላፊነትን፤ መሸምጠጥን ብቻ ሳይሆን መትከልን፤ መብላትን ብቻ ሳይሆን መስራትን፤ መውሰድን ብቻ ሳይሆን መክፈልን ያቀናጀ የህይወት ከህሎት ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡

በአንዳንድ ቦታዎች እንደተደረገው፤ በጋራ ብክነት የተራቆቱ ጋራዎችን፤ ነዋሪዎች ልክ እንደማሳ ተከፋፍለው በመውሰድ፤ ደን አልምተው እንዲጠቀሙ የሚያስችል ስርአት አንድ መፍትሄ ነው፡፡ ከማልማት ሃላፊነት ጋር ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ለዚህ አሰራር አመቺ ባልሆኑ አካባቢዎችም፤ አንድ ዛፍ ቆርጦ መጠቀምንና፤ 10 ዛፍ ተክሎ የመንከባከብ ሃላፊነትን ያስተሳሰረ አሰራር መሞከር ይቻላል፡፡

«ቢጋራ ብክነት ምህዋር» የተተበተበው «የነፃ ሕክምና» ስርአትም መፍትሄ ያስፈልገዋል፡፡ «ነፃ ህክምና»፤ ለስሙ እንጂ ከምር ነፃ አይደለም፡፡ ታካሚው ባይከፍል እንኳ፤ የሆነ ሰው፤ የሆነ አካል፤ መንግስት ወይም ኤንጂኦ ወጪውን ይሸፍናል ተብሎ ስለሚጠበቅ ነው፤ «ነፃ» የሚመስለው፡፡ ከሁሉም በፊት፤ ይህንን እውነታ በግልፅ ማወቅና ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ አለበለዚያ በነፃ የሚገኝ የጋራ ህክምና፤ እንደ ቢሌው ከቆይታ በኋላ መራቆቱ አይቀርም፡፡

ሌሎች ኢትዮጵያዊ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ «የጋራ ብክነት አዙሪቶች» Tragedy of the Commons አሉ፡፡ የሴቶችና የልጆች መብት አለመከበር፤ ሙስና፤ ግጭትና የመሳሰሉ ችግሮች፤ እንዲሁ በደፈናው «የህዝቡ የጋራ ጉዳይ ስለሆኑ፤ መፍትሄያቸውም የጋራ ሃላፊነት ነው» ይባላል፡፡ ነገር ግን መፍትሄ ለመፈለግ የሚደረግ ጥረት ብዙም አይታይም፡፡ በተቃራኒው፤ የ«ምን አገባኝ!» ወረርሽኝ ነው የተፈጠረው፡፡

በቅንብራዊ አስተሳሰብ (በሲስተም ቲንኪንግ) መሰረት፤ እንዲሁ በደፈናው «ያገባኛል»፤ በደፈናው «አያገባኝም» የሚሉ ሃሳቦችና ስሜቶች ስህተት ናቸው፡፡ «የትኛው ጉዳይ፤ ማንን፤ እንዴት እና እስከ ምን ድረስ ያገባዋል?» ብለን መጠየቅ ይኖርብናል፡፡ የነገሮችን ትስስርና መስተጋብርን በመዘንጋት፤ «የጋራ ጉዳይ ነው፤ ሁሉም ያገባዋል፤ የህዝብ ሃላፊነት ነው» ወደ ሚል ድፍን ድምዳሜ መድረስ ዋጋ የለውም - ቢጋራ ከመባከን በስተቀር፡፡

ለምሳሌ ሙስናን እንመልከት፡፡ (ሙስና፤ ለሌብነት የወጣለት አዲስ የብዕር ስም) ይመስለኛል፡፡ ያው ሙሰኛ ማለት፤ የሠረቀ ወይም ያሰረቀ፤ የዘረፈና ያዘረፈ ሌባ ነው!)፡፡ እና የሙስና ጉዳይ ያገባናል? እያንዳንዱ ዜጋ ያገባዋል? የንግድ ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራት ያገባቸዋል? ፓርላማ፤ ምክር ቤቶች፤ ፍ/ቤቶች፤ ፖሊስና አቃቤ ህግን ጨምሮ ሌሎች የመንግስት ተቋማት ያገባቸዋል? እንዴት? እስከ ምን ድረስ?

አንድ የቢዝነስ ተቋም ሰራተኞችን ሲቀጥር፤ ኀበዝና ታታሪ አመልካቾችን ትቶ፤ የወንድም የአክስት ልጆቹን ቢቀጥርና፤ ከሌሎች ሰራተኞች የበለጠ ደመወዝ ቢከፍላቸውስ? አንድ ስራ ፈላጊ ሰው ይህንን ሲያውቅ፤ «መጥፎ ተግባር ነው» ብሎ በመፀየፍ ወደ ሌላ የስራ እድል ፊቱን ያዞራል - እዚህ ድረስ «ያገባዋል»:: ታታሪ ሰራተኞችን ትቶ በዝምድና ከሚቀጥር ቀሽም ድርጅት ጋር ንግድ አላካሂድም የሚል የቢዝነስ ሰውም ይኖራል - እዚህ ድረስ «ያገባዋል»::

የቅጥር እድልዎ የተፈፀመው በመንግስት ተቋም ሃላፊ ቢሆንስ? አንድ ግለሰብ ይህን አይቶ፤ ከመፀየፍና ከመጠቆም የዘለለ ሚና ላይኖረው ይችላል:: ፖሊስ ግን የደረሰውን ጥቆማ ይዞ፤ በህግ በተሰጠው ስልጣን መመርመርና ለአቃቤ ህግ አሳልፎ እስከ ማስከሰስ ድረስ ኃላፊነት አለበት:: የመንግስት ተቋማትም፤ ለሙስና የማይመች አሠራር መትከልና አዲት ማስደረግ የመሳሰሉ ተቋማዊ ስርአትን አስቀድሞ የማበጀት ግዴታ አለባቸው:: ፓርላማና ምክር ቤቶችም፤ የመንግስት ተቋማትን በመከታተል፤ የአገሪቱ ህጎች ለሙስና በር የማይከፍቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው ሃላፊነታቸው::

የትኛው ጉዳይ፤ ማንን እንዴትና ምን ድረስ እንደሚያገባው፤ በማስተሳሰር በዝርዝር አቀናጅተን ካላሰብን፤ የተለመደው አይነት የድግስ ግርግር ይሆናል::

የሰርግ ይሁን የኮንሰርት ዝግጅት፤ በታቀደለት ሰአት ሲጀመር ማየት ለአገራችን ብርቅ ነው:: እንዲሁ በደፈናው፤ ቤተሰብ፤ ቤተዘመድ፤ ጓደኛና ጎረቤት በጋራ ተባብረው ድግሱን እንደሚያዘጋጁ ይታሰባል:: በቃ:: ስራው ግን አይከናወንም:: እያንዳንዱ ሰው፤ «ሌሎቹ ያከናውኑታል» እያለ፤ ስራው ሳይከናወን ይቀራል:: ባለቀ ሰአት፤ «አንትን የለም፤ እንትን አልደረሰም...» እየተባለ፤ ለ7 ሰአት የታቀደው ግብዣ፤ 9 ሰአትም አይጀመርም። ዝግጅቱም ስርአት የለሽ ይሆናል:: በደፈናው፤ «የጋራ ስራ ነው» የተባለ ነገር፤ በማንም ሳይከናወን ይቀራል (በጋራ ገሸሽ ይደረጋል)::

ኃላፊነትን በትክክል ለይቶ፤ በዝርዝር 1,2,3 ብሎ ማስቀመጥ፤ ለብዙዎች «አለርጂክ» ነው:: ልብ በሉ፤ የጎዳና ህፃናትን ወይም በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ልጆችን መንከባከብ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃላፊነት ነው ሲባል ሰምታችኋል:: ለዚያውም በተደጋጋሚና ለአመታት:: ግን ህፃናትና ልጆች እንክብካቤ አገኙ? «የሁሉም ሃላፊነት ነው» የሚል ድፍን ድምዳሜ፤ ግዙፍ የብዥታ ስዕል ከመፍጠር ውጭ ምንም አይነት ተጨባጭ ጥቅም ሰጥቶ አያውቅም::

እውነታውን ተቀብለን፤ እውነት እንነጋገር ከተባለ ግን፤ ሁሉም ልጅ ወላጅ አለው:: ሲቀጥልም ዘመድ ይኖረዋል:: ጎረቤት ወይም ወዳጅም አያጣም:: ከወላጅ ቀጥተኛ ሃላፊነትና ግዴታ ጀምሮ፤ በየደረጃው በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሌሎቹ ኃላፊነት በግልፅ ተዘርዝሮ መታወቅ አለበት። ይህ አልበቃ ካለም፤ የሌላው ዜጋ ተሳትፎና በረድኤት ድርጅት በኩል የሚደረጉ እገዛዎችን ጨምሮ 1,2,3, ተብሎ ሲቀመጥ ይገባል:: እለበለዚያ፤ እንዳለፉት አመታት፤ ወደፊትም በደፈናው «የሁሉም የጋራ ሃላፊነት» እያልን በጋራ የብክነት ምህዋር ተጨማሪ ምእተአመት እንደፍናለን::

ECMAP

ከተማችንን ማፅዳት «የሁላችንም ግዴታ ነው» የሚለው መፈክር፤ የጋራ ንፅህናን አልፈጠረም። በተቃራኒው፤ የግል ቆሻሻን የጋራ የማድረግ ልምድ ተስፋፍቷል:: ሁሉም ሰው፤ በየራሱ ቤት ለሚፈጥረው ቆሻሻ ወላጅ መሆኑን አውቆ፤ ቆሻሻውን በአግባቡ የማስወገድና የማፅዳት ሃላፊነት እንዳለበት መቀበል ይኖርበታል - ቢፈልግ ኢቃጥሉ፣ ከተመቸው በሪሳይክሊንግ፣ ከቻለ ቆሻሻ ለሚሰበስቡ ከፍሎ:: ይህ ግልፅ ሃላፊነት፤ «የጋራ ሃላፊነት» በሚል ብዥታ ሲድበሰበስ፤ ቆሻሻውን አደባባይ ላይ እየጣለ፤ የጋራ ቆሻሻ የሚፈጥር ይበራከታል - በጋር ብክነት አዙሪት።

አገራችን፤ እንዲህ በጋራ ብክነት አዙሪት የተሞላች ትመስላለች:: ሁሉም ዜጋ የአገሩን ባህልና ታሪክ መንከባከብና ጠብቆ ማቆየት አለበት ተብለናል - በደፈናው::

1ኛ ነገር፤ የትኛውን ባህል? የመከባበር ባህል ወይስ የጦርነት ባህል፤ ትምህርትን የማወደስ ባህል ወይስ በጥንቆላ የማመን ባህል፤ የስራ ባህል ወይስ የሽፍትነት ባህል?

2ኛ ነገር፤ ባህል መጠበቅና መንከባከብ ለምን? ጥቅምን ለማሳደግ ወይስ ጉዳትን ለማባባስ? ከጥንቱ ተምሮ ወደ ስልጣኔ ለመገስገስ ወይስ ከመጪው ጊዜ ሸሽቶ ወደ ኋላ ለመንተት?

3ኛ ነገር፤ የማን ሃላፊነት እስከ ምን ድረስ ነው?

«እኔ፤ ይሄኛው ባህል ጠቃሚ ስለሆነ አከብሬ አዳብረዋለሁ:: ያኛው ባህል ግን ጎጂ ስለሆነ አልንከባከበውም:: መጥፎ የሆኑ በርካታ ባህሎች ስላሉ፤ ሁሉንም በጥቅሉ አልደግፍም» ብልስ? ምክንያቱም ባህል በሚል ስያሜ የሚወደሱ ብዙ ድርጊቶችና የአኗኗር ዘይቤዎች፤ በጣም ጎጂና መጥፎ ልማዶች ናቸው:: ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ተቃራኒ በሆነ መንገድ፤ ህይወትን ከማጎሳቆልና ከማሰቃየት በተጨማሪ፤ በጉልበት ሰብዓዊ መብት እንዲጣስ ያደርጋሉ:: እንዲያውም አንዳንዶቹ በአገራችን ህጎች ውስጥ ወንጀል ሆነው የተመዘገቡ ናቸው::

በደፈናው «ባህልን መንከባከብ የሁሉም የጋራ ሃላፊነት ነው» በማለት የጋራ ብክነት አንፍጠር:: ፈቃደኝነትና ጥቅምን መሰረት በማድረግ በግልፅ የተዘረዘረ፤ ግብን ከሃላፊነት የማይነጣጥል የተቀናጀ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል::

ለምን ይመስላችኋል፤ የጋራ ብክነት አዙሪት በኢትዮጵያ የተንሰራፋው? የእንድን ሃሳብ ትክክለኛነት ሳይመረምር፤ የአንድን ባህል ጠቃሚነት ሳያመዛዝን፤ እንዲሁም የእያንዳንዱን ሰው ፈቃደኝነት ሳይጠይቅ፤ «በጋራ ይህን ሃሳብ ተቀበሉ፤ በጋራ ይህን ባህል ተንከባከቡ፤ በጋራ ሃላፊነት ተሸከሙ» የሚል ጋርዮሻዊ አስተሳሰብ በሰፊው ስለሰፈነ ነው - ሰውን ከመንጋ ጋር የሚያመሳስል አስተሳሰብ::

ትክክለኛ የሆኑ አዳዲስ አስተሳሰቦችን ሃሳቦችን መርምረን እንዳንቀበል፤ ጠቃሚ የሆኑ አዳዲስ ስርአቶችንና አሰራሮችን አመዛዝነን እንዳንተገብር፤ ስልጡን አኗኗርንና ባህልንም አገናዝበን እንዳናዳብር ጋሬጣ እየሆነ ያለውም ጋርዮሻዊ አስተሳሰብ ነው:: ከኛ የተለየ ሃሳብ፤

# 6. ላለው ይጨመርለታል ለሌለውም... ያው ማጣት ይጨመርለታል (Success to the Successful)

የአሜሪካ ኢኮኖሚ በአመት፤ 3.6 በመቶ ሲያድግ፤ ከአምናው በ500 ቢሊዮን ዶላር የሚበልጥ ተጨማሪ ሃብት ይፈጠራል፡፡ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአመት 10 በመቶ ሲያድግ፤ ከአምናው በ2 ቢሊዮን ዶላር የሚበልጥ ተጨማሪ ሃብት ብቻ ይፈጠራል፡፡ ለምን? ላለው ይበልጥ ይጨመርለታላ፡፡ አሜሪካ ውስጥ ኢንቨስት የሚያደርጉ ሰዎችና ድርጅቶች፤ ይበልጥ ስኬታማ በሆኑ ቁጥር፤ እንደገና ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን ይስባሉ፡፡ ስኬትን ስኬት ይከተለዋል፡፡

በርካታ ሰዎች ከአነስተኛ ደረጃ ተነስተው ቀስ በቀስ እየተሻሻሉ፤ ከትንሽ ጊዜ በኋላ በፍጥነት ሲመጠቁ የምናየውስ ለምንድነው? ላለው ይበልጥ ስለሚጨመርለት፡፡ በመጀመሪያ አንድ ደንበኛ ያገኝና፤ በጥራትና በብቃት ያስተናግደዋል፡፡ ደንበኛው በዚህ ተደስቶ፤ ለሌሎች ሰዎችም ይናገራል፡፡ በሚቀጥለው ጊዜ ሁለት ተጨማሪ ደንበኞች ያገኛል፡፡ እንደገና ሁለቱ ደንበኞች በስራው ተደስተው፤ አራት ተጨማሪ ደንበኞችን እንዲያገኝ መነሻ ይሆኑለታል፡፡ በእርግጥ በዚህ ጊዜ፤ የስኬት ጉዞው ፍጥነት ጎልቶ አይታየን ይሆናል፡፡ መጀመሪያ ላይ 1 ብቻ፤ በቀጣዩ ወር 2፤ በቀጣዩ ወር 4... ከዚያም 8፤ ከዚያም 16፤ 32፤ 64፤ 128፤ 256፤ 512፤ 1028 ... በአስራ ሁለተኛው ወር፤ 2056 ... አሁን የስኬት ግስጋሴው በጣም ጎልቶ ይታየናል፡፡ ጭማሪው እየበዛ ይሄዳል።

የሆነ ነገር ለማሰራት ስናቅድ ምን እናደርጋለን? በዚያ የቢዝነስ መስክ፤ «አቅምና ብቃት አሟልቷል» ብለን ወደምናምንበት ስኬታማ ድርጅት እንሄዳለን፡፡ የማናውቅ ከሆነም፤ «ስኬታማ ነው» የሚባል ድርጅት እንዲጠቁሙን ሰዎችን እያጠየቅን እንሄዳለን፡፡ ስኬታማው የቢዝነስ ድርጅት፤ አንድ ተጨማሪ ቢዝነስ አገኘ ማለት ነው፡፡

በድርጅቱ ስራ ከተደሰትን ቋሚ ደንበኛው ከመሆንም አልፈን፤ የማያውቅ ሰው ሲጠይቀንም ጥቆማ እንሰጣለን፡፡ ድርጅቱ እንዲህ ተጨማሪ ቢዝነስ እየገረፈለት፤ በትርፋማነት ራሱን፤ መሳሪያዎቹንና አገልግሎቱን ለማሻሻል የሚያስችል ተጨማሪ አቅም ስለሚያገኝ፤ ተጨማሪ ደንበኞችን ይስባል፡፡ ላለው፤ ይበልጥ ይጨመርለታል፡፡

በአንድ ፋብሪካ ውስጥ የተቀጠረ ሰራተኛ፤ መጀመሪያ ላይ የስራ ፍቅርና ትጋት፤ የስራ ጥራትና ቅልጥፍና በማሳየት ብቃቱን ለማስመስከር ጊዜ ይወስድበታል፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ግን፤ በፍጥነት እየገነነ ይሄዳል፡፡ ብቃቱን ሲያስመሰክር፤ የስራና የደመወዝ እድገት ይሰጡታል፡፡

መንገድ ከተጀመረ፣ ጉዞው እየተመቻ ይሄዳል፡፡ ለዚህም ነው፣ በሆነ አመት ከየክፍላቸው ከ1-3 የሚወጡ ተማሪዎች በዚያው የስኬት ጎዳና እስከ መጨረሻ ሲሄዱ የሚታዩት፡፡

ስኬታማ በሆንክ ቁጥር፣ አለም ሁሉ ለተጨማሪ ስኬት አብሮህ ይሰራል ቢባል ብዙም የተጋነነ አይደለም፡፡ እዚህ ላይ ሁለት ነጥቦችን እናንሳ፡፡

አንደኛ፣ «ስኬት ለስኬታማ» የሚባለው ነገር፣ ከላይ በተገለፀው መንገድ ሲታይ፣ ተገቢና ፍትሃዊ መርህ ነው - ሰነፍ ተማሪዎችን እየሸለምን እናድንቅ ካልተባለ በቀር፡፡ ሁለተኛ፣ ብቃትንና ስኬትን በማስመስከር፣ ከዚህ ፍትሃዊ መርህ ማግኘት የምንችለውን ተጨማሪ ስኬትና ጥቅም ለመቀዳጀት ሁልጊዜ ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል - በደካማነትና በውድቀት ለመሸለም እስካልተመኘን ድረስ፡፡ እነዚህን ቁምነገሮች ቸል ካልናቸው ግን ችግር እንፈጥራለን፡፡

እያንዳንዱን ስኬት፣ እንደገና ለተጨማሪ ስኬት እንደመሳሪያ ለመጠቀም ዝግጁ ካልሆንን፣ ለውድቀት እንዳረጋለን (ይህንንም፣ «የስኬት ገደቦች» እና «ኢንቨስትመንትን የዘነጋ ስኬት» በሚሉ ርእሶች ስር እንመለከተዋለን)፡፡ አሁን ሌላኛው ችግር ላይ እናተኩራለን፡፡

«ስኬት ለስኬታማ» የሚለውን መርህ፣ ከላይ በተገለፀው መንገድ ሳይሆን፣ «ስኬት፣ ለስኬታማ መሳይ» በሚል ትርጉም ተግባራዊ የሚያደርጉ ሰዎች በርካታ ናቸው፡፡ እናም ፈፅሞ ፍትሃዊ ያልሆነ የውድቀት ምህዋር ይፈጥራሉ፡፡

## ስኬት ለስኬታማ መሳይ

አትሌቶች ለአለማቀፍ ውድድር የሚመረጡበት አሰራር ሁሌ እንደሚያጨቃጭቅ ሰምታችሁ ይሆናል፡፡ ከጭቅጭቅም አልፎ፣ እስከ መታኮስ የተደረሰበት ጊዜም አለ፡፡ የአንዳንዱ ጭቅጭቅ መነሻ ምክንያት፣ ከተራ አለመግባባትና ከተራ ፀበኛ ባህርይ ያላለፈ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን፣ «ስኬት፣ ለስኬታማ መሳይ» የሚል ኢፍትሃዊ አሰራርም፣ የጭቅጭቅ መነሻ ይሆናል፡፡

ብቃቱን ያስመሰከረ ስኬታማ አትሌት፣ በአለማቀፍ መድረክ እንዲወዳደር መመረጥ አለበት - ለተጨማሪ ስኬት፡፡ ይህን ፍትሃዊ መርህ ተግባራዊ ለማድረግም፣ በቅድሚያ ብቃትን በተጨባጭ መመዘኛ የምንለካበት የስሌት ዘዴ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በአገራችን ግን «ተጨባጭ መመዘኛ» እና «የስሌት ዘዴ» የሚባሉ ነገሮችን ብዙም አንጠቀምባቸውም።

ከ«ተጨባጭ መመዘኛ» ይልቅ፣ በሰዎች ስሜታዊ አስተያየት በጭፍን መነዳት፣ የህዝብን ስሜታዊ እምነት በጭፍን መከተል የተለመደ ነው፡፡ «የስሌት ዘዴ»ን ትተን፣ በ«መሰለኝ፣ ደሳለኝ» ወይም በ«መሰለኝ፣ ቅርአለኝ» መመራትን እናዘወትራለን፡፡

ስለዚህ፣ የአትሌቶችን ብቃትና ስኬታማነት፣ በተጨባጭ መመዘኛ በስሌት ታውቆ ምርጫ መካሄድ ሲገባው፣ «እገሌ ብቃት ያለው መሰለኝ፣ ቢመረጥ ደስ ይለኛል»፣ እገሊት ስኬታማ አትመስለኝም፣ ብትመረጥ ቅር ይለኛል»፣ «እንቶኔ በህዝብ ይጠበቃል»፣ «እንቶኒት፣ ብዙ

ሰዎች ያደንቋታል» ... እየተባለ ምርጫ ሲካሄድ አሰቡት፡፡

ከፍተኛ ብቃት ያለው «አትሌት ሀ» ሳይመረጥ፤ ከሱ በታች የሆነ «አትሌት ለ» ለውድድር ይመደባል፡፡ በስኬት የላቀች «አትሌት መ» ቀርታ፤ ከሷ ዝቅ ያለች «አትሌት ሰ» ለውድድር ትሄዳለች፡፡ እንዲህ አይነቱ ስህተት በፍጥነት ካልታረመ፤ «ስኬት ለስኬታማ» የሚለው መርሀ ኢፍትሃዊ የውድቀት ምህዋር ይሆናል፡፡

መነሻውን ተመልከቱ፡፡ ከእውነታው በተቃራኒ፤ አትሌት ለ ከአትሌት ሀ ይበልጣል በሚል ጭፍን ስሜት ነው የጀመርነው፡፡ በዚህም ምክንያት አትሌት ሀ፤ የስኬትና የመታየት እድል ተነፍጎታል፤ ሽልማት አያገኝም፤ ወደሌሎች አለማቀፍ ወድድሮች አይጋበዝም፡፡ አትሌት ለ ግን፤ ቢያንስ በአለማቀፍ ውድድር የመታየት እድል አገኘ፤ ማጣሪያውን ካለፈ ወደ ሌሎች አለማቀፍ ውድድሮች ይጋበዛል፤ ሽልማቶችንና ክፍያዎችን ያገኛል፡፡

ይህን ሁሉ ስንመለከት፤ «አትሌት ለ፤ ከአትሌት ሀ ይበልጣል» የሚለው ስሜታችን ይጠናከራል፡፡ እንደገና ከቀድሞው በበለጠ ሁኔታ፤ ለተጨማሪ ውድድሮች ቅድሚያ ያገኛል፡፡ ምህዋሩ እንዲህ ይቀጥላል - ስህተታችንን ካላረምን በቀር፡፡

በፋብሪካ ለሰራተኛ እድገት ለመስጠት ስናማርጥ፤ በንግድ አገልግሎት ዘርፍ አከፋፋይ ስናፈላልግ፤ እቃ ለመግዛት ስናነፃፅር፤ ስኮላርሺፕና ሽልማት ለመስጠት ተፎካካሪዎችን ስናወዳድር... ሁሌም በተጨባጭ መመዘኛ በስሌት እውነታውን ለማወቅ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡

ሰራተኞችን ስንመዝን ከአበበ ይልቅ ከበደ የሚበልጥ ይመስለኛል በሚል የተሳሳተ ስሜት፤ ተማሪ ቢ ከተማሪ ኤ እንደምትበልጥ ሰምቻለሁ በሚል የሰዎች ግፊት፤ ዝቅ ላለው ሰራተኛ እድገት ከሰጠን፤ የበታች የሆነችውን ተማሪ ከሸለምን፤ ለውድቀት ምህዋር መነሻ እንሆናለን - «ስኬት፤ ለስኬታማ መሳይ»፡፡

በግል እና በድርጅት ብቻ ሳይሆን፤ በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ የሚፈፀሙ ተመሳሳይ ችግሮችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ቤተሰብ እንዲሁም ማህበረሰቡ፤ ሴት ልጆችን ከወንድ ልጆች አሳንሶ ያያል፡፡ «ወንድ ከሴት ይበልጣል» የሚለው ጭፍን እምነትና ስሜት ምን እንደሚያስከትል ተመልከቱ፡፡ ወንድ ልጆች እንዲማሩና እንዲያድጉ የምንሰጠውን ያህል ድጋፍ፤ ለሴቶች አንሰጥም፡፡ «ሴት ብትማር የት ትደርሳለች? አንቺ ባል አታጪም፤ ወንድምሽ ይማር» እንላለን፡፡

የትምህርትና የእድገት ድጋፍ ካገኙት ወንዶች መካከል ከፊሎቹ ስኬታማ ይሆናሉ - ድጋፍ ካላገኙት ሴቶች ይልቅ፡፡ ይህን በማየትም «እውነትም ወንድ ከሴት ይበልጣል» እንልና ይበልጥ ለወንድ ልጆች ብቻ ትኩረት እንሰጣለን፤ ሴቶችን ይበልጥ ዝቅ የሚያደርጉ ተግባራትም ይጨምራሉ፡፡ ምህዋሩ ይቀጥላል። ወንድ ከሴት ይበልጣል የሚለው ጭፍን እምነትና ስሜት

ይበልጥ ይጠናከራል፤ «ተፈጥሮአዊ ህግ» እስኪመስል ድረስ። «ስኬት ለስኬታማ» የሚለው መርህ በተሳሳተ መንገድ ሲተረጎም፤ ይህንን ይመስላል።

በትክክለኛው መንገድ ግን፤ «ስኬት፤ ለስኬታማ» የሚለው መርህ፤ ሁላችንም በጥረት ብቃታችንን እየገነባን ስኬትን በተቀዳጀን ቁጥር፤ ወደ ላቀ ተጨማሪ ብቃትና ከፍ ወዳለ ተጨማሪ ስኬት እንድንረማመድ የሚያስችል ነው። የአንዱ ስኬት በሌላው ውድቀት፤ የአንዱ ትርፍ በሌላው ኪሳራ የሚመጣ አይደለም። ሁሉም የብቃቱንና የስኬቱን ያህል ተጨማሪ ብቃትና ስኬትን እውን ማድረግ ይችላል።

«ስኬት፤ ለስኬታማ»፤ በተሳሳተ መንገድ ሲተረጎም ግን፤ ስኬታማ መሳዮች ናቸው ትርፍ የሚያገኙት፤ በሌሎች ኪሳራ። «የመበላላትና የመጠፋፋት ስኬት» ሊባል ይችላል። እንዲህ አይነት «ስኬት» ምን እንደሚመስል፤ በአሣዎቹ ታሪክ አይተናል።

«ምግብ በማምረት ስኬታማ እንሆናለን» ብለው ከማሰብ ይልቅ፤ የወዳደቀ ምግብ ለመለቃቀም መሻማትን የመረጡ ትልልቅ አሳዎች፤ «ትንንሽ አሳዎች ቁጥራቸው እየተበራከተ ብዙ ምግብ ስለሚፈጁ ጠላቶቻችን ናቸው» ብለው አምነዋል። በግዙፍነታቸው ተማምነው ትንንሽ አሳዎችን እያሳደዱ ለመብላት የዘመቱ ትልልቅ አሣዎች፤ ይህንን እንደ ስኬት ቆጥረውታል። ምግብ የሚሻሙ ትንንሽ አሳዎችን ለማጥፋት እያሳደዱ ሲሰለቅጧቸው፤ የትልልቆቹ አሳዎች ጉልበት ይጨምራል፤ በዚህም ዘመቻቸውን ያጠናክራሉ - ስኬት ለስኬታማ መሳይ።

«ትልልቅ አሳዎች፤ ሆዳቸው ሰፊ ነው፤ ብዙ ምግብ ይጨርሳሉ» በሚል የጥላቻ ስሜት የተቧደኑ ትንንሽ አሳዎችም፤ እያሸመቁ ጥቃት ይሰነዝራሉ - ትልልቅ አሳዎችን ለማደልና ለማቦጨቅ። ሙከራቸው በተሳካ ቁጥር፤ ትንንሾቹ አሳዎች እየጠገቡ ይዋለዳሉ፤ ቁጥራቸው ይበራከታል፤ ጥቃታቸው ይጠናከራል - ስኬት፤ ለስኬታማ መሳይ።

ከዚያስ... እርስበርስ በመበላላትና በመቦጫጨቅ ይጨራረሳሉ። እንዲህ በተሳሳተ መንገድ፤ «ስኬት ለስኬታማ» የሚለው መርህ ተግባራዊ ሲሆን፤ መጨረሻው ውድቀት ነው። በሌሎች ውድቀትና ኪሳራ ላይ የተመሰረተ ስኬትና ትርፍ አያዛልቅም።

አንደኛ፤ ሌላኛውም ወገን አፀፋውን ይመልስና አዙሪቱ ይከርራል፤ የጡዘት ምህዋር (ኤስካሌሽን) ይሆናል። ሁለተኛ፤ ሌሎች ሁሉ ሲከስሩና ሲወድቁስ? ያኔ አከሰረን የምናተርፍበት ባለንብረት፤ ጠልፈን የምንጥለው ቋሚ አካልአይኖርም።

ከዚህ የጥፋት አዙሪት ለመላቀቅ፤ መፍትሄው ቀላል ነው - «ስኬት መሳይን» ትተን፤ «እውነተኛ ስኬት» ላይ ማተኮር። ያኔ «ስኬት፤ ለስኬታማ» የሚለው መርህ፤ በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች የህይወት ምህዋር ይሆንልናል።

ነገር ግን፤ ይህን መፍትሄ የሚያደናቅፉ ጭፍን አስተሳሰቦችና ሃሳቦች አሉ። ለብዙ ዘመናት የተጠናወቱን በመሆናቸው አደገኛነታቸውን ተገንዝበል ነቅለን ልንገላግላቸው ይገባል።

ከእነዚህም መካከል ጥቂቶችን ተመልከቱ፡፡

1. አንዱ የሚሳካለት የግድ በሌላው ውድቀት ምክንያት ነው!

2. እኔ እንድኖር እርሱ መሞት አለበት!

3. ሳትቀደም ቅደም፣ ሳይበላህ ብላ!

4. ህይወት ሁሌም የሞት ሽረት ውድድር ነው!

እነዚህና ተመሳሳይ ሃሳቦች፤ አካባቢያችንንና ሌሎችን ሰዎች እንደ ጠላት እንድናይ ያደርጋሉ - በጭፍን አስተሳሰብ፡፡ አዲሱ አስተሳሰብ ግን፤

1. መወዳደር ብቻ ሳይሆን መተባበርም ይቻላል፡፡ በዚህም ብቻችንን መፈፀም የማንችለውን በጋራ መፈፀም እንችላለን፡፡

2. ሀብታም ሀብታም የሚሆነው በራሱ አእምሮ በሚያዳብረው ብሩህ አስተዋይነትና የጠራ አስተሳሰብ፤ በሚጨብጣቸው ግንዛቤዎችና በሚያደራጀው የእውቀት ትስስር፤ በትክክለኛ የአላማ ፅናትና የእቅድ ጥራት፤ በሚያካብተው ሙያዊ ልምድና በሚያካሂደው ብርቱ ጥረት ነው፡፡ አስተውሎ፤ አገናዝቦ፤ አመዛዝኖ፤ አቅዶ፤ አርሶ፤ ዘርቶ፣ ኮትኩቶ፣ አጭዶ... በአጠቃላይ አምርቶ ሃብታም ይሆናል፡፡ ከደሃው በዝብዞና ዘርፎ ነው ከሚለው ሌኒናዊ ሀንገሽር እንጠንቀቅ፡፡

3. ሀብት ማለት፤ የሆነ ቦታ ተከማችቶ የተቀመጠ ነገር ነው፤ሰውም ለመሸምጠጥና ለመዝገን እንዲሻማ፣ እንዲዋጋ ወይም እንዲበላላ የተፈጠረ እንስሳ ነው የሚል አስተሳሰብና አኗኗር፤ የ«ሀንተር ጋዘረር» የጋርዮሽ ኋላቀርነትና የእንስሳት ባህሪ ነው፡፡ ሀብት ማለት ምርት ነው፡፡ እራሳችን በአእምሯችን አስበን የምንፈጥረው፤ ጊዜያችንና ጉልበታችንን ዘርተን በትዕግሥት ኮትኩተን የምናሳድገው የራሳችን «ልጅ» ነው - ሃብት፡፡ ቢል ጌትስ ቢሊየነር የሆነው፤ የማንንም ሀብት ዘርፎ አይደለም፡፡ እንዲያውም፤ ሌሎችንም ቢሊየነር የሚያደርግ ምርት ፈጥሯል፡፡

በአካባቢያችን ለሺህ ዓመት የተቀመጠ መሬትና ወራጅ ወንዝ፤ ሃብት ሊሆኑን ስላልቻሉ እንራባለን፡፡ አንድ ታታሪ ገበሬ ወይም ኢንቨስተር፤ ወንዝ ጠልፎ መሬቱን እያለማ እህል ወይም ከብቶች በብዛት ሲያመርት፤ ያኔ ሃብት ፈጠረ ይባላል፡፡ ሚሊዮነር የሚሆነው እያመረተና እየሸጠ እንጂ፤ ከአካባቢው ሰዎች እየዘረፈ አይደለም፡፡ በተቃራኒው ለአካባቢው ብዙ የሥራና የገበያ እድል እንዲበረከት፣ በአርአያነትም የሥራ ባህል እንዲፈጠር እያደረገ በመሆኑ መደነቅ ይኖርበታል፡፡

በአስተዋይነት፣ በአላማ ፅናትና በብርቱ ጥረት ስኬትን እውን ያደረገ ሰው፣ እንደገና ተጨማሪ ስኬት ይጠብቀዋል፡፡ የስኬት መሰረትን እንዲሁም «ስኬት ለስኬታማ» የሚለውን

ስኬትን እያስከተለ ይመነደጋል፡፡ ሳለው ያለመርሳታል ነው፡፡

እስቡ፡ የስኬቱ ምክንያት ተግቶ መሥራቱ እንጂ ዕድሉ አይደለም፡፡ ሰውዬው ይህን እውነት በመገንዘብ፡ በራሱ አእምሮና ጥረት በመተማመን፡ ዕድሉ ጋ መመላለሱን ሊያቆም ይችላል፡፡ የስኬቱ ምንጭ ዕድሉ እንደሆነ እያመነ ከተጠለ ግን፡ በራስ የመተማመን መንፈሱ እየተሸረሸረና እየከሰመ ይሄዳል፡፡ የስኬት መሰረቱን እንደመገንዘብ እያደረገው ስለሆነ፡ ተጨማሪ ስኬት ማግኘት ይቅርና ባለበት ቦታም መቆየት ያቅተዋል፡ ወደ ውድቀት አዘቅት ይገባል (ኢንቨስትመንትን የሀብት እድገት ይገታል ባይቀለበ ማለት)፡፡ ሁሌም የስኬት መሰረትን ይበልጥ ማስፋትና ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

ከስኬት ወደ ስኬት የምናደርገውን ጉዞ የሚያሰናክሉብን ሌላ እንቅፋት፡ በቀጥታ ከእስ የምንመለከተው ነው  የስኬት ምሰሶዎችን በመዘንጋት በአቋራጭ ካስቀረናቸው፡ የስኬትን ጉዞ የሚገድቡ ይሆኑብናል፡፡

ቀጥሏል:: ግን እንደገና ሌላ ችግር ተፈጠረ:: የመስተንግዶ ቅልጥፍና ተዳከመ፤ ደንበኞች በወረፋ ተማርረዋል፤ እንደገና እድገታችን ተቋረጠ:: ለብዙ ደንበኞች የሚበቃ መስኮት ቢኖርም፤ ባለሱቁ ሁሉንም በፍጥነት ማስተናገድ ከአቅሙ በላይ ሆኗል::

በዚያ አይነት ሱቅ ውስጥ፤ አንድ ሰው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ስንት ደንበኞችን ማስተናገድ ይችላል? ልክ አለው:: ቀልጣፋ አገልግሎት፤ ከእድገት ምሰሶዎች አንዱ ነው:: በእድገት ሂደት ላይ፤ ይህንን ምሰሶ በመዘንጋት እንደ ድሮው በአጭሩ ስላስቀረነውና ስላላሻሻልነው እድገታችንን ገደበው:: ሱቁን ለፈጣን መስተንግዶ በሚያመች መንገድ በማስተካከል፤ ወይም ተጨማሪ አስተናጋጅ በመቅጠር፤ ምሰሶውን ካላሳደግን በስተቀር፤ እድገታችን ይቋረጣል::

አንዱን ምሰሶ ብቻ፤ ወይም የነገሮችን አንድ ክፍል ብቻ ነጥለን በቁንፅል የምንመለከት ከሆነ፤ ወይም ዛሬ በአሁኗ ቅፅበት በቂ ሆነው የሚታዩን ሌሎቹን ምሰሶዎችና ክፍሎች እንዘነጋቸውና እድገታችንን እንዲገድቡ እንፈቅድላቸዋለን፤ ነገ አጥረት ሲከሰት ዱብዳ ይሆንብናል::

አሲድና አልካሊ ሲዋሃዱ፤ ጨው ይፈጠራል:: የተወሰነ ያህል አልካሊ አምጥተን አስቀምጠናል:: ጨው ለመፍጠር፤ አሲድ ያስፈልገናል:: አሲድ አምጥተን አልካሊ ላይ እንጨምረዋለን፤ የተወሰነ ያህል ጨው እናገኛለን:: አሁንም ተጨማሪ አሲድ አልካሊ ላይ በማፍሰስ፤ ተጨማሪ ጨው እንፈጥራለን::

«አልካሊ ይዘናል። ዋናው ነገር፤ አሲድ ማምጣትና ማፍሰስ ብቻ ነው» በሚል ትኩረት፤ በተደጋጋሚ አሲድ እየጨመርን የጨው ምርታችንን እናሳድጋለን:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን፤ በምናመጣው አሲድ ተጨማሪ ጨው ማምረት የማንችልበት ደረጃ ላይ እንደርሳለን:: አልካሊው አልቋል:: የጨው ምርት እንዳናሳድግ ገደበን ማለት ነው:: በተወሰነ ያህል አልካሊ፤ የተወሰነ ያህል ጨው ነው ማምረት የምንችለው:: ሁሉም ነገር ልክ አለው::

በሌላ አነጋገር፤ 'ሁሉም ነገር የየራሱ ተፈጥሮ አለው (ሁሉም ነገር በየራሱ ተፈጥሮ ነው):: ተፈጥሯቸውን በማወቅና በማገናዘብ፤ በስሌት ስናቀናብራቸው፤ ስናዋህዳቸው፤ ስናገጣጥማቸው፤ ስናገናኛቸው ነው፤ ለህይወት የሚጠቅም ምርት በመፍጠር በስኬት የምንጓዘው::

ምግብ የበርካታ ነገሮች ቅንብር ነው:: የምጣድሙቀት፤ዱቄት፤ ውሃ፤ እርሾ፤ ጊዜ፤... በተወሰነ ምጣኔና ልክ ይቀናበራሉ:: ውሃ ስናከማች ዱቄቱ ቢያልቅ፤ እርሾ ሞልቶን-ሊጡ እንዲቦካ ጊዜ ካጣን፤ የቦካውን ምጣድ ላይ አፍስሰን እሳቱ ከጠፋ ... የእንጀራ ምርታችን ይቆማል::

የሚጣፍጥ ወጥ መስራት የምንችለውም፤ ስጋ፤ ቲማቲም፤ ሽንኩርት፤ ጨው፤ ውሃ፤ እሳት፤ ቅቤ.. የመሳሰሉ ነገሮችን እንደየተፈጥሯቸው አመጣጥነን ስናቀናብራቸው ነው:: ለሌሎቹ የሚመጥን ጨው ስናስገባ፤ የሚጣፍጥ ወጥ እንሰራለን:: በቁንፅል «ጨው ያጣፍጣል» በሚል ስሜት፤ የሌሎቹን ነገሮች መጠን ሳናገናዝብ፤ ደጋግመን ጨው ብቻ ብንጨምር ግን ያም

ለማደር ካልሆነ በቀር ዋጋ የለውም:: እንብላ ብንለው እንኳ፤ ትርፉ በሽታ ነው:: የሰው አካልም፤ የራሱ ተፈጥሮና ልክ አለው::

የተለያዩ አይነት ምግቦችና ንጥረነገሮች፤ ለሰው አካል ተመጥነው ካልተዘጋጁና ካልተመገብን ጤንነትን እናሳድግም:: ጨው፤ አትክልት፤ ስጋ፤ ወተት፤ ፍራፍሬ፤ ዳቦ፤ እንጀራ፤ ሽሮ፤ ቅባት፤ ማር... ወዘተ ለሰው ጤንነት ያስፈልጋሉ - በተወሰነ ልክ ተመጥነው:: እንዲሁ በቁንፅል «ማር ለጤንነት ያስፈልጋል» ብለን ማር ስንልስና ስንጠጣ ብንውልስ? «ማርም ሲበዛ ይመራል» የሚባለውን እንድናስታውስ ያደርጋል:: በመምረር ብቻ ካለፈልንም ጥሩ ነው:: በጣም አላበዛነውም ማለት ነው::

የእንቅልፍና የጥናት፤ የስራና የእረፍት፤ የምርምርና የመዝናኛ ጊዜም እንዲሁ፤ በተወሰነ ልክ ስናመጣጥናቸው ነው ስኬታማ የምንሆነው:: አብዛኛው ሰው፤ እንቅልፍ ያበዛል - ለዚያውም የመኝታና የቁም እንቅልፍ:: ከስራ፤ ከንባብ፤ ከእውቀትና ከምርታማነት የሚገኘውን ደስታ ሳያጣጥም፤ በዋል ፈሰስና በወሬ ጊዜ ማሳለፍን እንደ እረፍት ይቆጥረዋል።መስከርንና መቦዘንን እንደመዝናናት የሚቆጥሩ ሰዎችም ብዙ ናቸው - ከውድቀት ምህዋር ያልተላቀቁ:: ለእውቀት ሲያጠኑና ሲመራመሩ፤ ለምርታማነት ሲጥሩና ሲሰሩ፤ ያኔ እንቅልፍ፤ እረፍትና መዝናና ምንኛ እንደሚጣፍጡ ቢያውቁ ምናለበት? ሁሉንም በልኩ ሲያደርጉ፤ አለምና ህይወት ይጣፍጣሉ::

ሌሎች ደግሞ አሉ:: በተቃራኒው፤ የእንቅልፍ ሰአታችንን ቀንሰን ለረጅም ሰዓት ብናጠና፣ ብንሰራ... ለምሳሌ አንዳንድ የአይሱዙ ሾፌሮች እንደሚያደርጉት በጫትና ቡና እንቅልፋችንን እያባረርን ቀንና ሌሊቱን ስንነዳ፤ ስንሰራ፤ ስናጠና ውለን ብናድርስ? በሰራንና ባጠናን ቁጥር፤ እስከ ተወሰነ ጊዜ ተጨማሪ ውጤት እናገኛለን:: ከልኩ ካለፈ ግን፤ ውጤታችን እየተዳከመ ይሄዳል:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላም ሰውነታችን መቋቋም ስለሚያቅተው እንቅልፍ ይጥለናል::

የአይሱዙ ሾፌሩ የፈለገውን ያህል በጫትና በቡና እንቅልፉን ለማባረር ቢሞክር እንኳ፤ ያለእንቅልፍ የመቆየት የሰውነት ልክ ስለሚሟጠጥ ይፈዛል፤ መሪ እንደጨበጠ ያንቀላፋል፤ መንገድ ለቆ፣ የሞትና የንብረት ጥፋት ያደርሳል:: ሁሉም ልክ አለው:: ብዙውን ጊዜ ግን፤ ይህንን ተፈጥሮአዊ እውነት ወደ ጎን ትተን አንድ ነገር ላይ ብቻ በቁንፅል፤ ለዚያውም የአሁኗ ቅፅበት ላይ ብቻ እናተኩራለን::

ሸቀጦችን በተሻለ ጥራትና ዋጋ በማቅረብ ደንበኞችን ስላበራከትን፤ እሱ ላይ ብቻ እናተኩራለን - አመቺ የመሸጫ ቦታና ቀልጣፋ አገልግሎትም ለስኬት አስፈላጊ ምሰሶዎች እንደሆኑ ረስተን:: አሲድ በመጨመር ጨውን ስላመረትን፤ እሱን ብቻ እንደጋግማለን - አልካሊን ዘንግተን:: ,

አንድ ዘዴ፤ አንድ ምሰሶ፤ አንድ ክፋይ ላይ በቁንፅል በማተኮር ለጊዜው ውጤታማ ስንሆን፤ እርሱኑን ብቻ ይበልጥ ደጋግመን እንፈጽማለን:: ውጤታማ የምንሆነው ግን እስከተወሰነ ጊዜ፤

እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ብቻ ነው - የዘነጋናቸው ሌሎች ዋና ነገሮች፤ ምሰሶዎችና ከፋዮች ለጊዜው የተሟሉ በመሆናቸው:: ከጊዜ በኋላ ግን፤ አብረን ስላላሳደግናቸው የእድገት ገደብ ይሆናሉ::

ስለዚህ፤ በስኬት ላይ ስኬት ሲደራረብ፤ በዚያው የስኬት ዘዴ ጥረታችንን ከፍ እያደረግን በውጤታችን ከመጠቀም፤ከመርካትና ከመኩራት በተጨማሪ፤ ሁሌም በአስተዋይነት መመርመርና መፈተሽም እንደሚኖርብን የሚያስጠነቅቅ ነው - Limits to Success የተሰኘው አርኪታይፕ::

ለጊዜው የተሟላ ሆኖ ስለታየን ብቻ፤ ትኩረት የነፈግነው የስኬት ምሰሶ ካለ፤ ስህተታችንን በማረም በጊዜ ለማስተካከል ነቅተን መጠበቅ አለብን:: አለበለዚያ ግን ስኬትን የሚገድብ ሰበብ ይሆንብናል:: ወደ ውድቀት ምህዋርም ሊወረውረን ይችላል - አሳዎቹ እንደገጠማቸው::

አሳዎቹ ምግብ ለማምረት ዕፀዋት እንዲተከሉ አስተዋዩ ዊዝ አስምሯቸዋል - ለተክሎች እድገት ውሃ፤ ፀሃይ፤ አፈር እንደሚያስፈልግም:: አንዳንዶቹ የፀሃይ ሃሩር ጠልተው፤ ዋሻ ውስጥ መትከልን መርጠዋል - አፈር ላይ መትከላቸውን በቁንፅል በማየት፤ ለዛሬ መገላገላቸውን ብቻ በመመልከት:: ትክክለኛ ማሳ ላይ ሲተከሉ የዋሉ ሌሎች አሳዎች ደግሞ፤ ተክሎቹ ቶሎ እንዲያድጉ ወደ ላይ ሳብ-ሳብ አድርገዋል - መርዘማቸውን ብቻ በቁንፅል በማየት:: በተወሰነ የውሃ፤ የአፈር፤ የፀሃይና የጊዜ ቅንብር ውስጥ፤ ተክሎቹ የሚያድጉበትና የሚረዝሙበት የራሳቸው ተፈጥሮ አላቸው - የራሳቸው ልክ:: ቅንብሩ ሲለወጥስ? የተወሰነ ማዳበሪያ ተጨምሮበት ሌላ ቅንብር ሲፈጠርም፤ ተክሎቹ የሚያድጉበት ሌላ የራሳቸው ልክ አላቸው::

ተክሎቹን በፍጥነት ለማሳደግ የፈለጉ አሳዎች ማዳበሪያ መጠቀማቸው ተገቢ ነው:: በትንሽ ማዳበሪያ ተክሎቹ በፍጥነት የማደግ ምልክት አሳዩ:: አሳዎቹ እንደገና ማዳበሪያ ጨመሩ:: ተክሎቹ በደንብ አደጉ:: ይሄኔ፤ አሳዎቹ ከልክ በላይ ማዳበሪያ በመጨመር የበለጠ ውጤት የሚያገኙ መሰላቸው:: ተክሎቹ ግን ተመርዘው አረፉ:: ማዳበሪያ በተወሰነ ልክ፤ የተክሎችን እድገት ያፋጥናል፤ ከልክ በላይ ሲሆን የተክሎቹን እድገት ይገታል:: ለሁሉም ልክ አለው:: የተክሎቹ ጀነቲክ ቅንብር በባዮቴክኖሎጂ ቢሻሻል፤ በተጨማሪ ማዳበሪያ እድገታቸውን ይበልጥ ማፋጠን ይቻላል - አሁንም በተወሰነ ልክ::

ሌሎች የእድገት ምሰሶዎችን በመዘንጋት፤ ማዳበሪያ ላይ ብቻ በማተኮር ያንኑን ይበልጥ መደጋገም መፍትሄ አይሆንም:: ፈረንጆቹ The Bigger Hammer Syndrome የሚሉት አይነት አባዜ ውስጥ እንገባለን:: እናጢው በመዶሻ ሚስማር ይመታል - ሁሌም እንደሚያደርገው:: አሁን ግን፤ ሚስማሩ እንጨት ላይ አልገባ ብሎታል:: የሚስማሩ ሹልነትና ጥንካሬ፤ የእንጨቱ አይነትና ልስላሴ፤ በሞሃል ሌላ ብረት መኖር አለመኖሩ፤ የመዶሻው ጥራትና ክብደት፤ የእናጢው ሙያና ብርታት... እነዚህ ሁሉ ለስኬቱ ምሰሶዎች ናቸው::

ሁሉንም ምሰሶዎች በማገናዘብ ችግሩን መመርመር ትቶ፤ በቁንፅል የመዶሻው ክብደት

ላይ አተኩሯል አናጢው:: ተለቅ ባለ መዶሻ ይሞክራል:: አልሆን ሲለው ሌላ ትልቅ መዶሻ አምጥቶ ይቀጠቅጣል:: እንጨቱን ሰባብሮ ያሳርፈዋል:: ከዚህ ሁሉ በኋላ፣ ከስር የተሰበረ የድሮ ሚስማር ቢገኝስ?

በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ አንዳንድ ተማሪዎች የትምህርቱ ፅንሰሀሳብ በደንብ ሳይገባቸው በከፊል ብቻ ተገንዝበው፣ ይበልጥ በሽምደዳ ላይ በማተኮር ፈተና እያለፉ ይመጣሉ:: ትምህርቱ እየጠነከረ ይመጣል። ግን፣ ፅንሰሃሳብ የመገንዘብ ጥረት ከማጠናከር ይልቅ፣ ለረጅም ሰአት ቁጭ ብለው ለመሸምደድ ይሞክራሉ::

እንደምንም ያልፋሉ። ኮሌጅ ሲገቡ ግን፣ ቀንና ሌሊቱን ሁሉ ለሽምደዳ ቢያውሉት እንኳ፣ ውጤታማ የማይሆኑበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ:: የትምህርቱ ብዛትና ጥንካሬ ተቀይሯል:: እነሱ ደግሞ ፅንሰሃሳብ የመገንዘብ ብቃትን ዘንግተው በአጭር አስቀርተውታል:: ይህም ነው የስኬት ገደብ የሆነባቸው:: ሽምደዳን ይበልጥ በመጨመር ሳይሆን፣ ፅንሰሃሳብ የመገንዘብ ብቃትን ለማዳበርና፣ ወደኋላ ሄዶ የእውቀት መዋቅሮችን ለመገንባት መጣር ያስፈልጋል::

አንድ ነገር ላይ ብቻ አተኩረን በምናደርገው ጥረት፣ ለጊዜው ስኬቶችን ልናስመዘግብ እንችላለን:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን፣ ያንኑን ጥረት ይበልጥ ብንጨምር እንኳ፣ ተጨማሪ ስኬት እውን ማድረግ ያቅተናል:: በቁንፅል አንድን ነገር ብቻ እያየን፣ ከጎን የዘነጋነው ሌላ የስኬት ምሰሶ አለ ማለት ነው::

ነገሮችን ከትስስርና መስተጋብራቸው ጋር በመመርመር፣ በቅንብራዊ አስተሳሰብ መፍትሄ ልናገኝለት ይገባል:: አለበለዚያ፣ ያንኑን ጥረት ብቻ ይበልጥ መከመር ፋይዳ አይኖረውም፣ ከኪሳራ በቀር - (The Bigger Hammer Syndrome):: አገርአቀፍ ችግሮችን በምሳሌነት እንጥቀስ::

በኢትዮጵያ፣ ኤችአይቪ ኤድስንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ጨምሮ፣ በርካታ ችግሮችን እንዴት ለመፍታት እንደሚሞከር አስተውሉ:: «ችግሮቹ፣ በመረጃ እጥረት ሰበብ የሚፈጠሩ ናቸው» ከሚል ሃሳብ በመነሳት የሚቀርቡ መፍትሄዎችን ታዝባችሁ ይሆናል:: ሁልጊዜ ለሕዝቡ ተጨማሪ መረጃ በመስጠት፣ ችግሮቹን መፍታት ይቻላል ብለው ያምናሉ።

በእርግጥም፣ «የግንዛቤ እጥረትን ለመቅረፍ» ተብለው በሚሰራጩ መረጃዎች አማካኝነት የተወሰኑ ለውጦች እውን ይሆናሉ:: ነገር ግን፣ የሚያጠግብ ለውጥ አናገኝበትም:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላም፣ የስኬት ለውጥ ተመናምኖ ይቆማል:: የመረጃ አቅርቦቱን ይበልጥ ብንጨምር እንኳ፣ ተጨማሪ ለውጥ ማምጣት ያቅተናል:: ቆም ብሎ እንደመመርመር፣ «የግንዛቤ እጥረትን ለመቅረፍ» በሚባለው የተለመደ መፈክር በሚሊዮን የሚቆጠር ብር እየወጣ፣ በሬድዮ፣ በቲቪ፣ በህትመት፣ በስብሰባ፣ በስልጠና... መረጃ ለማሰራጨት ተጨማሪ ጥረት ይደረጋል::

ነገር ግን የመረጃ ስርጭቶቹ ይበልጥ ቢስፋፉም የተጠበቀውን ለውጥ እንዳላመጡ ጥናቶች በተደጋጋሚ ያረጋግጣሉ:: በንፅህና ጉድለት ለበሽታ ላለመጋለጥ፣ መፀዳጃ ቤት

አበጅቶ በመጠቀም ተቅማጥን መከላከል እንደሚቻል ተደጋጋሚ መረጃ ቢሰራጭም፤ በተግባር በቂ ለውጥ አልመጣም::

ለኤድስ ላለመጋለጥ፤ ኮንዶም በመጠቀም ኤችአይቪን መከላከል፤ ባልታቀዱ ወሊዶች ድህነትን ላለማባባስ የቤተሰብ ምጣኔ መንገዶችን መጠቀም፤ የሰዎችን ህይወትና ደስታ ላለማጨናገፍ ጎጂ ባህሎችን ማስወገድ... በእነዚህ መስኮችም የተጠበቀውን ያህል ለውጥ እውን አልሆነም:: በጥናቶች እንደተገለፀው፤ በኤችአይቪ ኤድስ ዙሪያ የህብረተሰቡ የመረጃ እውቀት ከ90% በላይ ሲሆን፤ በተግባር የተገኘው ለውጥ ግን ከ40% በታች ነው። ለምን?

ችግሮቹን ለማስወገድና ስኬት ለማስመዝገብ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች ምንድናቸው ብለን መጠየቅ ይኖርብናል:: የመረጃ አቅርቦትና ስርጭት፤ አንድ የስኬት ምሰሶ ነው:: ሌሎች የስኬት ምሰሶዎችን ከዘነጋናቸውና ካላሳደግናቸው ግን፤ እስከተወሰነ ደረጃ እንጂ በመረጃ ስርጭት ብቻ ለውጥ ልናመጣ አንችልም::

መረጃዎችን አውቆ በተግባር እንዲጠቀምባቸው፤ በቅድሚያ ለህይወት ከፍተኛ ክብር እንዲሁም ለመረጃዎች ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጥ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ሊኖር ይገባል:: እነዚህም የስኬት ምሰሶዎች ናቸውና:: ሳይንሳዊ አስተሳሰብን ቸል ብለን በአጭሩ ስናስቀረው፤ ስኬታችን ይገደባል:: ይህን ለማረጋገጥ፤ ተቃራኒ የሆኑ መጥፎና ኋላቀር አስተሳሰቦችን መመልከት ትችላላችሁ::

በኮንዶም፣ በፀረቫይረስ ህክምና፣ በእርግዝና መከላከያ ዙሪያ፤ እውነታ ላይ ያልተመሠረቱ ሃሰተኛና አደገኛ ወሬዎችን የማሰራጨት ዘመቻ በሰፊው ይታያል:: በፀረሳይንስ ዘመቻው፤ ስነምግባር በጎደለው ሁኔታ በሳይንስ ያልተደገፉ የባህልና የኃይማኖት መፍትሄዎችን አስፋፍቷል:: የስኬት ምሰሶ የሆነውን ሳይንሳዊ አስተሳሰብ እንዲህ በአጭሩ እያስቀረን፤ በመረጃ ስርጭት ብቻ ተጨማሪ የለውጥ ስኬቶችን እውን ማድረግ አይቻልም:: ህይወትን ከማፍቀር የመነጨ አላማ፤ በራስ ጥረት ህይወትን አስደሳች የማድረግ ክህሎትና ታታሪነትም የስኬት ምሰሶዎች ስለሆኑ፤ እነዚህንም የሚገነባ ጥረት ያስፈልጋል - ስኬታችን በአጭሩ እንዳይገደብ።

# 8. ኢንቨስትመንት የጎደለውን እድገት ሳይመግቡ ማለብ (Growth and Underinvestment)

የጡዘት ምህዋር (ኤስካሌሽን) በሚለው ርእስ ያነሳነውን ኩባንያ አስታውሱ:: ከ40 አመት በፊት፤ ከአውሮፓና ከአሜሪካ ኩባንያዎች ጋር የሚፎካከር ጠንካራ መሰረት ነበረው - በቴክኖሎጂ፣ በምያተኛ፣ በአገልግሎት። በጠንካራ መሰረቱም ነው፣ ገቢውን እያሳደገ በስኬት የተጓዘው።

ከጊዜ በኋላ፣ አንድ ማሽን ተበላሽቶበት መለዋወጫ እቃ ለመግዛት ሲሞክር ግን፤ ያንን አይነት ማሽን ማምረት ካቆምን ብዙ አመታት ተቆጥረዋል የሚል ምላሽ ነው ያገኘው::

የቴክኖሎጂ ፈጠራ በየጊዜው እየተራቀቀ፤ የተሻሻሉ ማሽኖች በየጊዜው ይፈበረካሉ:: ኩባንያው ግን፤ በድሮው ቴክኖሎጂ ላይ ቆሞ ቀርቷል:: የገቢ ምንጭ የሆነለትን ጠንካራ መሰረት ለበርካታ አመታት ቸል ብሎታላ።

የስኬት መሰረቱን በየጊዜው ለማጠናከር ኢንቨስት ስላላደረገ፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የተወዳዳሪነት አቅሙ ተዳከሞ፤ ስኬትና ገቢው አደጋ ላይ ይወድቃል:: «ሳይመግቡ ማለብ» ይሉሃል ይሄ ነው - ለዛሬ ገቢ ማሳደግን ብቻ በቁንፅል (በቅፅበታዊነት) በመመልከት፤ የስኬት ስረመሰረትን መዘንጋትና መሸርሸር::

ከራሳችን ጀምረን እንመልከት:: ትናንት እንጨት ስለመፍለጥ የሆነች ግንዛቤ ይዘን፤ እንጨት በመፍለጥ ገቢ ለማግኘት ወስነን (መርጠን)፤ እንጨት ለመፍለጥ ጥረናል እንበል:: ባገኘነው ገቢ ዛሬ ላይ ደረስን:: ዛሬ ደግሞ፤ ጭቃ ስለማቡካት የሆነች ግንዛቤ ጨብጠን፤ በዚሁም ገቢ ለማግኘት ወስነን፤ ጥረት እያደረግን ነው:: የዛሬው አለቀ::

በነገራችን ላይ፤ የቀን ገቢ ብቻ አይደለም የምናገኘው:: በእያንዳንዱ ግንዛቤ ተጨማሪ የአስተዋይነት አቅም እናገኛለን። ከእያንዳንዱ ውሳኔም በራስ ምርጫ የመተማመን አቅም፤ ከእያንዳንዱ ጥረት የብርታት አቅም እያዳበርን ነው። ያለ ግንዛቤ፤ ያለ ውሳኔ፤ ያለ ጥረት የእለት ገቢ ብናገኝ ኖሮ፤ እነዚህን አቅሞች አናዳብርም ነበር:: ነገስ?

ነገ ደግሞ፤ ቆሻሻ ስለመጥረግ አንዳች ግንዛቤ ወስደን፣ በዚህችው ገቢ ለማግኘት እንወስንና ጥረት እንጀምራለን:: ግን እንዲህ «ከእጅ ወደ አፍ» በሆነ የድህነት ኑሮ እስከመቼ? የአስተዋይነት አቅምና ግንዛቤ፤ በራስ የመተማመን አቅምና ውሳኔ፣ የብርታት አቅምና ጥረት... እነዚህን የስኬት ምሰሶዎች አሟልተናል። ታዲያ ምንድነው የጎደለው? ምንድነው ችግሩ?

በየጊዜው እየተደማመረ የሚሄድ ብቃት መች አዳበርን? በረዥም ጊዜ ተደማምሮ የሚዳብር ብቃት ማለት፤ በዚያውም ልክ ለረዥም ጊዜ የሚያገለግል ኢንቨስትመንት ማለት ነው። ይህ ጎድሎናል።

ሰውዬው በረዥም ጊዜ ተደማምሮ ለረዥም ጊዜ የሚያገለግል ጥልቅ፤ ሰፊና ጠንካራ እውቀት እያዳበረ ነው? ትናንት እንጨት ስለመፍለጥ የያዘውን ግንዛቤ ለዛሬ አይጠቀምበትም። ዛሬ ጭቃ ስለማቡካት የጨበጠውን ግንዛቤም ለነገ አይሆንም። ነገ ቆሻሻ ስለመጥረግ የሚኖረው ግንዛቤም፤ ለነገ ብቻ ነው። በየቀኑ ቅንጭብጫቢ ግንዛቤዎችን ያሳድዳል እንጂ፤ ለረዥም ጊዜ የሚያገለግል የተጠናቀረና የተሳሰረ እውቀት አላዳበረም (ኢንቨስትመንት ላይ አላተኮረም)።

የየእለቱ ውሳኔዎቹም፤ ቅንጫቢ ናቸው - የማይመጋገቡ። የዛሬና የነገ ውሳኔዎቹን የሚመዝንበት፤ የሚያስማማበትና ቅደም ተከተል አስይዞ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርሰበት የህይወት አላማ አላበጀም - የረዥም ጊዜ አላማ አልያዘም።

ጥረቶቹም፤ እንዲሁ በየእየቱ አይደማመሩም። ባልተሳሰሩ የዛሬና የነገ ጥረቶች፤ የሙያ ብቃት ወይም ልምድ ማዳበር አይችልም። በአጭሩ፤ የስኬት ስረመሰረቶችን (የተጠናቀረ እውቀት፤ የህይወት አላማ፤ የሙያ ልምድ) ለመገንባት ትኩረት አልሰጠም። የእለቷን ግንዛቤ፤ ውሳኔና ጥረት ከየእለቷ ገቢ ጋር ብቻ በማያያዝ ነው የሚመለከተው።

በአንጨት ዙሪያ፤ ሰውዬው የተጠናቀረ እውቀት፤ የህይወት አላማና የሙያ ልምድ ለማዳበር በሚያስችል የረዥም ጊዜ አቅጣጫ ቢጓዝ ኖሮስ? እንጨት ፍልጦ የእለት ገቢ ከማግኘት በተጨማሪ፤ ቀስ በቀስ ወደ ረቀቀ ዘመናዊ የእንጨት ስራ በመሸጋገር ገቢውን በብዙ እጥፍ የማሳደግ ብቃት ያዳብራል። በየቀኑ በሚጨብጣቸው ግንዛቤዎች አማካኝነት የተጠናቀረ እውቀቱን እየገነባ፤ በየቀኑ በሚመርጣቸው ውሳኔዎች የህይወት አላማውን እያፀና፤ በየቀኑ በሚያደርጋቸው ጥረቶች የሙያ ልምድ እያዳበረ ይሄዳል።

የተቀናበረ እውቀት ሲገነባም በየእለቱ ለአዳዲስ ግንዛቤ ይበልጥ የአስተውሎት ሃይል ይኖረዋል። የህይወት አላማውን ሲያፀናም፤ በየእለቱ ለትክክለኛ ውሳኔዎች ይበልጥ ጥንካሬን ይጎናፀፋል። የሙያ ልምድ ሲያዳብር፤ በየእለቱ ለተጨማሪ ጥረቶች ይበልጥ ብርታትን ያገኛል። በስኬት ላይ ስኬትን እየጨመረ ይሄዳል።

የስኬት ስረመሰረቶችን (ኢንቨስትመንትን) ቸል ካለ ግን፤ ስኬቱ በአጭሩ ከመቀጨት አይድንም። «የእለቱን ነው የማስበው፤ የእለቱን ነው የምኖረው» እያለ የዛሬዋን ቀን ብቻ በቁንፅል የሚመለከት ከሆነ፤ «ከእጅ ወደ አፍ» በሆነ ኑሮ ህይወትን ይገፋል - እጅ እስኪያጥረው ድረስ።

«ዋናው ኮኔክሽንን መጠቀም ነው» የሚሉ አንዳንድ ነጋዴዎችንም ተመልከቱ። ግንኙነቶችን ተጠቅሞ የስራና የቢዝነስ እድሎችን በማግኘት ገቢን ማሳደግ ያስፈልጋል። በእርግጥም፤ «ኮኔክሽንን መጠቀም» አንድ የስኬት ምሶሶ ነው። ነገር ግን እንዲህ በስኬት

ገቢያቸውን ሲያሳደጉ፣ የስኬት ስረመሰረቶችን መገንባት እንዳለባቸው ይዘነጋሉ፣ የስራ ወይም የቢዝነስ ብቃታቸውን ለመገንባት አይገለገሉበትም:: ብቃታቸውን በስኬት በማስመስከርና ደንበኞችን በማርካት ተጨማሪ «ኮኔክሽንን» ለመፍጠር አይሞክሩም።

«ኮኔክሽንን በመጠቀም» ከአቅማቸው በላይ የሥራ ትዕዛዝ ሰብስበው፣ ቅድሚያ ክፍያ ይቀበሉና... ባገኙት ገንዘብ ግን፣ ስራ የመምራት አቅማቸውን አይገነቡበትም:: የተዋዋሉበትን ስራ መፈፀም ሲያቅታቸው ደግሞ፣ ቃላቸውን ባለማክበር ደረጃውን ያልጠበቀ ዕቃ ወይም አገልግሎት ስለሚያቀርቡ፣ ብዙ ደንበኛ ጥሏቸው ይሄዳል:: ኮኔክሽናቸው ይበጣጠሳል::

«ኮኔክሽንን ለመጠቀም» በቅድሚያ «ኮኔክሽን» መኖር አለበት፣ የዚህ መሰረቱ ደግሞ የስራ ብቃት ነው:: አለበለዚያ፣ ምቹ የቢዝነስ አማራጭ ሲፈጠርም፣ በብቃታችን ማነስ ሳቢያ ያመልጠናል። ከትልቅ ኃላፊነት ወይም ለከፍተኛ ትምህርት ብንመረጥ፣ ስኬዜው ድክመታችን ቢሸፈንም እንኳ፣ ብዙም ሳይቆይ ከአቅማችን በላይ የሆነውን ሃላፊነትና ትምህርት እንዳልቻልነው መታወቁ አይቀርም:: ሁሌም አቅምን ማሳደግ ያስፈልጋል - የስኬት መሰረት ነውና::

በየእለቱ በትኩረት እያስተዋልን፣ እያነበብንና እያገናዘብን እውቀታችንን ስናዳብር፣ በየእለቱ በምንመርጣቸው ውሳኔዎች በራስ የመተማመን መንፈሳችንም፣ የሙያ ፍቅራችንንና የህይወት አላማችንን ስናጠነክር፣ በብርታት ተግተን እየጣርን የሙያ ብቃትና ልምድ ስንገነባ፣ በአጠቃላይ የህይወት ክህሎት ስናሳድግ፣ ምቹ አማራጮችን መጠቀም እንችላለን።

ክፍል 4

# የህይወት ክህሎት

**የራስን ህይወት መቅረፅ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ህይወት ቀያሽና ቀራጺ ነው**

በየጊዜው የሚበለፅግ ህይወት፣ ለራሳችን መቅረፅ እንችላለን።

የህይወት ክህሎትን ተጠቀም

የህይወት ክህሎትን ገንባ

የነጠሩ ሃሳቦችና መሳሪያዎችን (አርኪታይፖችን) ያዋሃደ "ስኬታማ የህይወት ሶፍትዌር" በስራ ላይ-ለብልፅግናና ለትራንስፎርሜሽን በ8ቱ አርኬታይፐስ

1. ከከሻፊ ጥገና .... (ታጭቦ ጭቃ እንደገና?)

   ወደ ሁነኛ መፍትሄና ወደ አስተማማኝ እርምጃ መሸጋገር

2. ሃላፊነትን እንደሸክም ከማንቋቀቅ... (አለባብሶ ማረስ፣ በአረም ለመመለስ)

   ለስኬት ሃላፊነትን መጨበጥ

3. ግቦችን ከመሸርሸር... (ሰበብ ፈጣሪ፣ ቅርብ አዳሪ)

   ግቦችን በፅናት ማሳደግ

4. ከመተጋተግ፣ ከመበላላት... (የእልህ ቤት፣ ሳይዘጋ ያድራል)

   በአነቃቂ ፉክክርና ትብብር ስኬትን ማፋጠን

5. ከማህበር ብሬ አሳዛኝ አወዳደቅ (የሁሉም የሆነ፤ የማንም ሳይሆን ይቀራል)

   የጋራ አእምሮ የለም፤ የራስህን ተጠቀምበት

6. ከስኬት ለስኬታማ መሳይ (ተጨማሪ ስኬት፤ ለእውነተኛው ስኬታማ

7. የስኬት ገደቦች (ኋላ ቆሞ ከመገተር፤ አስቀድሞ ማሳመር)

   የማያቋርጥ የስኬት ምህዋር መፍጠር

8. ብቃትን ከማይገነባ እድገት... (ሳይመግቡ ከማለብ)

   እያበለፀገ ብቃትን የሚገነባ ስኬት

# የህይወት ክህሎቶችና የ8ቱ አርኬታይፖች ተያይዥነት

በእውነታ ላይ የተመሰረተ ቅንብራዊ አስተሳሰብ (ST)፣ ለሁላችንም አጅግ የሚያስፈልገን፣ ከውድቀትና ከችግር ለመዳን ብቻ አይደለም። ስኬትን ለመቀዳጀትና በየጊዜው ያለማቋርጥ የሚበለፅግ አስደሳች ህይወት ለመጎናፀፍ ስለሚያስችለን ነው።

ነገሮችን በቁንፅል እየነጣጠልን አንደናበርም። በደፈናው እየገረዳደፍን አንጃጃልም። ዋና ዋና ነገሮችን በዝርዝር ከነመስተጋብራቸው እያገናዘብን በብርሃን እንራመዳለን።

በቅፅበታዊነት ዛሬንና አሁንን ብቻ እየተመለከትን በየአቅጣጫው በዘፈቀደ አንቅበዘበዝም። በደፈናው "ወደፊት ጊዜ ይመጣል፤ አንድ ቀን ይሆናል" እያልን አንደነዝዝም። እያንዳንዱ አመት፣ ወር፣ ቀን፣ ሰአት፣ ደቂቃና ሴኮንድ ከህይወት ዘመን ጋር የመስተጋብር ሂደታቸውን እያሰላን እንጓዛለን።

በደፈናው ስኬትን እየጎመጀንና ችግርን እየፈራን አንቃዥም። በቁንፅል የስኬት ምልክቶችን ለመሻማትና ከችግር ምልክቶች ለመሸሽ አንንደፋደፍም። የችግር ስረመንስኤና መፍትሄዎችን፣ የስኬት ስረመሰረትና ምሰሶዎችን ከነመስተጋብራቸው እየመረመርን ችግርን ከስሩ እንነቅላለን። ስኬትን ከስሩ እየገነባን፣ የእንዱ ግብ ስኬት ለተጨማሪ ከፍተኛ የግቦች ስኬት አቅም እያጠናከረልን እንገሰግሳለን።

ከህይወት ግብ ጋር አስተያይተን ሳንመዝን፣ በ"መሰለኝ ደስ አለኝ" ስሜትና በጭፍን የምኞት ፈረስ እዚህና እዚያ እየረገጥን አንዋከብም። በ"እይሞቀኝ አይበርደኝ" ትርጉም የለሽ ግብ አልባ ህይወት አንባክንም (እዛ እንሆንም)። ሃሳባችን፣ ምኞታችንና ድርጊታችን ሁሉ፣ ከህይወት አላማችን ጋር በመስተጋብር አስተሳስረን፣ በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወትን እውን እናደርጋለን። ለዚህ ነው ቅንብራዊ አስተሳሰብ የሚያስፈልገን - ስኬታማ የህይወት ክህሎት ለመታጠቅ - የህይወት አላማን ለመቀዳጀት።

## የህይወት አላማና ግብ

ሀ. ህይወት በዘፈቀደ እየተመራ ፈፅሞ ችግር የማይደርስበት ቢሆን ኖሮ፣ ስህተትን ማረም፣ ጥፋትን ማስተካከል፣ ችግርን ማስወገድ የሚባል ነገር አይኖርም ነበር። ትክክለኛ አስተሳሰብ ለማግኘት መጣርም አያስፈልግም ነበር። ህይወት ግን በራስ ተነሳሽነት፣ በራስ ምርጫና ጥረት ካልሆነ በቀር፣ በዘፈቀደ መቀጠል አትችልም - ተሰናክላ ትወድቃለች። በራስ ተነሳሽነት ራስን

# 1. ሁነኛ መፍትሄን እንጂ.... ከሻፊ ጥገናን አይሻም

አላማና ግቦቹን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው፣ በከሻፊ ጥገና (fix that fail) ጊዜና አቅሙን ለማባከን ፍቃደኛ አይደለም። የህይወት አላማው እና ግቦቹ በሙሉ፤ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከሁሉም ተግባሮቹ ጋር የተሳሰሩ እንደሆኑ በደንብ ገብቶታል።

ስለዚህ በጊዜያዊ ችግርና ጉጉት ተገፋፍቶ፣ በማያዛልቅ አቋራጭ መንገድ መባከንን ወይም ከቆይታ በኋላ በሚከሽፍ ጥገና መጠመድን አይፈቅም. የህይወት አላማውንና ግቦችን ለማሳካት እንደማይጠቅሙት በግልፅ ያውቃል። የህይወት አላማውን የሚያፈቅር እስከሆነ ድረስ፣ አላማና ግቦቹን ሊያሳካ የሚችል አስተማማኝ አርምጃና ችግሮችን የሚያስወግድ ሁነኛ መፍትሄ ላይ ማተኮር ይኖርበታል።

## ሀ. ከህሎትን መጠቀም

አስተማማኝ እርምጃና ሁነኛ መፍትሄ፣ ሁሌም በቀላሉ ይገኛሉ ማለት አይደለም። የህይወት ከህሎቱን ተጠቅሞ መጣር አለበት።

በሰፊው የተለመዱና ካሁን በፊት የሚያውቃቸው ቀላል እርምጃዎች፣ ለግቦቹ ስኬት የሚጠቅሙ አስተማማኝ መንገዶች ላይሆኑለት ይችላሉ። ከባድ ችግር ሲገጥመውም፣ ከከሻፊ ጥገናዎች ውጭ፣ አስቀድሞ የተዘጋጀና በሰፊው የሚታወቅ ሁነኛ መፍትሄ ላይኖር ይችላል። ነገር ግን፡ በተለመደው አቅጣጫ ብቻ ከመንደርደር ይልቅ፣ አዳዲስ አስተማማኝ እርምጃዎችንና ሁነኛ መፍትሄዎችን ማቀናበር ይችላል - የህይወት ከህሎቱን በመጠቀም።

በጊዜያዊ ችግሮች እንዳይረበሽና በጉጉት ስሜቶች እንዳይማረክ፣ አላማና ግቦቹ ላይ በማተኮር ቆም ብሎ ነገሮችን በጥልቀትና በጥራት በማገናዘብ፣ አዳዲስ ሃሳቦችን ማመንጨት የሚችለው የህይወት ከህሎቱን በመጠቀም ነው። ባፈለቃቸው አዳዲስ ሃሳቦች አስተማማኝ እርምጃዎችንና ሁነኛ መፍትሄዎችን መርጦ መወሰን መቻልም፣ አንድ የህይወት ከህሎት ነው። ውሳኔውን በተግባር የመተርጎም ፅናትም እንዲሁ። **ለከሻፊ ጥገና ፊት አለመስጠት ማለት፣ የህይወት ከህሎቱን** ሙሉ ለሙሉ ለመጠቀም መጣጣር ማለት ነው። በየጊዜው ለሚኖሩን ግቦችና ለሚገጥሙን ችግሮች፣ የአስተማማኝ እርምጃና የሁነኛ መፍትሄ ምንጮችን፣ ሌላ ሳይሆን የህይወት ከህሎት ነው። ግን ምንጭ ብቻ አይደለም። ሰፋ አድርገን ስናየው፣ የህይወት ከህሎት በራሱ፣ አስተማማኝ እርምጃ ነው። ሁነኛ መፍትሄም ነው።

## ለ. ከህሎትን ማዳበር

ህልውናን የምናለመልምበት፣ አስደሳች የብልፅግና ህይወት የምንመሰርትበት አስተማማኝ የስኬት ስረመሰረታችን፤ የህይወት ከህሎት አይደል? ይህን ጠንቅቆ የተረዳ ሰው፤ በህይወት ከህሎት ምትክ፤ የከሻፊ ጥገና ጨዋታዎችን አይሞካከርም።

ECMAP

የአምፖል ፋብሪካው በዋጋና በጥራት ተመራጭ የሆኑ አምፖሎችን በብዛት የማምረት እንዲሁም ለገበያተኛ የማስተዋወቅና የመሸጥ ክህሎቱን በማዳበር ስኬታማ ለመሆን መጣር አለበት? ክህሎትን ለማዳበር ሳይጥር፤ መናኛ አምፖሎችን እያመረተ፤ በማስታወቂያ ብዛት ብቻ በአቋራጭ ተመራጭ ለመሆን ቢሞክርስ? ጥቂት ሰዎች ለተወሰነ ጊዜ እየተታለሉ መናኛውን አምፖል ቢገዙ እንኳ፣ ብዙም ሳይቆይ ጉዱን ያዩታል።

የማያዛልቅ ከሻፊ ጥገና፤ አስተማማኝ የውድቀት መንገድ እንጂ አስተማማኝ የስኬት መንገድ አይደለም። የህይወት አላማውንና ግቦችን የሚያፈቅር ሰው፤ ሁነኛና አስተማማኝ የስኬት መንገድ የሚገኘው የህይወት ክህሎትን በማዳበር እንደሆነ ስለሚረዳ፤ በፍቅር እየጣረ ይራመዳል። ለከሻፊ ጥገና ፊት አለመስጠት ማለት፤ የህይወት ክህሎትን ለማዳበር መጣጣር ማለት ነው።

# 2. ግቦችን ያጠናክራል እንጂ... አይሸረሽርም

በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወትን ለመቀዳጀት ያነጣጠረ የህይወት አላማ ስንይዝ፣ ሚዛን ወይም ኮምፓስ ፈጥረናል ማለት ነው። የጉሮ አቅጣጫችንን (ወይም ግቦቻችንን) ለመቀየስ፣ ለመመርመር፣ ለመለካትና ለማስተካከል አንቸገርም፤ በዚሁ የአላማ ኮምፓስ ወይም የአላማ ሚዛን እንጠቀማለንና።

ለምሳሌ፤ ሁለት ወጣቶችን ውሰዱ፤ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ምን አይነት ግቦችን ቢይዙ ይመረጣል? ዩኒቨርሲቲ ገብተው፤ እንስሳ ህክምን ወይስ የእርሻ ሳይንስን፤ የዲዛይን ወይስ የፊልም ጥበብን ለመማር ቢያልሙ ይሻላቸዋል? ምን አይነትና ምን ያህል መፃህፍት ቢያነብቡ ይሻላል? የትኞቹ የትምህርት አይነቶች ላይ ቢያተኩሩና ከትምህርት ክፍለ ጊዜ ውጪስ ምን ቢያደርጉ ይጠቅማቸዋል?

ጥያቄዎቹን ለመመለስ ያስቸግራል። ራሳቸው ወጣቶቹም የህይወት አላማቸውን ካላወቁ፤ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ማግኘት አይችሉም። ግቦችን ለመምረጥና ለመወሰን የሚያስችል፤ ግልፅ የመለኪያ ሚዛንና የማንፀሪያ ኮምፓስ አልያዙም። ግቦችን በዘፈቀደ ቢመርጡ እንኳ፤ ግቦቹ ትርጉምና ክብደት አይኖራቸውም። ዛሬ የመረጡትን ግብ ነገ ይቀይሩታል፣ ይሸረሽሩታል። የህይወት አላማቸውን የመረጡ ከሆነ ግን፤ ጥያቄዎቹ ከፍተኛ ትርጉም ይኖራቸዋል።

አንደኛዋ ወጣት፤ ወደፊት የፊልም ስራ ኩባንያ በመመስረት ምርጥ ፊልሞችን በአዘጋጅነትና በአስተባባሪነት የምትሰራ ስኬታማ ባለሙያና ባለሃብት ለመሆን የህይወት አላማዋን መርጣለች። ሁለተኛው ወጣት ደግሞ በአገር ውስጥ ገበያ፤ ከዚያም በውጭ አገር ገበያ በተወዳጅነት የሚቸበቸቡ አሪፍ የልብስ አይነቶችን የሚፈጥር ዲዛይነር ለመሆን የህይወት አላማውን መርጧል። እንደገና ተመልሰን ጥያቄዎቹን እንያቸው። ወጣቶቹ የ10 እና የ5 አመት ግቦች (ለምሳሌ የዩኒቨርሲቲ ምርጫቸውና የስራ እድል ፍለጋቸው) ምን ምን ቢሆኑ ይሻላል? የትምህርት አይነትና የንባብ ትኩታቸውስ? አዋዋላቸውስ?

የፊልም ሙያን የመረጠች ወጣት፤ በኪነጥበብ መስክ እንጂ በእንስሳት ህክምና የዩኒቨርስቲ ትምህርት የመከታተል ግብ መምረጥ እንደሌለባት ማወቅ ትችላለች - አማራጮችን የምትለካበት ሚዛን አላትና። ስኬታማ የልብስ ዲዛይነር ለመሆን ራእይ የሰነቀ ወጣትም፤ በእርሻ ሳይንስ የመሰልጠንና የመስማራት ግብ ሊኖረው አይገባም - በዲዛይን ጥበብ የመሰልጠን ግብ እንጂ።

የራሳችንን ሃላፊነት ወደሌላ ስንገፋ የሕይወት ክህሎታችንን በአንጭጩ እየቀረ ይዳከማል። ትምህርህት ቤት ወይም ሌሎች ሰዎች የሚረዱን፤ በራሳችን ጥረት የህይወት ክህሎትን እንድናዳብር እንጂ ስኬት አምጥተው እንዲያስታቅፉን አይደለም።

- ትምህርት ቤታችን፤ የማትሪክ ፈተና መልሶችን እንዲነግረን ሳይሆን፤ የእውቀት ክህሎት አዳብረን እንዴት ፈተናዎችን እንደምንመልስ የሚረዳን መሆን አለበት።

- ሌሎች ሰዎችም፤ ዘላለም ምግብና ገንዘብ እንዲመፀውቱን ሳይሆን፤ ራሳችን የህይወት ክህሎት አዳብረን እንዴት ምግብና ሃብት መፍጠር እንደምንችል በማስተማር ቢያግዙን ይመረጣል - (ዘላለም ሳይሆን አንዴ ብቻ)።

# 4. በግል ክህሎቱ ይተባበራል እንጂ ክህሎትን ለመጋራት አይሞክርም

በማህበረሰብ ውስጥ በመኖር ከሚከፈቱልን ትልቅ የጥቅም እድሎች መካከልም፣ የተከማቹ እውቀቶችንና ሙያዎችን በቀላሉ ለመማር መቻላችን ነው - የመማር ክህሎትን በመጠቀም። ማንም ሰው እንትን ወይም እንቶን ተከቶ የህይወት ክህሎት መጠቀምና መማር አይችልም። የሚቻል ከመሰለን ግን፤ "የህይወት ክህሎታቸው ተጠቅመው እነእንትና ይጥሩልኛል፣ እነእገሌ ያውቁልኛል" በሚል ስሜት፤ ሁላችንም የግል ክህሎታችንን ሳንጠቀም፣ ሳንጥር፣ ሳናውቅ እንቀራለን።

የተከማቹ እውቀቶችን ስንማር ጊዜያችንን ስለሚቆጥብልን፤ አዳዲስ ተጨማሪ ክህሎቶችን ለመፍጠርና ለማዳበር ምቹ ይሆንልናል። ማኅበረሰብ ውስጥ ስለምንኖር ብቻ፤ የሌሎች ሰዎችን ክህሎት አየር በአየር "የጋራ" ማድረግ የምንችል ከመሰለን ግን ተሳስተናል። የራስ ክህሎትንም፤ "የጋራ" ማድረግ አይቻልም።

የሌሎችን ክህሎት በማየትና በመማር የሚጥር ሰው፤ በየጊዜ የህይወት ክህሎቶችን ማደበር እንደሚችል ግልፅ ነው። ይሁን እንጂ፤ የጋራ ክህሎት የሚባል ነገር የለም። ሕይወት በመጀመሪያ የግላችን ናት። ስንበላ፣ ወሲብ ስናደርግ፣ ስናጠና ወዘተ... የግል አእምሮና አካላችንን ነው የምንጠቀመው። የህይወት ክህሎት የሚዳብረውም በግል ነው።

የየራሳችንን የህይወት ክህሎት የሚያዳብር የየራሳችን ጥረት ለማድረግ መተባበር ይኖርብናል። የአንድ ሰው ክህሎት፣ ያለጥረት አየር በአየር "የጋራ" እንዲሆን የምንጠብቅ ከሆነ ግን፤ በጋራ የምናገኘው ውጤት ክህሎት አልባነትን ነው። የጋራ የሆነ የማንም ሳይሆን ይቀራል - Tragedy of commons።

# 5. በስራ እየበለፀገ፣ አቅሙንም ይገነባል እንጂ አቅሙን አይንድም

አላማውን በፅናት ይዞ አውን ከሚያደርጋቸው ግቦች መከከል አንዱ፣ የህይወት ክህሎትን የመገንባት ግብ እንደሆነ አይተናል። የህይወት ክህሎትን መገንባት፣ ራሱን የቻለ ትልቅና የማያቋርጥ ግብ የሚሆነው ለምንድነው? ምክንያቱም፣ የህይወት ክህሎት፣ ሌሎቹን ግቦችና በአጠቃላይ የህይወት አላማችንን ለማሳካት የሚያስችሉን ብቃቶችን ሁሉ ያካትታል።

በአንድ በኩል በእለት ተእለት ስራችን ውስጥ፣ የህይወት ክህሎታችንን በመጠቀም ስንጥር፣ ውጤታማ ምርትን ወይም ትርፍና ደሞዝን ያስገኝልናል፣ ገቢ እያገኘን እበለፅጋለን። ከጥረታችን የምናገኘው ጥቅም ግን ይህ ብቻ አይደለም። የእለት ተእለት ስራችን፣ ዛሬውኑ ገቢ ለማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ ወደፊት ለላቀ ውጤታማነት የሚያዘጋጅ ተጨማሪ የሙያ ወይም የንግድ ክህሎት ለመገንባት የሚያገለግል መሆን አለበት። ዘንድሮ ትምህርታችንን የምናጠናው፣ እውቀት ለመጨበጥና ጥሩ ውጤት ለማምጣት ቢሆንም፣ የማጥናት ክህሎታችንንም በሚገነባ መንገድ ልናከናውነው ይገባል። የህይወት ክህሎት፣ እንደ ኢንቨስትመንት ነው።

ለዛሬ ኑሮአችን የምርትና የገቢ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግለንን የማምረቻ ፋብሪካ እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ፋብሪካው የማምረቻ አቅም ነው፣ ካሁን በፊት የተገነባ ኢንቨስትመንት። ይህን ኢንቨስትመንት በመጠቀም እናመርታለን፣ ገቢ እንፈጥራለን። ነገር ግን ለተጨማሪ የኢንቨስትመንት ግንባታ መነሻ ልናደርገው ይገባል።

በጊዜና በስራ ብዛት ፋብሪካው ሲያረጅ ዝም ብለን ከተመለከትን፣ የማምረት አቅማችን (ኢንቨስትመንታችን) እየተናደ ይሄዳል - በብልሽት። ስለዚህ በፋብሪካው ስናመርት ለዛሬ የኑሮ ገቢ እንዲያመነጭልን ብቻ ሳይሆን፣ ለነገ ተጨማሪ አቅም የሚፈጥር የኢንቨስትመንት ምንጭ እንዲሆን ማድረግ ይኖርብናል። የህይወት ክህሎትም በተመሳሳይ መንገድ፣ ዛሬ እየተጠቀምንበት ለወደፊትም ኢንቨስት ልናደርግበት የሚገባ ዋነኛ የህይወት አቅም ነው።

የህይወት ክህሎት ግንባታን ቸል የምንል ከሆነ ግን፣ ኢንቨስትመንት እንደራቀው ፋብሪካ ብቃታችን እየተናደ ይሄዳል። የፋብሪካውን ምርት ለእለት ፍጆታ ብቻ እያዋልን፣ ለተወሰኑ አመታት መቀጠል እንችላለን። ከዚያ በኋላ ግን የፋብሪካው የማምረት አቅም ተዳክሞ፣ ለጥገና የሚሆንም አቅምም በማጣት እንቅስቃሴው ይቆማል።

የህይወት ክህሎትን የማይገነባ ሰውም፣ ለተወሰኑ አመታት በእለት ጉርስ እንቅስቃሴውን መቀጠል ይችላል፣ በዚሁ መንገድ መዝለቅ የማይታሰብ ነው። ሁላችንም እንደምናውቀው፣ የእለት ጉርስ ካገኘን፣ ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ፣ የአካላችን እድገትና የእድሜያችን ቁጥር

እየመጨመረ መሄዱ፤ ከሞላ ጎደል ተፈጥሮአዊ ነው።

የወሲብና የመራቢያ አካሎቻችን ከእድሜ ጋር ያድጋሉ፤ ከልጅነት ወደ ወጣትነትና ጎልማሳነት የሚደረገውን ጉዞ፤ ከዚሁም ጋር የሚመጣውን የማርገዝና የማስረገዝ አካላዊ ለውጥ ልናስቆመው አንችልም - በወላጆች ወይም በምፅዋት የእለት ጉርስ ከተገኘ በቂው ነው። ግን እስከ መቼ?

በሃሳብና በተግባር ራስን መቻል፣ ኑሮን ማሻሻልና ንብረት ማፍራት፣ መገበያየትና ጓደኝነት መፍጠር፣ በፍቅር ቤተሰብ መመስረትና ልጅ መውለድ... እነዚህ ሁሉ ሃላፊነትን ይጠይቃሉ። እላማና ግብ መምረጥን፣ ለስኬታማነታቸውም የህይወት ክህሎትን እየገነቡ መስራትን ይጠይቃሉ።

ከሌሎች ሰዎች በምናገኘው እለት ጉርሻ የመራቢያ አካላት ከእድሜያችን ቁጥር ጋር ሊያድጉ እንደሚችሉ እናውቃለን - ተፈጥሯዊ እውነታ ነው። በሚያስደንቅ ሁኔታ ብዙ ዜጎች የማይገነዘቡት ሌላ ተፈጥሯዊ እውነታም አለ። አላማና ግብ መምረጥ፣ ኑሮን ማሻሻልና ራስን መቻል፣ ቤተሰብ መመስረትና መውለድ ... በአጠቃላይ የጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወት ለመጎናፀፍ የሚያስችለን የህይወት ክህሎት ግን በሌሎች ሰዎች የእለት ጉርሻ ሊያድግ አይችልም።

የህይወት ክህሎትም ሆነ፤ የዚሁ ክህሎት እስኳል (ማለትም የማሰብ ክህሎት)፤ በእያንዳንዱ ግለሰብ ምርጫና ውሳኔ ብቻ ነው ሊገነባ የሚችለው። እያንዳንዱ ሰው በመነሻ አቅሙ ላይ ተመስርቶ እያሰበና እያወቀ፣ በየጊዜው እየጣረና እየገነባ... በአጭሩ ኢንቨስት እያደረገ ሲጓዝ ነው - የህይወት ክህሎቱ የሚያድገው። ማሳደግ መፈለጉ ነው። አካላዊ እድገት ከእድሜ ጋር እየጨመረ፤ በህይወት ክህሎት ግንባታ ግን በእንጭጩ ከቀረ፤ በመካከላቸው ከፍተት ይፈጠራል። ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ተበሎ ከሚነገረው አባባል ጋር ይመሳሰላል። ራሱን ማገረመድ ይቅርና ራሱን መደገፍም አቅቶት ይወድቃል - ኢንቨስትመንት የጎደለውን እድገት ነውና (growth and under investment)።

ከሕይወት ክህሎት መጓደል ጋር አብረው የሚመጡ፤ ሃላፊነት የጎደለው ወሲብ፣ ራሱን ችሎ መኖር ያቃተው የ30 አመት ህፃን እና ሌሎች በየእለቱ በርካታ የኑሮ ውጉንቅጦችን ተመልከቱ። በእድሜ አካላችን እያደገ ጣፋጭ ኑሮን ለማጣጣም (« ወተት ለማለብ») ከፈለግን፤ አእምሮን በክህሎት ማዳበር («መቀለብ») የግድ ነው። ሁለቱንም አስተሳስረን መጓዝ እንዳለብን ለማስገንዘብ ነው፤ የሕክምናና የስነአእምሮ ሳይንስ ባለሙያዎች፤ ሁለት አይነት እድሜ እንዳይኖረን የሚነግሩን።

በተለምዶ የሚታወቀው እድሜ (chronological age) በአመዛኙ አካላዊ እድገትን ይወክላል። ሌላኛው እድሜ ደግሞ፤ የአእምሮ ብስለት እድሜ (mental age) ይባላል። 40ኛ እድሜውን ቢደፍንም፤ የአእምሮ ብስለት እድሜው ግን የ10 ሊሆን ይችላል - የህይወት ክህሎትን ሳይገነባ የጎለመሰ ህፃን።

# 6. የትብብር መንገድን እንጂ የመበላላት መንገድን አይሻም

ከሰዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነት ወይም መስተጋብር፤ በአግባቡ ከመራነው ምንኛ ጠቃሚ እንደሆነ አይተናል። በተለይም ከሰዎች ጀግንነት የምናገኘው የአርአያነት ጥቅም እጅግ ትልቅ ነው። በአንድ ሰው አርአያነት መንፈሳችን ተነቃቅቶ፤ የህይወት ከህሎታችንን በመጠቀም የላቀ ስኬት ስናስመዘግብ፤ በተራችን ለሰውዬው አርአያ እንሆነዋለን። በእንዲህ አይነት አነቃቂ ትብብር ወይም አነቃቂ ፉክክር፤ የእያንዳንዳችን ስኬት እየጨመረና እየመጠቀ ይሄዳል።




አላማቸውንና ስራቸውን ከሚያፈቅሩ ሰዎች ጋር የትብብር ግንኙነት ብንመሰርት፤ ይበልጥ ውጤታማና ተጠቃሚ እንደሚያደርገን በመገንዘብ፤ የግብይትና የአጋርነት ትስስር መፍጠር አለብን - ትብብር የመመስረት ከህሎታችንን በመጠቀም።

አጋርነትን መመስረት ባንችል እንኳ፤ አነቃቂ ፉክክርን በመፍጠር የህይወት ከህሎታችንን ይበልጥ ለመጠቀም መንፈሳችንን ማደስ፣ ወይም መብትን እየጠበቁ ተከባብሮ መኖር እንጂ ጠላትነትን መለኮስ የለብንም። አፀፋና የአፀፋ ምላሽ እየተባባልን መተኳኮስና ማጋጋል

(escalation) ማንንም አይጠቅም።

አላማውን ያልዘነጋ ሰው፤ የራሱን አሴት በመፍጠር እንጂ፤ የሌሎች ሰዎችን እሴት በማጥፋት የሚያገኘው ጥቅም እንደሌለ ያውቃል። የራሱን አስደሳች የብልፅግና ህይወት እውን ለማድረግ የሚችለው፤ የሌሎችን ህይወት በማንሳቆልና በማጨለም አይደለም።

ስለዚህ ከቻለ ትብብርን ወይም አነቃቂ ፉክክርን፣ አለበለዚያም በመብት ተከባብሮ በየፊናው መኖርን ይመርጣል፤ መተጋተግን ያስወግዳል። ለዚህም ሲባል፤ በጤናማ ትብብርና በጤናማ ፉክክር ለመነቃቃት፣ እንዲሁም ተከባብሮ ለመኖር የሚያስችል የህይወት ክህሎትን ያዳብራል። በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ወደ መተኳኮስና መተጋተግ እንዳያመሩም፤ ግጭትን የመፍታት ክህሎት ያዳብራል።

# 7. የስኬት ጎዳናን ይጠርጋል እንጂ ስኬት እስኪገደብ አይጠብቅም

አስደሳች የብልፅግና ህይወትን የሚያጎናፅፉ የሙያ መስኮችና ምርጫዎች ብዙ ናቸው። ሁሉንም መሆን አይቻልም። በአስር የሙያ መስክ እንሰማራ ብንል፤ የህይወት ክህሎታችንን በአግባቡ መጠቀም አንችልም።

በሁሉም መስኮች ይበልጥ ውጤታማ እንድንሆንና የላቀ የህይወት ክህሎት ለማዳበር የሚያስችል በቂ ጊዜና ጠንካራ ትኩረት አናገኝም። ቀስ በቀስም፤ አካሄዳችን እድገታችንን የሚገድብ (limit to growth) ይሆንብናል። በሁሉም መስክ ውሱን የህይወት ክህሎት ብቻ በመያዝ፤ ከእለት እለት በማይሻሻል ኑሮ እዚያው ባለንበት መርገጥ እንጀምራለን።

እድገታችን እንዳይገደብ፣ መነሻ አቅማችንንና ዝንባሌያችንን በማገናዘብ፤ የህይወት ክህሎታችንን በአግባቡ በመጠቀም፤ አላማና ግባችንን አስበን መምረጥ ያስፈልገናል። አላማና ግቡቹን የመረጠ ሰው፤ የዛሬውን ጥረት ከረዥም ጊዜ የህይወት ክህሎት ግንባታ ጋር አስተሳስሮ በማየት፤ የማያቋርጥ የስኬት ጎዳናን ይጠርጋል። ስኬትን የሚገድብ ችግር እስኪፈጠር ድረስ አይጠብቅም። 10 ያባረረ አንድ አይዝምና... በተለይ በሙያና በቢዝነስ መረጣችን ላይ በትኩረት ማጤንና በጥንቃቄ መወሰን ይኖርብናል።

# 8. ከስኬት ወደ ሌላ ስኬት ያንደረደራል እንጂ ማስመሰልን አይፈልግም

አንድ ሁለት ብለን እስካሁን የተዘረዘሩት ሃሳቦች የሚተገብር ሰው፤ ውጤታማና ስኬታማ መሆኑ በጭራሽ አያጠራጥርም። በዚያ ላይ ተጨማሪ ስኬት ወይም ሽልማት ይጨመርለታል። መነሻ ክህሎቱን በመጠቀም እየተማረ፤ እውቀትን የጨበጠና ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚሸጋገር ተማሪ ነው ስኬታማ የሚባለው። ግን ከክፍል ክፍል ሲሸጋገር፤ ሽልማትም ይጨመርለታል። እውቀትን ሲጨብጥም እንዲሁ፤ ጎን ለጎን ተጨማሪ የመማር ክህሎት ይዳብርለታል።

ዛሬ ጥራት ባለው ስራና በዋጋ ተመጣጣኝነት ደንበኞቹን እያስደሰተ ገቢ ያገኘ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ጠጋኝ ስኬታማ መሆኑ አያከራክርም። ነገር ግን፤ የዛሬ ስኬቱ ለነገ ተጨማሪ ስኬቶች መንደርደሪያ ናቸው።

ጥራት ባለው ስራ አማካኝነት የሙያ ክህሎቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየገነባ ነው - ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኝ ክህሎት። ዛሬ ያስደሰታቸው ደንበኞችም፤ ነገ ተጨማሪ ደንበኞችና ገቢ እንዲያገኝ መነሻ ይሆኑለታል። ላለው ይጨመርለታል (Succes to the succesful) እንደሚባለው ነው። በስኬት ምህዋር ውስጥ፤ በስኬት ላይ ስኬት እየተጨማመረ መሄዱ አይቀሬ ነው።

**ስኬትን ስኬት ይከተለዋልና!**
**መልካም ስኬት!!**

ECMAP

# ክፍል 5

# ስኬታማ የህይወት ካርታ

# The 5Ps

## ለአዲሱ ሚሊኒየም የሚመጥን

አጥር ምጥን ያለ ስኬታማ የህይወት ካርታ

የተሞከረና በተጨባጭ የሰራ አስተማማኝ መሳሪያ ስለሆነ ይጠቀሙበት

የፍሬውን ማማር በማየት ይለዩታል

የዘራነውን እናጭዳለን ይባል የለ! እውነት ነው።

አእምሯችንን በዝባዝንኬ ካጨቅነው፤ ውጤቱም ያው ነው።
garbage in, garbage out (GIGO)

አእምሯችንን የስኬት መሳሪያ ከታጠቀ፤ የስኬት ምህዋር ይፈጥራል።
Value in, Value out (VIVO)

hGIGO ወደ VIVO እንሸጋገር።

አእምሯች የስኬት መሳሪያ እንዲታጠቅ፣ አስተማማኙን የተግባር ሶፍትዌር ከገፅ... እስከ ... በሰፈረው መሰረት በጥንቃቄ ይጫኑት

ከአሰልቺ ያረጀ ከለሳ፤ ወደ አዲስ የራዕይ ቅየሳ

hRevision ወደ Vision እንኳን ደህና መጡ

# የህይወታችንን ሂደት እናስተካክል

## Life Process Reenginering (LPR)

አንዳንዴ በሰዎች ህይወት ውስጥ፤ ስኬቶች በየጊዜው እየቀረቡ፣ እየጎሉና እየበዙ የሚመጡ ይመስላሉ። ግን ሰዎቹ ናቸው እየገሰገሱ ወደ ስኬቶቹ የሚጠጉትና የሚያጎሏቸው፤ የሚያበራክቷቸው። ችግሮች ደግሞ እየራቁ እየሟሙና እያነሱ ሲጠፉ ታያላችሁ። ግን ሰዎቹ ችግር ሲፈጠርባቸው ስለሚሸሹ አይደለም - ፊት ለፊት ተጋፍጠው ስለሚፈቷቸው እንጂ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ፤ በተቃራኒው ስኬቶች እየራቁና እየደበዘዙ ሲሄዱ ታያላችሁ - ወደ ስኬት ከመራመድ ይልቅ ቆሞ በመጠበቅ ሳቢያ። ችግሮችም እየቀረቡና እየጎሉ ይመጣሉ - ችግሮችን ሳለመጋፈጥ በሸሸን ቁጥር።

### ውስብስብ፣ ዘጊ፣ ጨለማ - የብዥታ ሂደት

የምንመኘው ስኬትና የምንፈልገው ግብ ይኖራል። ግን ከባድና ሩቅ ሊመስለን ይችላል። ለመጠጋትና ለመሞከር በመፍራት ከዳር ቆማችሁ ስትጠብቁ፤ ያ የምትመኙት ስኬትና ግብ በየጊዜው እየራቀና እየተወሳሰበ፣ ቀስ በቀስም መንፈሳችሁን እየተፈታተነ አስጨንቋችሁ አያውቅም? ወይም ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ይልቅ በፍርሃት የምትሸሹት ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰበ፤ እየተበራከተና ህይወታችሁን እያጨለመ የተሰቃያችሁበት አጋጣሚስ ታስታውሳላችሁ?

አዎ፤ ከስኬት እየራቅንና ችግር እየተደራረበብን ህይወታችን ሊወሳሰብ ይችላል - መፍትሄ የሌለው እስኪመስል ድረስ። ግን ደግሞ የተወሳሰበውን ማሳመር፣ የጨላለመውን ማብራት ይቻላል።

### ያማረ፣ አጓጊና ብሩህ - የጠራ ሂደት

ቀረብ ብሎ የመሞከር ድፍረት አጥተን ለረዥም ጊዜ ከቆየን በኋላ፤ ግዴታ ሆኖብን በተግባር ስንሞክረው፤ ጨርሶ እንደፈራነው ከባድ አለመሆኑ ያየንበትና ለስኬት የበቃንበት አጋጣሚምሞልቷል። ያለመፍትሄ የምትሸሹት ችግርም፤ በመጨረሻ ፊት ለፊት ስትጋፈጡት፤ የፈራችሁትን ያህል ከባድ እንዳልሆነ የምታረጋግጡበት አጋጣሚም ብዙ ነው።

"ምነው ድሮውኑ ለስኬትደፍሬ በሞከርኩት ኖሮ!"፤ "ምናለ ከመነሻው ችግሩን ተጋፍጬ

በፈታሁት ኖሮ!" የሚል ቁጭት ይፈጥርብናል። በጭፍን ስሜት ነገሩን አካብጄ ባላየው ኖሮኮ... በፍርሃት ራሴን አቅመ ቢስ ባላደርግ ኖሮኮ... ለካ ህይወት እንዲያ መወሳሰብና መጨለም አልነበረበትም... ለካ አጓጊና ብሩህ መሆን ይችል ነበር... ያስብላል። የህይወት አቅጣጫችንን መቀየር እንችላለና።

## የራሳችን መሪ መሆን

የህይወታችንን አቅጣጫ የምንወስነው (ወይም መሪውን የምናሽከረክረው) ራሳችን ነን። መሪው የተፈጥሯችን አካል ነው። እዚህ ላይ ምርጫ የለንም። መሪው በእጃችን ነው (መሪው በአእምሯችን ነው)። ግን መሪውን መጠቀምና አለመጠቀም እንዲሁም የመሪውን አቅጣጫ መወሰን የእያንዳንዳችን ምርጫ ነው። በዚህም ነው፤ አንዳንዴ ህይወት እንድትጨልምና እንድትወሳሰብ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ በጣም አጓጊና ብሩህ እንድትሆን የምናደርጋት። የህይወትን ሂደት (Life Process ) በአግባቡ የመምራትና ያለመምራት ጉዳይ ነው።

መሪው በእጃችን ስለሆነ፤ በገዛ ራሳችን ህይወታችንን እናወሳስበዋለን። ለምሳሌ በተግባር ከመሞከር ይልቅ በፍርሃት ከስኬት እየራቅን፤ ችግር ሲፈጠርም ፊት ለፊት ተጋፍጦ ከመፍታት ይልቅ እየሸሸን፤ የህይወት ሂደታችንን እናበላሻለን። ሌላ ጊዜስ፤ የጠበቅነውን ያህል ስኬት እንደማይከብድ፤ ችግርም እንደፈራነው እንደማያስቸግር በተግባር የምናየው ለምን ይሆን? በአንዳች ተአምር አይደለም። መሪው በእጃችን ስለሆነ፤ የህይወት አቅጣጫችንና ጉዟችንን ለዘለቄታው ማሳመር እንችላለን - ይሄው ነው መሰረታዊ የህይወት ሂደት ለውጥ ማለት - Life Process Reenginering (LPR)።

ጥንቅራዊ አስተሳሰብ (ST)፤ ምሉእነትን የሚያጎናፅፍ የተግባር መሳሪያ ነው የምንለው አለምክንያት አይደለም። ከየትኛውም የህይወት ገፅታ በመነሳት ጥንቅራዊ አስተሳሰብን በመመርመር፤ ይህን እውነታ መገንዘብ ይቻላል። ከህይወት ግብ አንፃር መርምረነዋል። ከህይወት ከሀሎት አንፃርም አይተነዋል። አሁን ደግሞ ከህይወት ሂደት አንፃር እንፈትሸዋለን። መሰረታዊ የህይወት ሂደት ለውጥ (ኤልፒአር) የምንተገብርበት መሳሪያ መሆኑንም እናያለን።

ለለውጥ ለመነሳትና መሳሪያዎችን ለመጠቀም፤ በቅድሚያ የህይወት ሂደትን አንጥረን ማውጣትና ማየት ይኖርብናል። ትክክለኛውን የህይወት ሂደት በግልፅ ፍ ብሎ እንዲታየን ማድረግ ከቻልን፤ ከዚያ በኋላ አያከብድም። በቁጥጥራችን ስር ያለውን መሪ እያሽከረከርን በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች የህይወት ጎዳና እየገነባን መገስገስ ነው። ስለዚህ የህይወት ሂደትን (Life Process) አንጥረን ለማየት አይናችንን እንክፈት። ካርታው ከፊታችን ተዘርግቷል - ይህን የሂደት ( Process) ካርታ፤ ትልቁ "P" ብለን እንሰይመው።

ትልቁ "P"፤ የህይወትን ሂደት አንጥረንና አጠናቅረን የምናይበት ካርታ ስለሆነ፤ ዋና ዋና ነገሮች በፈርጅ እአደራጅቶ የያዘና መስተጋብራቸውንም ያጠናቀረ አትላስ ነው። ካርታው በአምስት ሂደቶች ተቀናብሯል።

## አምስቱ ዋና ዋና - 5ቱ "P"

1. እውኑን ተፈጥሮ የምንገነዘብበት ሳይንሳዊ አመለካከት (philosophy)፤
2. ሀልወናን ለማለምለም ያነጣጠረ አላማ (Purpose)፤
3. ተጨባጭ ውጤታማ ስራ (Productiveness)፤
4. አስደሳች የህይወት ብልፅግና ስኬት (Prosperity) እና
5. አነቃቂ አዳኝ ስብእና (Positive Personality)።

5ቱ "P" ልንላቸው እንችላለን። እነዚህ አምስት ሂደቶች በተራቸው በሶስት በሶስት ንኡስ ሂደቶች የተቀናበሩ ናቸው። አንደኛ በሃሳብና በተግባር ደረጃ ይዘረዘራሉ። ሁለተኛ በስሜትና በመንፈስ ደረጃ ይመነዘራሉ። ሶስተኛ ከሌላ ሰውና በማህበረሰብ ውስጥ በሚኖር ግንኙነት ደረጃ ይተረጎማሉ። (ተጨማሪ 15P ማለት ነው)

## በስሜትና በመንፈስ ደረጃ

1ሀ. በእውን ያለ ዝንባሌ ወይም አቅም (potential)
2ሀ. የአላማ ፍቅር (passion)
3ሀ. የስራ አይበገሬነት (perseverence)
4ሀ. የስኬት ደስታ (Pleasure)
5ሀ. አነቃቂ የራስ ክብር (Pride)

## በሃሳብና በተግባር ደረጃ

1ለ. በእውነታ የተመሰረተ መርሀ (Principle)
2ለ. የአላማ እቅድ (plan)
3ለ. የስራ ብቃት/ሙያ (profeciency)
4ለ. የስኬት ፍሬ (Property)
5ለ. አነቃቂ ኪነጥበባዊ ምስል (Power-up Art)

## በሃሳብና በተግባር ደረጃ

1ሐ. እውን ሰዎች (people)፤
2ሐ. የአላማ መፈቃቀድ (persuation)፤
3ሐ. የስራ ትብብር (partnership)፤
4ሐ. የስኬት ትርፋማነት (Profit)፤
5ሐ. አነቃቂ የሚደነቅ አርአያ (Praiseworthy)

# ሃያዎቹ "ፒ"

የህይወታችን ሂደት በአጠቃላይ፤ በአምስቱ ዋና ሂደቶችና፤ በአስራ አምስቱ ንኡስ ሂደቶች የተጠናቀረ ነው - በድምር ሃያ ናቸው (20 "ፒ"ዎች የምንላቸው)።

| ዋና ሂደቶች | በሃሳብና በተግባር ሲመነዘሩ | በስሜትና በመንፈስ ሲመነዘሩ | በግንኙነትና በማህበረሰብ ሲመነዘሩ |
|---|---|---|---|
| philosophy - science | Principle | potential | people |
| Purpose | plan | passion | persuation |
| Productiveness | profeciency | perseverence | partnership |
| Prosperity | Property | Pleasure | Profit |
| Positive Personality | Power-up (Art) | Pride | Praiseworthy |



MAP

# የህይወት ካርታ

በህይወት ካርታ ውስጥ የተካተቱትን ነገሮች (ሀንፃዎች፣ ጎዳናዎች፣ የማመንጫ ማእከሎች፣ መነሃሪያዎችና የመዝናኛ ስፍራዎችን) ... ገና በወጉ ባንነሸራሽርባቸውም፣ ስያሜያቸው ደርሰናል። እንግዲህ ሽርሽር መውጣታችን ነው።

መጀመሪያ ላይ፣ የህይወት ካርታው አዲስ ሆኖብን፣ ትንሽ ብንደነቃቀፍና ብንደነጋገር አይከፋንም አይደል? በአጭር ጊዜ ውስጥ የመዳፋችንን ጣቶች ያህል ካርታውን አብጠርጥረን ከራሳችን ጋር ስናዋህደው እንደልባችን ወደ መንሸራሸር እንሻገራለን። ስለዚህ አካሳችን ትንሽ ቢንቀራፈፍ አትሰላቹ። በህይወት ካርታ ላይ በዝግታ ጉዟችንን እንጀመር። አለማችን እና ህይወታችን ውጥንቅጥ እንዳልሆኑ ወዲያውኑ በማረጋገጥ ፍጥነታችንን እንጨምራለን።

## ውጥንቅጥ አለም?

የህይወት አለም ውስጥ ብቅ እንዳልን፣ ወዲያውኑ የሚያጋጥመን ነገር ቢኖር... "ያንተ ያለህ! የእውኑ ተፈጥሮ አይነትና ቁጥር አበዛዙ!" ያስብላል። የድንጋዩና የአፈሩ (ባልጩቱ፣ እብነበረዱ፣ ኖራው፣ አሸዋው፣ ቀዩ አፈር፣ ጥቁር አፈሩ...) ቁጥሩ የትየለሌ ነው። የዛፉና የቅጠሉ (የግራሩ፣ የባህርዛፉ፣ የዋንዛው፣ የፅዱ፣ የበቆሎው፣ የሰንዴው፣ የሰላጣው፣ የሸንኩርቱ....)፣ የእንስሳውና የነፍሳቱ፣ የፈሳሹና የአየሩ፣ የጂረቁና የእርጥቡ፣ የተንሳፋፊውና የዝቃጩ... ቁጥሩ ከመብዛቱ የተነሳ፣ ግራ ያጋባል።

መጠኑና አኳሃኑም እንደዚያው ብዙ ነው። ሌሎች ነገሮችን ሁሉ ትተን፣ ፈሳሾቹን እንኳ ብንቃኝ...፣ ኖኖ... ሌሎቹን ፈሳሾች ትተን ውሃን ብቻ ብንመለከት፣ ኖኖ... ከላይ የሚዘንበውንና ከመሬት ስር ያለውን ውሃ ትተን፣ በቅርባችን ያሉትን ብቻ ... ለዚያውም የደፈረሰውን፣ የተበከለውንና ሌላውን ትተን የጠራውን ውሃ ብቻ በየቦታው ብናይ የመጠንና የአኳሃን ብዙቱ_ ከቅንጣት ጠብታና ከአንድ ጉንጭ ውሃ ጀምሮ፣ በብርጭቆና በጆግ፣ በጀሪካንና በገንዳ፣ እስከ ግድብና ሰፊ ሃይቅ ድረስ... ለቁጥር የሚያስቸግር የመጠን ልዩነት።

አኳሃናቸውን እዩ፣ ከቅጠል፣ ከቧንቧ፣ ከጣሳ፣ ከፀጉር... የሚንጠባጠብ፣ የሚርከፈከፍ፣ የሚንቀረቀር፣ የሚንቦጫቦጭ፣ የሚጎርፍ፣ የሚፍለቀለቅ... አኳሃኑ ብዙ ነው። ስትነኩት የሚቀዘቅዝ፣ የሚሞቅ፣ ስትቀምሱት የሚጥም የሚከብድ፣ ስትሰሙትም ....።

የውሃ ነገር ብቻ ቁጥሩ፣ መጠኑና አኳሃኑ የትየለሌ! ሌሎች ፈሳሽ ነገሮችን ስናይ፣ ከፈሳሽ በተጨማሪ ጠጣርና ግኡዝ ነገሮች፣ ተቆጥረው የማያልቁ አፀዋትና እንስሳት ሲጨመሩበት፣ በዚያ ላይ የሰው ነገር ሲታከልበት... ነገር አለሙ ሁሉ ተደበላልቆብን በብዥታ ይፈታተነናል። ግን ጨለማና ብዥታ አይወርሰንም። ከህይወት ካርታ ውስጥ፣ የምናገኘው የመጀመርያው ስፍራ ብዥታንና ጨለማን የሚያባርር ነው።

# 1. Philosophy (ፍልስፍና/ አመለካከት)

የምንገበኘው "የአመለካከት ግቢ"፤ አንዳንዶች የብርሃን ተራ ወይም መነፅር ተራ ይሉታል። ከሻማ ጀምሮ እስከ ፀሃይ ድረስ የተለያዩ የብርሃን ምንጮችን የሚያፈልቅ ዋና ማዕከል ነው። የሩቁን አቅርበው ወይም ደቃቃውን አጉልተው የሚያሳዩ መነፅሮችም ሞልተዋል። ይህን ቦታ የጎበኘ ሰው ሁሉንም ነገር በግልፅ ማየት ይችላል።

## ስርአት ያለው አለም

በእውኑ ተፈጥሮ፤ የነገሮች ቁጥር፣ መጠንና አኳሃን ከመብዛቱ የተነሳ የሚያደናግር ቢመስልም፤ ከእንግዲህ ጨለማና ብዥታ የለም። ነገር አለሙ ሁሉ ድብልቅልቁ የወጣ ውጥንቅጥ እንዳልሆነ ፍንትው ብሎ ይታየናል። ቦግ ባለው ብርሃን፤ ነገሮቹን እያነፃፀርን ማየት ጀምረናል - በመነፅሮቻችን። ለካ፤ እውኑ ተፈጥሮ... ስርአት የያዘ ነው። ሁሉም ነገር በየራሱ ተፈጥሮአዊ ባህርይ እንዳለው ይገብቶናል። ተመሳሳይነትንና ልዩነትን በሚያሳይ መነፅር እውኑን ተፈጥሮ መመልከት ስንጀምር፣ ሁሉንም ነገር በመልክ በመልኩ፣ በፈርጅ በፈርጁ ማደራጀት እንችላለን - ስያሜ እየሰጠን። ሳይንሳዊ አመለካከት ማለት ከዚህ ይነሳል - የመጀመሪያው "P" ነው - Philosophy።

የፍልስፍና ስራ (የሳይንስ ስራም ጭምር) ምን መሰላችሁ? ነገሮችን መመርመር፣ ማነፃፀር፣ ተመሳሳይነትና ልዩነትን እያገናዘ በፈርጅ በፈርጅ ማደራጀት ነው። እውኑ ተፈጥሮ ህይወት ያላቸውና የሌላቸው (ህያዊ እና አልህያዊ) ተብሎ በሁለት ፈርጅ እንደሚደራጅ በሳይንስ ከፍለጊዜ ህፃናት ሲማሩ፤ አለም ሁሉ በአዲስ ብርሃን ቦግ ብሎ የተገለጠላቸው ይመስላቸዋል። አለምክንያት አይደለም። በህያዋንና በግኡዛን መካከል ያለው ልዩነት ምን ያህል በጣም ወሳኝ እንደሆነ አስቡት። ህይወት በሌለበት ቦታ፤ ፍልስፍና፣ ሳይንስ፣ አላማ፣ ስኬት፣ ደስታ፣ እርካታ... ብሎ ነገር የለም።

## ህያውነት - የህይወት ሂደት

ከግኡዛን የሚለዩበት የህያዋን የጋራ ባህርያቸው (ምንነታቸው)፤ ሌላ ሳይሆን ህይወት የምንለው ነገር ነው። ህልውናን ለማለምለም ያለመ ከራስ የሚመነጭ ቀጣይ ሂደት ነው ህይወት። ህያዋን በዚህ ይመሳሰላሉ። ነገር ግን፣ ህያው መሆን ማለት ሁልጊዜ ለዘላለሙ በህልውና ይቀጥላል ማለት አይደለም።

## ህይወት ምንን ይጠይቃል?

ግኡዝ ነገሮች መልከና ይዘታው ይቀየር እንደሆነ እንጂ፣ ሁሌም ይኖራሉ። ህያዋን ግን፤ ተስማሚ ሁኔታ ሲሟላ ብቻ ህልውናቸው ይለመልማል - የተስተካከለ የህይወት ሂደት

ሰው ምርጫ ነው። አውቶማቲክ እውቀትና ሃሳብ የለም። አውቶማቲክ ስራና ፈጠራም የለም። ህልውናውን ማለምለም የሚፈልግ ሰው፤ አቅሞቹን ለመጠቀም የመምረጥ አቅም አለው፤ ስኬታማ የህይወት ሂደትን ይመርጣል። ህልውናውን ማለምለም ካልፈለገም፣ አቅሞቹን ላለመጠቀም የመምረጥ አቅም አለው፤ በምርጫውም የህይወት ሂደትን እያወሳሰበ ያሰናክላል።

ከላይ የተዘረዘሩት አስደናቂ አቅሞች በሙሉ፤ በአእምሮ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው። ለትክክለኛ እውቀትና ሃሳብ፤ የአእምሮ አቅምን መጠቀም ወይም ማሰብ ያስፈልጋል። ሙያንና ስራን ውጤታማ ለማድረግ፤ የአእምሮ አቅምን መጠቀም ያስፈልጋል (ማሰብ)። የመምረጥ አቅምም፤ የአእምሮ አቅም ነው፤ የማሰብ አቅም ነው። ስለዚህ የሰው ህይወት ዋነኛው መሰረት፤ አእምሮ ነው። የህይወት ሂደት ዋነኛ ማጠንጠኛም፤ የአእምሮ ስራ ነው - ማሰብ (thinking)። ይህን አቅም መጠቀምና አለመጠቀም በራስ ምርጫ ይወሰናል።

የየግል እንጂ የጋራ አእምሮ እንደሌለ ግልፅ ቢሆንም፣ ከዚህ ተፈጥሯዊ እውነታ በሚቃረን ጭፍን እምነትና ሃሳብ እየተነዱ፣ "የግድ እንደኔ አስብ፤ የግድ የእኔን ውሳኔ ተቀበል፤ የኔ ሃሳብና ውሳኔ የግድ የጋራ ሃሳብና ውሳኔ መሆን አለበት" የሚሉ ሞልተዋል። የአእምሮ አቅማችንን እንዳንጠቀም ለመከልከል (የህልውና መሰረታችንን ለማፍረስ) ይሯሯጣሉ።

ሰዎች አእምሯቸውን እንዳይጠቀሙ የሚያፍን ጭፍን እምነትና ኋላቀር ባህል ሲኖር፣ የሰዎች ግንኙነት እንደአውሬ በአእምሮ ቢስ ጉልበትና ጥቃት ላይ የተመሰረ ይሆናል። እናም ሰዎች በጦርነት ይተላለቃሉ። የአእምሮ አቅምን ለመጠቀም አለመምረጥና አውሬያዊ የጉልበት ጥቃት እርስበርስ የተሳሰሩ ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ተፈጥሯዊ የአእምሮ አቅምን ለመጠቀም የመረጡ ሰዎች፣ አእምሮና ምርጫ፣ አካልና ህይወት የግል መሆናቸውን በማገናዘብ፣ በፈቃደኝነትና በምርጫ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እየፈጠሩ በስልጣኔና በብልፅግና ይገሰግሳሉ።

## የትኛውን ነው የምንሻው? ህይወትን እንምረጥ

ስልጣኔና ኋላቀርነትን፣ ብልፅግናና እልቂትን፣ ሰላምና ጦርነትን በእኩል አይን እናያቸዋለን? ለህይወት ደንታ ከሌለን፣ አዎ። ከሁሉም በላይ ህይወትን የምናከብር ከሆነ ግን፣ ጥሩና መጥፎውን እየለየን መመዘን ይኖርብናል። የአእምሮ አቅምን በመጠቀም የየግላችንን ህይወት መምራት፣ ከዚህም ጋር በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሰዎች ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ ሊኖርብን ነው።

ህይወትን ለማክበር ካልመረጥንስ? እንግዲህ፣ መልካም የህይወት ሂደት ለመምራት ካልመረጥን...፣ በቃ ምንም አያስፈልገንም። ለመኖር እንጂ ላለመኖር ደግሞ ምን ያስፈልጋል? ምንም አያስፈልግም።

መልካም የህይወት ሂደት ለመምራት ከመረጥን ግን፣ እንቀጥል። ስለእውነት ተፈጥሮ ምንነቶች ተነጋግረናል። ስለእያንዳንዳችን ተፈጥሯዊ አቅም ተነጋግረናል። ስለሰዎች ተፈጥሮም ተነጋግረናል። አሁን በእነዚህ እውቀቶች ላይ በመመስረት፣ የሂይወት ሂደታችንን ለመምራት ወደሚያስችሉን መርሆች እንሸጋገር።

# 1ኛ. Principle (መርህ)

ከእውነተ ተፈጥሮ ጋር ወይም በአካባቢዬ ካሉ ነገሮች ሁሉ የማኖረኝ ግንኙነት ምን አይነት ነው፣ በየቀኑ የምናያቸውን እውነታዎችንና አዳዲስ መረጃዎችን "እይቶ እንዳላየ" ሳያሸቀነጥርን፣ ድር ባእንድ አጋጣሚ በየዝነው ጭፍን እምነት መነዳት ይኖርብናል?

ይስ ዘወትር የምንመለከታቸውን ነባራዊ ተፈጥሮአዊ እውነታዎችና መረጃዎችን እየ ፍን፤ በእሁኗ ቅፅበት የሚያሩ የመን ሰው ይዘን በጭፍን ስሜት መፈርጠጥ አለብን?

# A. እውኑን ተፈጥሮ በአወንታ (ምርምር፣ ፈጠራና ብሩህነት)

እውኑ ተፈጥሮ በአንዳች "ተአምር"፣ በጭፍን "አምነት" ወይም በስሜታዊ "ምኞት" የማመራ አይደለም። ሁሉም ነገሮች የየራሳቸው ምንነት አላቸው።

አነሩ ድንገት ድንጋይ አይሆንም፤ ውሃው ድንገት ወተት አይሆንም፤ ኪኩ ድንገት ኩበት አይሆንም። በ"ጥንቆላ" ወይም "በህዝብ ውሳኔ" አይታዘዙም። በቃ ተፈጥሯቸው ነው። እኔን ለማስተየም በአምቢተኝነት ወይም እኔን ለማስደሰት በታዛዥነት ተፈጥሮአዊ ምንነታቸውን በምርጫ የሚወስኑ አይደሉም።

ተፈጥሯዊ እውነታዎችን ስንመለከት፣ በአወንታ መገንዘብ እንጂ፤ መቃወም ወይም መደገፍ፣ ማውገዝ ወይም ማወደስ ትርጉም አልባ እንደሆነ እስተውሉ። ከተፈጥሮአዊ እውነታዎች ጋር መፍጠር ያለብን ትክክለኛ ግንኙነት፤ በእስተዋይነት የመመልከት፣ በአወንታ እያገናዘቡ የተቀናበረ እውቀት የመገንባት ግንኙነት ነው።

የማገናዘቢያ መሳሪያችንም እእምሯችን ስለሆነ፤ እስደሳች የብልፅግና ህይወትን ከፈለግን፣ ዋነኛው ምርጫችን "አእምሮን በአግባቡ መጠቀም" የሚል መሆን አለበት። ይህን ምርጫ ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመፈተሽ፤ መልካም መርሆዎችን አንድ በአንድ እንጥረን ማየት እንችላለን።

## መርህ 3 ፅናት (Integritiy)

በአንድ ጉዳይ ዙሪያ እውነተኛ ሃሳብ (እውቀት) መያዝ፤ እዚያው በዚያው ትክክለኛ ድርጊት እንድንፈፅም ያደርገናል ማለት አይደለም። እውነተኛ ሃሳብ (እውቀት) ለመጨበጥ ጥረት እንደሚያስፈልገው ሁሉ፤ ያንን ሃሳብና እውቀት በተግባር ለመተርጎምም ጥረት ያስፈልገዋል።

በስንፍና ወይም በፍርሃት፤ በተፈጥሯዊ ተግዳሮት ወይም በሰው ሰራሽ ፈተና ሳንበገር፤ በእውቀታችን መሰረት ተግባራችንን የመምራት ፅናት ማዳበር አለብን። ለእውነታ ታማኝ የመሆን አስተዋይነት (rationality) ያስፈልገናል። ይህን መርህ በአዲስ አቅጣጫ ይበልጥ እንድንገነዘበው ይረዳናል - የፅናት መርህ። እውነታ ላይ ተመስርተህ እውቀት መገንባት፣ በእውቀት ላይ ተመስርተህ መምረጥና መወሰን፤ በውሳኔህ ላይ ተመስርተህ መፈፀም ... ከተጨባጭ ተግባር አንፃር ለእውነታ ታማኝ መሆን ማለት ይሄው ነው። ያኔ የሚያቆምህ ሃይል አይኖርም፤ ድርጊትህና ተግባር የእውነታ ውጤት ነውና።

## መርህ 4 ታታሪነት (Industriousness)

ከተፈጥሮአዊ እውነታዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነት፤ በአስተዋይነት የመመልከት፣ በእውነታ የማገናዘብና የተቀናበረ እውቀት የመገንባት ግንኙነት ነው ብለናል - (rationality)። ከእውነታ ላይ የተመሰረተ እውቀትና ሃሳብ የሚኖረን በዚህ መንገድ ብቻ ነው። ፅናት (integrity) ደግሞ፤ እውቀታችንን (እውነተኛ ሃሳቦቻችንን) በተግባር የመተርጎም ብቃት ነው። እነዚህን መርሆች ከተጨባጭ ኑሯችን አንፃር እንጥረን ስንመለከታቸውስ?

መልከም ኑሮ ማለት ሌላ ሳይሆን፤ እሴት (value) መፍጠር ማለት ነው። በእውቀታችን መጠን፤ በአካባቢያችን የሚገኙ ተፈጥሯዊ ነገሮችን በአዲስ ቅንብር እያደራጀን ለህይወት ተስማሚ እናደርጋቸዋለን። ድንጋዩን በብረት ጠርበን፣ ሲሚንቶ ቀብተን፣ ድንጋይ እየደረብን.... (እያቀናበርን) ህልውናን የሚያለመልም ቤትና ህንፃ፣ መንገድና ድልድይ እንፈጥራለን።

በእርግጥ የድንጋይ፣ የብረት፣ የሲሚንቶ ተፈጥሯዊ ምንነቶችን እንደ አዲስ አንፈጥርም። በአዲስ መልክ ሳናቀናብራቸው ድንጋይ ብረትና ሲሚንቶ "በራሳቸው ጊዜ" ተቀናብረው ህንፃ እንዲሆኑ አዲስ ተፈጥሮ አልሰጠናቸውም። ነባሩን ምንነታቸው አንቀይርም። አንችልምም።

ነገር ግን ተፈጥሯዊ ማንነቶችን በእውነታ በማገናዘብ፤ ካሁን በፊት ያልነበረ አዲስ ቅንብር የመፍጠር አቅም አለን። ይህን አቅም ሙሉ ለሙሉ ለመጠቀም መምረጥ ነው፤ ውጤታማ ታታሪነት። ለህይወት የሚመች መኖሪያ ቤት በተፈጥሮ ተገንብቶ አይጠብቀንም - በተፈጥሮ ምንነቶች መሰረት እያቀናበርን እንገነባዋለን እንጂ።

## መርህ 5 የራስ አክብሮት (Pride)

አእምሮ እና አካል በሚሉ ሁለት ፈርጆች ሊቀመጡ የሚችሉ አራት የቅዱስነት ወይም የጀግንነት መርሆችን አይተናል። ነገር ግን፤ በሰው ህይወት ውስጥ አእምሮና አካል ለየብቻ የተነጣጠሉ ነገሮች አይደሉም። የሰው ህይወት የአእምሮና የአካል ጥንቅር እንደመሆኑ መጠን፤ የጀግንነት መርሆዎቹም በጥንቅር መዳበር ይኖርባቸዋል። በዚህ መንገድ ነው፤ ምልአትን የተጎናፀፈ ስብእና የምንገነባው፤ ብሩህ መንፈስ የምንቀዳጀው።

ዛሬ ያለንበት ደረጃ ምንም ሆነ ምን፤ በየቦታውና በየጊዜው የሚያጋጥሙ ተፅእኖዎችና ማበራታቻዎች ምንም ሆኑ ምን፤ እያንዳንዱ ሰው የህይወት አቅጣጫውን የመምረጥና የመወሰን አቅም አለው። በሌላ አነጋገር የአእምሮና የአካል አቅሞቹን አዋድዶ ለመጠቀም መምረጥ ይችላል። መምረጥም ይገባዋል።

በሌላ አገላለፅ፤ የጀግንነት መርሆቹ በህብር እንዲጎለብቱ ራእይ ሰንቆ፤ በጥልቅ ፍቅር መልካም ስብእና እውን እንዲሆን በራስ የመተማመን መንፈስ መገንባት ያስፈልጋል። መልካም ስብእናን እውን ማድረግ እችላለሁ፤ አደርገዋለሁም በሚል መንፈስ የሚገለፀው መርህ፤ የራስ አክብሮት ይባላል።

## መርህ 6 ወኔ (Courage)

የመልካም ስብእና ግንባታ የህይወት ዘመን ኑሮ እና ራእይ ነው - አሁን እየኖርከው፤ ወደፊትም የምትገነባው። በአሁኑ ወቅት ገና ባልዳበረ ስብእና ውስጥ ብዙ እንቅፋቶች፣ ተፅእኖዎችና ተግዳሮቶች በእጅጉ ፈታኝ ሊሆኑብን ይችላሉ። ወደፊት በአመታት ጥረት እውን እየሆነ የሚመጣው ራእያችን ደግሞ፤ በጣም ርቆ እየታየን ይፈታተነን ይሆናል።

ነገር ግን ከመልካም ስብእና ውጭ ሌላ የስኬት መንገድ ስለሌለ፤ የቅርቡን ተግዳሮት የምንቋቋምበት የሩቁን ራእይ አጥብቀን የምንይዝበት ወኔ ያስፈልገናል። ሰው ከንቱ ነው፣ እኔ ከንቱ ነኝ የሚል ውርደትን በጭራሽ አለመቀበል ነው - ወኔ።

---

### የመጀመሪያዎቹ ስድስት መርሆች

| ፈርጅ 1 - አእምሮ (እውቀት እና ሃሳብ) | ፈርጅ 2 - አካል (ስራ እና ተግባር) | ፈርጅ 3 - ስብእና (መንፈስ እና ስሜት) |
|---|---|---|
| አስተዋይነት (rationality) | ፅናት (Integrity) | የራስ አክብሮት (Pride) |
| ቅንነት (honesty) | ታታሪነት (Industriousness) | ወኔ (Courage) |

ስለዚህ፤ ህልውናን ማለምለም የምንፈልግ ከሆነ፤ ሚዛን ሊኖረን ይገባል። ህይወትን የሚያጠወልጉ ጭፍን እምነቶችና የተሳሳቱ ሃሳቦች፤ መጥፎ ልማዶችና አጥፊ ተግባሮችን ለይተን ለማወቅ፤ ከዚያም ለመቃወም፣ ተጠያቂውንም ሰው ለመገሰፅ፣ ከባሰበትም ለማውገዝ የምንችልበት ሚዛን ያስፈልገናል። ተጨባጭ እውቀቶችና ትክክለኛ ሃሳቦችን፣ ጥሩ ሙያዎችና ጠቃሚ ተግባሮችን ደግሞ ለመደገፍ፣ ባለቤቱንም ሰው ለማወደስ የምንችልበት ሚዛን ያስፈልገናል።

ተፈጥሮአዊ አቅሞችና ምርጫ የግል የሆኑትን ያህል፤ የጥፋትና የስኬት ባለቤትነትም የግል ነው - እንደየተሳትፏቸው መጠን። መልካምና ፀያፍ ስብእናም የግል ናቸው። የአንዱ ተጨባጭ እውቀት ወይም ጭፍን እምነት፣ በአንዳች ተአምር የጋራ ሊሆኑ አይችሉም። "ስለዚህ..." ብለን ወደ መርሆዎች እንሸጋገራለን።

## መርህ 7 — መማር (Learning)

ከማህበራዊ ህይወት ውስጥ ልናገኝ ከምንችላቸው ጥቅሞች መካከል ዋናውና ትልቁ፤ ትምህርት ነው። የተከማቹ እውቀቶችንና የዳበሩ ሙያዎችን በአጭር ጊዜ በመጨበጥ ለተጨማሪ የእውቀትና የሙያ እድገት ትልቅ አቅም መገንባት እንችላለን - በትምህርት።

በእርግጥ ትምህርት ማለት፤ "መደበኛ ትምህርት" ማለት ብቻ አይደለም። መደበኛ ያልሆኑ ስልጠናዎችን መከታተል፣ መፃህፍትን ማንበብ፣ በተለያዩ ዘዴዎች ሃሳቦችን መለዋወጥና መወያየትም፣ መመካከርና መለማመድ... እና ሌሎች የመማሪያ መንገዶችን መጠቀም ይኖርብናል።

ነገር ግን፤ መማር ማለት ከፍል ውስጥ ወይም በውይይውት ወቅት የሰማነውን ሃሳብ ሁሉ በጭፍን መቀበል ማለት አይደለም። መፅሃፍ ላይ ወይም በኢንተርኔት ያነበብነውን ሁሉ በጭፍን ማመን ማለትም አይደለም። ሃሳቦችን ከእውኑ ተፈጥሮ ጋር ለማገናዘብ፤ ትክክል የሆኑትንና ያልሆኑትን ሃሳቦች ለመለየት ማሰብን ይጠይቃል።

## መርህ 8 — ራስን መምራት (Independence)

ለመማርም ሆነ ለማወቅ፤ ማሰብ ያስፈልጋል ብለናል። ሌላ ሰው አንቺን ተከቶ ሊያስብልሽ አይችልም። ግን ሌላ ሰው አንተን ተከቶ ሊማርልህ አይችልም። ከትምህርቱና ከውይይቱ የምታገኛቸው ሃሳቦች ከእውኑ ተፈጥሮ ጋር የሚጣጣሙ ተጨባጭ እውቀት መሆናቸውን ለመለየት፤ የጭፍን እምነት ሃሳቦች እንዳይሆኑ ለማረጋገጥ፤ እያንዳንዱ ሰው ማሰብ ይጠበቅበታል።

ከእውኑ ተፈጥሮ ጋር እጣጥሞ አእምሮውን "ፕሮግራም" ማድረግ የሚፈልግ ሰው፤ በራሱ አእምሮ መመራት አለበት። አለበለዚያ፤ ሌሎች ሰዎች በዘፈቀደ አእምሮህን ፕሮግራም ያደርጉታል። አእምሮህ፤ እንዳበፈለጋቸው የሚጠመዝዙት ጨርቅ፣ እንዳሰኛቸው የሚያሾሩት እንዝርት እንዲሆንላቸው በታዛዥነት የሰዎች ጥገኛ ተከታይ ጭቃ፣ እንዳሻቸው የሚጨፈልቁት መሆን የለብህም። የህይወትህ መሪ በእጅህ (በአእምሮህ) ነው፤ ራስህን ምራበት።

ጥገኛና ተከታይ አለመሆን ማለት፤ አፈንጋጭ ወይም አስከታይ መሆን ማለት አይደለም። እንዲሁ ለማፈንገጥ ያህል ወይም አስከታይ ለመሆን ብቻ የምትሄድ ከሆነ፤ ራስህን እየመራህ አይደለም። በሰዎች እየተመራህ ነው። የሰዎችን አቅጣጫ እያየህ (እየተመራህ) በተቃራኒው መንገድ ትሄዳለህ፤ ወይም ተከታይ አገኝበታለሁ ወደምትለው አቅጣጫ ታመራለህ።

ራሱን የሚመራ ሰው ግን፤ ጥገኛ ወይም አፈንጋጭ፤ ተከታይ ወይም አስከታይ ለመሆን አይደለም ፍላጎቱ። እውኑን ተፈጥሮ ማወቅና መማር ነው ፍላጎቱ። ለዚህም አእምሮውን ይጠቀማል። ከሰዎች የሚማረውንና የሚሰማውን ሃሳብ በጭፍን አይቀበልም፤ በጭፍን አይጥልም። ትክክለኛውንና የተሳሳተውን ሃሳብ ከእውኑ ተፈጥሮ ጋር እያመሳከረና እያየ፤ ከሰዎች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ያስተካክላል - ራስን መምራት በሚለው መርህ።

## መርህ 9 ንግድ (Trade)

ትምህርት፣ ስልጠናና ውይይት፣ በማህበረሰብ ውስጥ ከምናገኛቸው ከፍተኛ ጥቅሞች መካከል ናቸው። በምርት ደረጃ ደግሞ፣ ንግድን የመሰለ ትልቅ ጥቅም እናገኛለን - በማህበረሰብ። ስራን ተከፋፍሎ በማከናወን፣ በመተባበርና በመተጋገዝ፤ ምርታማ ሰዎች እንደየድርሻቸው የላቀ ጥቅም መጎናፀፍ ይችላሉ።

በምርት ደረጃ በማህበረሰብ ውስጥ መፈጠር ያለበት ግንኙነት፤ "የእሴት ልውውጥ" ነው። የሙያ ጥረት አንድ እሴት ነው፤ ደሞዝ ደግሞ ሌላ እሴት። ደሞዝ ሳትከፍል የባለሙያዎችን ጥረት ለማግኘት መመኘት የለብህም። በሙያህ ሳትጥርና ሳትሰራም ደሞዝ እንዲከፈልህ መፈለግ የለብህም። እሴትን በእሴት ነው - (value for value)።

የንግድና የምርት ልውውጦች በሙሉ በዚህ መርህ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

## መርህ 10 ራስን መቻል (Self reliance)

በመማማርና በመወያየት ከሰዎች ጋር ስትተባበር፤ "ራስን መምራት" የሚለው መርህ መዘንጋት እንደሌለብህ ሁሉ፤ በምርት፣ በስራና በንግድ ከሌሎች ሰዎች ጋር ስትተባበርም "ራስን መቻል" የሚል መርህ ሊኖር ይገባል።

ወሳኝነት ከህይወታችን ጋር አስተሳስረን በምልአት ማገናዘብ የምንችለው የህይወት አላማ ሲኖረን ነው። እውነታውንና ምርጫችንን ያስተሳስርልናል።

በምን ሁኔታ ምን አደርጋለሁ? በቁንፅሌ አስተሳሰብ፤ በዘፈቀደ ይሄኛውን ነገር ወይም ያኛውን ጉዳይ ብቻ እያየን መደናበር ኪሳራን እንጂ ትርፍ እንደማያስገኝ ተገንዝበናል። የጉዳዮችንና የሁኔታዎችን ምንነት፣ ከአጠቃላይ ተፈጥሯዊ እውነታ ጋር አስተሳስረን መርሆዎችን በምልአት መተግበር የምንችለው የህይወት አላማ ሲኖረን ነው። ሃሳብና ተግባራችንን ያስተሳስርልናል።

በአጠቃላይ የህይወት አላማችንን በአግባቡና በግልፅ ለይተን ስንመርጥና ስንወስን፤ የምሉዕ ስብእና፣ የምሉዕ ህይወት መሰረት ይሆንልናል። የህይወት አላማ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ልናየው እንችላለን። በአንድ በኩል የህይወትና የአላማ ውስጣዊ ፍቅር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፤ የህይወትና የአላማ እቅድ ሆኖ ሊታይ ይችላል።

# 2ሀ. Passion (ውስጣዊ ፍቅር)

ጥልቅ ውስጣዊ ፍቅር ለአላማችን እጅግ ከፍተኛ ዋጋና ክብር እንደምንሰጥ ያረጋግጣል።

የህይወት አላማችን፤ ያለማቋረጥ በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወትን መቀዳጀት ስለሆነ፤ ውስጣዊ ፍቅር ማለት፤ በህይወት ፍቅር መጥለቅለቅ እንደማለት ይሆናል። ጥልቅ ፍቅር፣ ሃያል ጉልበት ነው።

ለየትኛውም እንቅፋትና ተግዳሮት፤ እጅ ሳንሰጥ መርሆቻችንን ለመተግበር የሚያስችለን የሃይል ምንጭ ነው - ጥልቅ የህይወት ፍቅር። ስለዚህ ውስጣዊ ፍቅር ስንል፤ የአላማና የመርህ ፍቅርም ይሆናል።

የህይወት አላማችን በሙያ ምርጫ አማካኝነት የሚገለፅ በመሆኑ፤ ውስጣዊውን ፍቅር የሙያ ፍቅር ልንለው እንችላለን። ለዚህም ነው፤ ከመነሻ አቅማችን ጋር ዝንባሌያችንን በደንብ ማጤን የሚኖርብን። በምንወደው የሙያ መስክ ስንሰማራ፤ የየእለቱ ስራችንና ጥረታችን አሸቻጋሪ ሸክም አይሆኑብንም። ውስጣዊ አቅማችንን በሚያመክን ድብርት አንሰቃይም።

በተቃራኒው የዘወትር ስራችንና ጥረታችን የማያቋርጥ የደስታ ምንጫችን ይሆናል። በየጊዜው የምንቀዳጀው ስኬት ደግሞ ድርብ ደስታን ያጎናፅፈናል።

ዝንባሌ ግን፤ በአንዳች ተአምር የሚፈጠር አይደለም። ከልጅነታችን ጀምሮ በግልፅ ሳንረዳው ሲዳብር የቆየውን ዝንባሌ መርምረንና ምንነቱ አውቀን ለህይወት አላማ መጠቀም ተገቢ ነው። ዝንባሌያችንን በግልፅ ሳንለይና ሳናውቅ በአንድ የሙያ መስክ የህይወት ጉዞ ብንጀምርስ? ችግር የለውም።

ከሙያ መስክ ምርጫችን ጋር የሚስማማ፤ አዲስ ዝንባሌ ማዳበር ይቻላል። ለተወሰነ ጊዜ ትእግስታችንን ይፈታተን ይሆናል። በፅናት ጥረታችንን ከቀጠልን ግን በጣም ከባድ አይደለም። ከአጭር ጊዜ በኋላ፤ ከሙያ ጥረታችን የምናገኘውን ውጤት እየተመለከትን፤ በምናገኘው ውጤት ከመደሰት በተጨማሪ፤ የሙያ ጥረታችንም አስደሳች እየሆነልን ይመጣል - ዝንባሌና የሙያ ፍቅር ማዳበር ጀመርን ማለት ነው። የመርህ ፍቅር፤ የህይወት ፍቅርም በተመሳሳይ ነገድ በጥረትና በስኬት ተደጋጋፊነት እየዳበረ ይሄዳል።

የሙያ ፍቅር ሲኖረን፤ የሙያ እውቀታችንን፣ የሙያ ክህሎታችንና ስኬታችንን ይበልጥ እንድናሳድግ ለተጨማሪ አስደሳች ጥረት ያነሳሳናል። በዚህ ጥረት የምንቀዳጀው ሙያዊ እውቀት፣ ክህሎትና ስኬት ደግሞ እንደገና ከደስታ ስሜት ጋር የሙያ ፍቅራችንን ያጠናክራል።

ECMAP

ዋናው ቁልፍ ጉዳይ፤ የራስ ብቃት ነው። መነሻ አቅምን በመጠቀም፣ ለእያንዳንዱ እቅድ የሚመጥን አቅም (ብቃት) ማዳበርና ማሟላት ያስፈልጋል - የእውቀትና የሙያ፣ የባህርይና የጤንነት ብቃቶች።

ከዚሁም ጋር አብሮ፣ የገንዘብ አቅም፣ የቁሳቁስ አቅም፣ የመስሪያ ቦታ፣ የመሸጫ ቦታ፣ የጥጥ ማሽን፣ ማዳዳሪ፣ የእርሻ መስኖ፣ ቢሮ ወዘተ... እቅዶቹ እውን እንዲሆኑ መሟላት ያለባቸው ነገሮች መታወቅ አለባቸው - ከመነሻ አቅም ጋር ተገናዝበው።

የራስ ብቃትን ለማዳበር፤ ብቻችንን ከምናደርገው የመመርመርና የማሰብ፣ የስራና የተግባር ጥረት በተጨማሪ፣ ከሰዎች ጋር ምን አይነት ግንኙነቶችን መመስረት ይኖርብናል? መማርና መወያየት፣ ስልጠናና ልምምድ መውሰድ አለብን። በቀጠባ የገንዘብ አቅምን ማዳበር እንችላለን። በራስ ጥረት የስራ ቁሳቁስን መፍጠር፣ የስራና የመሸጫ ቦታ ማዘጋጀት ወዘተ እንችላለን። ግን ሽርክና ተጨማሪ የገንዘብ አቅምን መፍጠርስ? የስራ ቁሳቁስ መግዛትና ቢሮ መከራየትስ? እነዚህና ከሰዎች ጋር የሚኖረን ሌሎች ግንኙነቶች፣ የእቅዶቻችን አካል ናቸው።

# 2ሐ. Persuation (መግባባት በፈቃደኝነት)

በህይወት አላማችንና እቅዶቻችን ውስጥ የሌሎች ሰዎች ድርሻ ምንድነው? ከሰዎች ጋር የሚኖረንን ግንኙነት እንዴት መምራት እንዳለብን የምንመዝንባቸው መርሆዎችን ተመልክተናል።

የጋራ ህይወት፣ የጋራ አእምሮ፣ የጋራ እውቀት፣ የጋራ ጥረት ብሎ ነገር ስለሌለ፤ ምርጫና ውሳኔም የግል ነው። አንተን ተከቶ ማንም ማሰብ ስለማይችል፤ ማንንም ተከተሽ አንቺ ልታስቢለት ስለማትችይ፤ ምርጫና ውሳኔ ላይም ራስን የመምራት መርህ መዘንጋት የለብንም።

ነገር ግን መማማርና መወያየት እንደሚቻለው ሁሉ፤ የህይወት አላማ ላይም፤ እያንዳንዱ ሰው ራሱን እየመራ፤ ለየራሱ አላማ ፈጣን ስኬት ሲል በፍቃደኝነት መግባባት ይችላል። አንደኛው ሰውዬ ገንዘብ ከፍሎ መማር ይፈልጋል፣ ሌላውኛው ደግሞ እያስከፈለ ማስተማር ይፈልጋል። እነዚህ ሰዎች ለየራሳቸው አላማ ሲሉ በፍቃደኝነት ተግባብተው የትምህርት ግንኙነት መፍጠር ይችላሉ።

አንዱ ባለሙያ ለስራው ረዳት መቅጠር ይፈልጋል፤ ሌላው ከአንጋፋ ባለሙያ ጋር በረዳትነት መለማመድና ደሞዝ ማግኘት ይፈልጋል። እነዚህም በፍቃደኝነት የስራ ግንኙነት ቢፈጥሩ እንደሚጠቀሙ በመገንዘብ መግባባት ይኖርባቸዋል። ነገር ግን፤ ለመግባባትም ጥረት ያስፈልጋል።

አንደኛው ወገን፤ ምን ጥቅም እንደሚያገኝ በግልፅ አልታየው ይሆናል - በተለያየ ምክንያት። ስለዚህ ለአላማችን ውጤታማነት የሚጠቅም ግንኙነት ለመፍጠር፤ የማግባባት ጥረት ያስፈልገናል።

በዛቻ፣ በድብደባ ወይም በሌላ አስገዳጅ የጉልበት ተግባር አማካኝነት፤ መግባባትን መፍጠር አይቻልም። ሰዎችንና ራሳችንን እንደ አእምሮ ቢስ አውሬ ካልቆጠርን በስተቀር፤ ከማግባባትና ከፍቃደኝነት ውጭ ሌላ የግንኙነት መሰረት የለም።

ማግባባት ሲባል፤ ማታለል፣ ማሞኘት፣ መዋሸት፣ መደለል ማለት አይደለም። ከእውነታ ጋር የሚጋጭ መንገድ እንደማያዋጣና ውሎ አድሮ ህይወትን እንደሚያጠወልቅ በመርሆቻችን አረጋግጠናል። ስለዚህ ከሰዎች ጋር በምንመሰርተው የስራ ግንኙነት፤ ለየራሳችን አላማ ተጠቃሚ እንደምንሆን በተጨባጭ ማስረጃ በግልፅ ማሳየት ነው - ማግባባት ማለት።

የሚበለፅግ አስደሳች ህይወትን የሚያቀዳጅ እሴት (value) ለመፍጠር። የህይወት አላማችንን እውን ለማድረግ፤ ከእያንዳንዱ ደቂቃና እለት ጀምሮ ወራትንና አመታትን የሚሸፍኑ እቅዶች በየደረጃው ይኖሩናል።

ለህይወታችንና ለሙያችን ጥልቅ ፍቅር እናዳብራለን። ከሰዎች ጋር የምንፈጥረው ግንኙነት፤ ለየራሳችን አላማና እቅድ በሚጠቅም መንገድ፤ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

## 3ሀ. Profeciency (የሙያ ብቃት)

እሴት የማይፈጥር ወይም ውጤት የሌለው ጥረት፤ ከንቱ ልፋት እንጂ ስራ አይደለም። እውቀትን የማያስገኝ ሽምደዳና የትምህርት ቤት ምልልስ ከንቱ ልፋት ነው። ለመኖሪያነት ሳያገለግል በነፋስ የሚፈርስ የቤት ግንባታ፤ መድረሻው ያልታወቀ ጉዞ፤ ደስተኛ ቤተሰብን የማይፈጥር የጋብቻ ኑሮ ... ከንቱ ድካም ነው።

በግማሽ ሰአትና በቀላል ዘዴ የሚከናወነውን ነገር፤ ቀኑን ሙሉ በአስቸጋሪ ዘዴ ስንሰቃይበት ብንውል፤ ቅንጣት ተጨማሪ ዋጋ የለውም - የጊዜና የሃይል ብክነት እንጂ። የጥረትና የስራ ፋይዳ የሚመዘነው፤ በእሴቱና በውጤቱ ነው። ለውጤታማ ስራ የሙያ ብቃትን ማዳበር ወሳኝ የሚሆነውም በዚህ ምክንያት ነው።

## 3ሐ. Partnership (የስራ ትብብር)

ያለ ጥረት ወይም ያለ ስራ የሚገኝ እሴት ወይም ውጤት የለም ብለናል። ያለ ጥረት አንዳች እሴት አግኝተናል የምንል ከሆን፤ በሌላ ሰው ጥረት የተፈጠረ ውጤት ወስደናል ማለት ነው - ወድቆ ስላገኘን ወይም በልመና አልያም በዝርፊያ። ይህ መንገድ ደግሞ የህልውና ዋስትና ሊሆነን አይችልም።

ህይወታችን በሌላ ሰው ይሁንታ ስር እንዲወድቅ ያደርጋል። ተጨባጩ ኑሮአችን መቅኖ ያጣል። በዚያ ላይ የስብእና ከንቱነት ይጫነናል። ህይወቴን በራሴ የማለምለምና እሴት የመፍጠር ብቃት የሌለኝ ከንቱ ሰው ነኝ የሚል መንፈስ ይወርሰናል።

ህይወትን የምናለመልምበት ትክክለኛው መንገድ፤ በአይበገሬ ውጤታማ ስራ እሴት መፍጠር ነው። ከሰዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነትም በውጤታማ ስራ ላይ እንዲመሰረት ማድረግ አለብን። ከሰዎች ጋር የምንፈጥረው ትብብር፤ እንደየዝንባሌያችን እና እንደየሙያ ክህሎታችን - ወደ ስራ እንድንሰማራ ያስችለናል። እናም በስራችን ይበልጥ ውጤታማ እንሆናለን።

# 4. Prosperity (የመንፈስና የኑሮ ብልፅግና)

አላማ መያዝ፣ ማቀድ እና መስራት ይከብድ እንደሆን እንጂ፣ ከዚያ በኋላማ ምን ያስቸግራል የሚል ጥያቄ ሊፈጠርብን ይችላል። "ለደስታና ለብልፅግና ዋጋ መስጠት ቀላል ነው"፣ "ደግሞስ ደስታንና ብልፅግናን የማይወድ ማን አለ!" ብለን እናስብም ይሆናል። ራሳችንና አካባቢያችንን እንፈትሽ። "ገንዘብና ሃብት ይወዳል፣ የራሱን ጥቅም ታስቀድማለች" የሚል ንግግር ስንሰማ፣ ውግዘትና ውንጀላ ሆኖ የሚሰማን ለምን ይሆን? ማን ላይ የተነጣጠረ ውግዘት ነው?

አላስተዋልነው እንደሆን እንጂ ታታሪዎች ላይ ያነጣጠረ ውግዘት ነው። በማጭበርበርና በማታለል፣ በስርቆትና በዝርፊያ፣ በተንኮልና በሙስና ገንዘብ ለማግኘት፣ ሃብት ለማካበት ወይም ተጠቃሚ ለመሆን የሚፈፀሙ ተግባራትን ለማውገዝ ከተፈለገማ፣ በቀላሉ "ሌባ ነው፣ ዘራፊ ናት፣ አጭበርባሪዎች ናቸው" ብሎ መናገር ይቻላል።

ታዲያ በጥረታቸው ሃብት ለመፍጠር፣ በታታሪነታቸው ንብረት ለማፍራትና ህይወታቸውን አስደሳች ለማድረግ የሚፈልጉ ሰዎች፣ አድናቆት ሲገባቸው ለምን ይወገዛሉ? ሃብትን፣ ንብረትን፣ ገንዘብን፣ ደስታን ያልወደደ፣ በታታሪነት አይጥርም፣ ህይወቱን ለማቆየትና ለመደሰትም አይችልም። ስለዚህ እንዲህ አይነት ኋላቀርና ጭፍን ውግዘቶችን በፅናት መቃወም ይኖርብናል - ለደስታና ለብልፅግና ከፍተኛ ክፍር በመስጠት።

ለደስታና ለብልፅግና ከፍተኛ ከብር መስጠት ማለት፣

1. የህልውና ልምላሜ ገፅታዎች መሆናቸውን ጠንቅቆ መገንዘብ ማለት ነው።
2. ከሰዎች ድንቅ አእምሯዊ አቅምና ከሰዎች ድንቅ ተግባራዊ ጥረት የሚመነጩ ሽልማቶች እንደሆኑ መንገዘብ ማለት ነው። የመንፈስና የኑሮ ሽልማቶች ናቸው - ደስታና ብልፅግና።

ለደስታና ለብልፅግና ከፍተኛ ከብር ስንሰጥ፣ እነሱን ለመቀዳጀት የሚያስችለንን አላማ ለማሳካት በትክክለኛ አስተሳሰብና በትክክለኛ መርሆዎች የስራ ተነሳሽነትና የሰራ ወዳድነት አቅማችን ይጠናከራል።

# 4ሀ. Pleasure (ደስታ)

ደስታ የህይወት ልምላሜ መገለጫ ነው - የመንፈስ ብልፅግና ወይም ሽልማት ልንለው እንችላለን። በአቋራጭ የሚገኙ ደስታ መሳይ ጊዜያዊ ስሜቶች በብዛት አሉ። ግን ከእውነተኛ ደስታ ጋር ሊምታቱብን አይገባም።

ህይወትን የማያለመልሙ ደስታ መሳይ ጊዜያዊ ስሜቶች፤ ድርብ ጉዳት አላቸው። በጊዜ ነቅተን ቶሎ መፍትሄ ካላበጀንላቸው፤ ህይወትን ከሚያለመልም ጎዳና እንድንዘናጋና መንገድ ስተን እንድንወጣ ያደርጉናል። በዚያ ላይ፤ የእውነተኛ ደስታን ጣእም ምንኛ ጣፋጭ እንደሆነ ቀምሰን እንዳናውቅ ወይም እንድንረሳ ያደርጉናል።

የኑሮ ብልፅግና (ንብረትና ሃብት) የስኬት አካላዊ መገለጫ እንደሆነው ሁሉ፤ እውነተኛ ደስታም የስኬት አእምሯዊ መገለጫ ነው - የመንፈስ ብልፅግና። ከትክክለኛ አስተሳሰብና መርህ፣ ከአላማ ፅናትና እቅድ፣ ከውጤታማ አይበገሬነትና የሙያ ስራ የሚገኝ ስኬት፤ እውነተኛ ደስታን ያጎናፅፋል።

ለዚህ እውነተኛ ደስታ ከፍተኛ ክብር የምንሰጥ ከሆነ፤ በደስታ መሳይ ጊዜያዊ ስሜቶች በቀላሉ አንታለልም። ወዲያኑ ነቅተን፤ ወደ እውነተኛው ጎዳና መመለስና መገስገስ እንችላለን።

# 4ሰ. Property (ንብረት)

ድንገት ቤታችን ሁሉ በንብረት እንዳይጥለቀለቅ መስጋት አለብን እንዴ? ድንገት ሃብት በሃብት እንዳንሆንም ብለንስ መጨነቅ ይኖርብናል እንዴ? በጭራሽ መስጋትና መጨነቅ የለብንም። ለምን? ሃብትና ንብረትን ማክበር ይኖርብናል። ለምን? ሃብትና ንብረት ህይወትን የሚያለመልም ስለሆነ፤ እንዲሁም ሰው ያላፈራው ንብረትና በሰው ያልተፈጠረ ንብረት ከየትም ስለማይመጣ።

ከምንም ነገር አንዳች ነገር መፍጠር አይቻልም። ያለአእምሮ አንዳች አዲስ ነገር አይፈጠርም። እውኑ ተፈጥሮ፤ በአእምሮ አማካኝነት ሲቀረፅ ነው፤ ሃብትና ንብረት ተፈጠረ የሚባለው።

እውኑ ተፈጥሮ በነባር ቅንብር (ተፈጥሯዊ - ያለ፣ የነበረ).... ተግባር በአእምሮ የተመራ .... እውኑ ተፈጥሮ በአዲስ ቅንብር (ሰው ሰራሹ- ሃብት፣ ንብረት)

በአእምሮ ውስጥ የተፈጠረ የሃሳብ ቅንብር (እውቀት፣ መርህ፣ አላማ፣ እቅድ) .... ተግባራዊ ጥረት (በአእምሮ የተመራና በእውኑ ተፈጥሮ ውስጥ የሚካሄድ ጥረት) ... በእውኑ ተፈጥሮ ውስጥ የተፈጠረ አዲስ ቅንብር (ሃብት፣ ንብረት)

ስለዚህ፤ ሃብትና ንብረት ማለት በአእምሯችን ውስጥ የነበረው ሃሳብ፣ በእውኑ አለም ቅርፅና አካል ሲይዝ ማለት ነው። በቀጥታ ኑሯችን ውስጥ ጥቅም ላይ የምናውለው፤ ወይም በሽያጭ የምንለውጠው አልያም አስተማማኝ የገቢ ምንጭ ሊሆን ይችላል - የፈጠርነው ሃብትና ንብረት።

መኪና ወይም ቤት፤ ድንች ወይም ጫማ፣ የዜማ ወይም የግጥም ድርሰት፣ መፅሃፍ ወይም ስእል፣ መልካም የሙያ ዝና ወይም የብቃት ምስክር ወረቀት፣ አውሮፕላን ወይም ኮምፒዩተር ሊሆን ይችላል - ያፈራነው ሃብትና ንብረት። ድንቅ የአእምሮ አቅማችንን ምን ያህል ልንጠቀምበት እንደቻልን ያሳያል - ሃብትና ንብረት።

ሃብትና ንብረት ማለት፤ በእውኑ ተፈጥሮ ውስጥ ለህይወት ልምላሜ በሚጠቅም መንገድ አዲስ ቅንብር መፍጠር ማለት ነው። ህይወትን ምን ያህል ማለምለም ወይም ማበልፀግ እንደቻልን ያሳያል - ሃብትና ንብረት።

እዚህ ላይ፤ ሃብትና ንብረትን ላለማክበር እንደሰበብ የሚነሳ ጉዳይ አለ። አጭበርብረው ወይም ሰርቀው ባለንብረትና ባለሃብት የሚሆኑ ሰዎች ይኖራሉ የሚል ወቀሳ እንስማለን። ታዲያ አጭበርባሪዎቹንና ሌቦቹን መውቀስ እንጂ፤ ሃብትና ንብረትን ማውገዝ ለምን አስፈለገ? የተሰረቀ የሃኪም መታወቂያ ይዞ፤ ሆስፒታል ውስጥ የሚያጭበረብር ሰውም ይኖራል። በዚህ

ኮርMAP

ሰበብ የህክምና ዶክተርንና የሆስፒታል ህክምናን እናወግዛለን እንዴ? ሃብትና ንብረት ላይም ተመሳሳይ ነው።

የተጭበረበረ ሃብትና የተሰረቀ ንብረት ሲያጋጥም፣ ሌባውና አጭበርባሪውን በማውገዝ፣ ለእውነተኛ ባለቤቱ በክብር እንዲመለስ መፈለግ ይኖርብናል - በጥረቱ ያንን ንብረትና ሃብት ለፈጠረው ሰው። በአጠቃላይ በምንም ሰበብ ሃብትና ንብረት እንዲወገዘ መተባበርም ሆነ በዝምታ ማለፍ የለብንም። ሃብትና ንብረት ክቡር መሆናቸውን ተገንዝበናልና።

የደሞዙን ያህል የማይሰራ እልማጭ ወይም ቀሽም ሰራተኛ፤ ለተወሰነ ጊዜ ቀጣሪውን ማታለል ቢችልም ውሎ አድሮ በስራው ደካማነት ይጋለጣል።

ከሰራተኛው ሙያና ጥረት ጋር የማይመጥን ደሞዝ የሚከፍል ቀጣሪ፤ ብዙም ሳይቆይ ጎበዝ ሰራተኞቹ አንድ በአንድ እየለቀቁ ወደ ተሻለ ቦታ ለመሄድ መሞከራቸው አይቀርም። ጎበዝ ሰራተኞቹን በማጣት፤ ስራው እየተዳከመ ወደ ኪሳራ ያዘግማል። ስህተቱንም በማስተካከል፤ ጎበዝ ሰራተኞችን መልሶ ማግኘት ከፈለገ፤ የግድ የተሻለ ደሞዝና የስራ ሁኔታዎችን ማቅረብ መቻል ይኖርበታል።

ሰዎች ያለ አስገዳጅ ሃይል በፍቃደኝነት በሚመሰርቱት ግንኙነት ውስጥ፤ የሚጠቅም ነገር በማቅረብ ነው ተጠቃሚ መሆን የሚቻለው፤ እሴትን ለእሴት። አለበለዚያ ከኛ ጋር ሊገበያይ ወይም የስራ ግንኙነት ለመፍጠር የሚፈልግ ሰው አይኖርም።

እቃ ስንገዛም ሆነ ስንሸጥ፣ ትምህርት፣ መፅሃፍና ሙዚቃ የመሳሰሉ አእምሯዊ እሴቶችን ስንለዋወጥም ሆነ ስንገበያይ፣ ሰራተኛ ስንቀጥርም ሆነ ስንቀጠር፣ ሁሌም በርካታ አማራጮችን ማመዛዘናችን አይቀርም።

ከአማራጮቹ መካከል አንደኛውን የምንመርጠው እንዴት ነው? የተሻለ ጥቅም (ማለትም ትርፍ) ስለሚያስገኝልን መሆን አለበት። ሰዎች ለየራሳቸው አላማ መገበያየትና ወይም የስራ ግንኙነት መፍጠር የሚኖርባቸው፤ ከግብይታቸውና ከግንኙነታቸው ተጠቃሚ ወይም አትራፊ ስለሚሆኑ ነው።

የሰዎች ግንኙነት ውስጥ የምናገኘው ትርፍ፤ ቁሳዊ ብቻ አይደለም። መንፈሳዊ ጥቅሞችም አሉ - ጓደኝነትና ፍቅር የመሳሰሉ። እነዚህ ውድና ድንቅ ጥቅሞችም፤ እውን ሊሆኑ የሚችሉት በትክክለኛ መርህና በእሴት ፈጠራ ላይ የተመሰረቱ ሲሆኑ ነው። ሁለት ሰዎች ጓደኞች ወይም ፍቅረኛሞች መሆን የሚኖርባቸው፤ ሁለቱም የመንፈስ ጥቅም (ደስታ) የሚያገኙበት ሲሆኑ ነው።

## 4ሐ. Praiseworthy (የጅግንነት አርአያ)

ውስጣዊ ሃይላችን ወይም ብሩህ መንፈሳችን የሚነቃቃው፣ በብሩህ ኪነጥበብ ብቻ አይደለም። የጀግንነትና የስኬት ህይወት አርአያ የሆኑ ሰዎችም መንፈሳችንን ያነቃቃሉ። እንዲያውም፣ ከሰዎች ዘንድ ከምናገኛቸው እሴቶችና ጥቅሞች መካከል፣ የጀግንነት አርአያነታቸው እጅግ ወድና ድንቅ ነው።

ጀግናን ስናደንቅ፣ ራሳችንንም እየገነባን እንደሆን መገንዘብ አለብን። የጀግኖችን ተጨባጭ ኑሮ በማየትም ሆነ ታሪኩን በመስማትና በማንበብ፣ "ይሄ ጀግና፣ ድንቅ የአእምሮ አቅሙን በመጠቀም በጀግንነት ስኬትን መቀዳጀት ችሏል" እንላለን።

"ሰው መሆን ታላቅ ክብር ነው - በአስደሳች የብልፅግና መንገድ የራሱን ህይወት መቅረፅ የሚችል የጀግንነት ድንቅ አቅም አለው" ከሚል እውነታ ጋር፣ "እኔም እችላለሁ" በሚል መንፈሳችን ይነቃቃል። ብሩህ ስብእናችን ይታደሳል።

## ነጻጅ ሞልተናል፤ እንበረር

ለብሩህ መንፈስና ለብሩህ ስብእና እጅግ ከፍተኛ ክብር መስጠት እንዳለብን ተገንዝበናል። "ችያለሁ፤ ወደፊትም ይበልጥ እችላለሁ" በሚል መንፈስ የሚበለፅግ ስብእና፤ ከትክክለኛ አመለካከትና መርህ፣ ከፅኑ አላማና እቅድ፣ ከብርቱ ስራና ከህሎት የመነጨ ውድ እሴት ነው። ምን ይሄ ብቻ!

ብሩህ ስብእና፤ እንደገና ተመልሶ ለተጨማሪ ብልፅግና በሚጠቅም መንገድ፤ መነሻ ጉልበትና የጉዞ ሃይል ይሆነናል። አመለካከታችንን፣ እቅማችንንና መርሆቻችንን ይበልጥ እንድናሳድግ፤ አላማችንን፣ የአላማ ፍቅራችንንና እቅዳችንን እንድናዳብር፤ ስራችንን፣ እይበገሬነታችንንና ከህሎታችንን እንድናጠናክር ሃይል ይሰጠናል - ብሩህ ስብእና።

በአጠቃላይ ብሩህ ስብእና፤ በህይወት ካርታችን ላይ ለምናደርገው ግስጋሴ ነዳጅ ይሆነናል። ስለዚህ በየጊዜው የሚበለፅግ አስደሳች ህይወት በምንጎናፀፍበት የህይወት ካርታ ላይ እንንሸራሸር፤ እንገስግስ።

ተፈፀመ!

# ልዩ የኑሮMAP ፕሮጀክት ግብዣ

1. በኦሮሚኛ፣ በትግረኛና በሌሎች ቋንቋዎች ለመተርጎምና አብሮ ለማሳተም ለምትፈልጉ፤ ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ ነን።
2. "ኑሮMAP - ለህፃናት"…. ህፃናጽ በተፈጥሮ "Systems thinkers" ናቸው ይባላል፡፡ ለህፃናት የሚሆን የST መፅሃፍ ለመሥራት የሚፈልግ ባለሙያ መነጋገርና መተባበር እንችላለን፡፡
3. ከማንኛውም የትምህርትት መስክ በኑሮMAP ላይ, መመረቂያ ፅሁፍና ጥናት መስራት ለምትፈልጉ መተባበር እንችላለን!!
4. በኑሮMAP ፍልሥፍና ላይ የተመሠረተ የልቦለድና ሌላም የሥነ ጥበብ (ART) ፈጠራዎችን ለመስራት ለምትፈልጉ መተባበር እንችላለን፡፡
5. ለትርፍ ወይም ለጠቃሚ የማህበረሰብ ለውጥ ኑሮMAPን ከተለያዩ የሚዲያ ዝግጅቶችና መንገዶች ጋር አገናኝቶ ለመስራት ለምትፈልጉ የሚዲያ ባለሙያዎችና ድርጅቶች በዚህ አድራሻ እንነጋገር፡፡

Email:-erssido@yahoo.com
WWW.Dr.erssidobooks.Com

# ይህንን መጽሐፍ እንዴት ጻፍኩት

የሙያ መሰረቴ ህክምና ሳይንስ መሆኑ ለSystems thinking (ST) ማለትም
ለቅንብራዊ አስተሳሰብ አረዳዴ የማያወላዳ መሰረት የሰጠኝ ቢሆንም፣ በተደራጀ መልኩ ከST
ጋር የተዋወቅሁት ከ8 ዓመት በፊት የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ የኤች አይቪኤድስ ጽ/ቤት ኃላፊ ሆኜ
ስሰራ ነው።

የ14 ሚሊዮን ሰዎች የሚኖሩት፣ ከ56 በላይ ብ/ብሐረሰቦች የሚገኙበት፣ እንደ ቁጥሩ ሁሉ በርካታ የሆኑ ባህሎችና ቋንቋዎች የፈጠሩት ውስብስብ አኗኗርን አስቡት፣ የግለሰብና የማኅበረሰብን ዘርፈ ብዙ ባህሪያትንም አሰላስሉት።

እንግዲህ በ29 ዓመት እድሜ ከዶክትሬት ዲግሪ እና የ5 ዓመት የጤና ጣቢያ የሃኪምነት ልምድ ሌላ፣ ጠንካራ የማናጅመንት ልምድ ሳይኖረኝ በ«ድንገት» ይህ ሃላፊነት ሲሰጠኝ መፍትሄ ፍለጋ ላይ ታች ማለት ነበረብኝ። በዚህ ጊዜ ነበር ከST ጋር የተዋወቅኩት።

የተባበሩ መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) የሚያካሂደው በST ላይ ያተኮረ የሜይንስትሪሚንግና የአመራር የስልጠና ለመጀመሪ ጊዜ የወሰድኩት ያኔ ነው። ለ4 ጊዜም በደቡብ አፍሪካ የአሰልጣኝነት ስልጠና ወስጄ በኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ከ10,000 በላይ ሃላፊዎችን ፣ወጣቶችን፣ መምህራንን እና ባለሙያዎችን አሰልጥኛለሁ።

በወቅቱ የነበረው የደቡብ ክልል ኤችአይቪ ፕሮግራም አገር አቀፍ ምሳሌ ለመሆን የበቃውና ለአፍሪካም እንደ ማኅበረሰብ ውይይት ያሉ የፕሮግራም ዘርፎችን በአርአያነት ያበረከተበት ምስጢር ሌላ ሳይሆን ST ነው።

በአጠቃላይ በግሌ፣ በመንግስት ስራና በቢዝነስ ስራ የST ሳይንስን በመጠቀሜና ሌሎችም እንዲረዱት በማድረጌ ኢትዮጵያ ውስጥ በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ፈጥሬአለሁ ብዬ አምናለሁኝ።

መጨረሻም ከብዙ ሰልጣኞችና ከጓደኞቼ የተሰጠኝ አስተያየት በST ዙሪያ በሚዲያ ትምህርት እንዳቀርብ ወይም መፅሃፍ እንድፅፍ የሚገፋፉ ነበር።

ይህንን አዲስ ሳይንሳዊ ፅንሰ ሃሳብና የተግባር መሣሪያ በአማርኛ ለኢትዮጵያ አንባቢያን ለማዘጋጀት ሞቅ ቀዝቀዝ እያለ ከ7 ዓመት በላይ ፈጅቷል፡፡ በርካታ መፃህፍትንና ፅሁፎችን ማንበብ፣ 200 ከሚደርሱ ስልጠናዎች ላይ ኢትዮጵያዊ ሀሳቦችን መሰብሰብና ማጠናከር እንዲሁም ሌሎች ጥረቶች ማድረግ ነበረብኝ።

ብዙ ባለሙያዎች የመፅሃፉን የመጀመሪያ ፅሁፍ እንዲሁም የመፅሃፉን የተለያዩ ክፍሎች

በማንበብ ፖክቢ አስተያየት ሰጥተውኛል። እንዲያም ሆኖ ጊዜ ወሰዱ ሌ። ይህንን ጥልቅ፣ ግን ደግሞ "ቀላል" ሳይንስ እንዴት ምቹ በሆነ መንገድ ለሚሊዮኖች ማሳወቅ እንደሚቻል ለማሰብ ተጠቀምኩበት - ጊዜውን።

በሲንጋፖረ ዩኒቨርሲቲ 3 ፕሮፌሰሮች የጻፉት Big fish eat small fish የምትል በጣም "ትንሽ" መፅሃፍ ማግኘቴ እንደመነሻ ረድቶኛል። በዚሁ መነሻነት የመጣ ነው የአሳዎቹ ታሪክ። መፅሃፉ መነሻ ታሪክ ስለሰጠኝ መጠቀስ አለበት። ግን የአሳዎቹ ታሪክ በእጅጉ ተሻሽሎና ራሱን የቻለ ኢትዮጵያዊ ስራ ሆኖ እንዲቀርብ ተደርጓል።

# ዋቢ መፃህፍት
# Reference Books

እጅግ በርካታ መፅሀፍት ለዚህ መፅሀፍ ግብአት ሆነዋል የሚከተሉት ሶስቱ በተለይ መጠቀስ ይኖርባቸዋል።


1- Peter Senge, The Fifth discipline, 1994
2- Leonard Piekof, Objoctivism the Phillo-
sophy of Ayn Rand
3- Big fish eat Small fish

- እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሕይወት ቀራፂ ነው!
- አእምሯችንን በዝባዝንኬ ካጨቅነው፤ ውጤቱም ያው ነው። Garbage in, garbage out (GIGO)
- አእምሯችን የስኬት መሳሪያ ከታጠቀ ደግሞ፤ የስኬት ምህዋር ይፈጥራል። Value in Value out (VIVO)
- ከGIGO ወደ VIVO እንሸጋገር።

ይህ መጽሐፍ በተረትና ምሳሌ እጅግ ታላቅ ቁም ነገር ለማስጨበጥ የተጻፈ ነው ::‹Systems thinking ባለፉt 50 አመታት እያደገ የመጣ የቴዎሪና ተግባር አዲስ መሳሪያ ሆኖ ለውስብስብ የኑሮ ችግሮች እንደ በቢዝናስ ድህነት ኤች አይቪ ወዘተ ችግሮችመፍቻ እየዋለ ያለ አዲስ ሳይንስ ነው ::

ዋጋው ብር 40.00 (አርባ ብር) $ 12.00

Cver Design By Ashenafi Sertse

Printed by Addis Trat PLC